መጽሐፈ አክሲማሮስ

ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ



ዘስድስቱ ዕለታት
ንባቡና ትርጓሜው

አዘጋጅና አሳታሚ፡-
አባ ሠናይ ምስክር
ባሕር ዳር

ለ፪ ጊዜ በ፪፻፲፪ ዓ.ም በትንሣኤ
ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ

መጽሐፈ አክሲማሮስ

ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ



ዘስድስቱ ዕለታት
ንባቡና ትርጓሜው

አዘጋጅና አሳታሚ፦-
አባ ሠናይ ምስክር
ባሕር ዳር

ለ፪ ጊዜ በ፪፻፲፪ ዓ.ም በትንሣኤ
ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ

©
ያለአዘጋጁና አሳታሚው ፈቃድ መልሶ
ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው::



ለእግዚአብሔር ምድር በምልአ። ዓለምኒ ወኀሌሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ። ወውእቱ በባሕር ሣረራ። ወበዓፍላግኒ ውእቱ አጽንዓ። ምድርና መላዋ ለእግዚአብሔር ናት። ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ። እርሱ በባሕሮች መሥርቷታልና። በፈሳሾችም አጽንቷታልና።

መዝ 23÷1-3

መቅድም



መታሰቢያነቱ

የባሕር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳምን ለአርባ ዓመታት ሲታስተዳድሩ ለቆዩና አሁንም በማስተዳደር ላይ ላሉት ታላቅ መንፈሳዊ አባት ለመልአከ ገነት ኃይለ ማርያም ፈንታሁን ይሁንልኝ።

መልእክት

ለዚህ አክሲማሮስ ለተባለው መጽሐፍ አቀራረብ የተሠጠ መልእክትና ልዩ አስተያየት

አክሲማሮስ ማለት የስድስት ቀናት ሥነ ፍጥረት መጽሐፍ ነው፤ የሚተላለፈውም በተለይ ለካህናትና ለክርስቲያኖች ነው። እነዚህም ለልጆቻቸው ያስተላልፉታልና፤ የፍጥረታት ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ ጠቢበ ጠቢባን ነው፤ ጠቢባን ነን የሚሉ ሁሉ ብዙ ቢፈላሰፉ ከተፈጠረው ነገር ነው፤ ጠቢበ ጠቢባን እግዚአብሔር ግን «እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ» ነው ማለት ከሌሉበት ወደ ሚኖሩበት አምጥቶ ነው እነዚህም አራቱ ባሕርያት መሬት፣ ውኃ፣ ነፋስ፣ እሳት ናቸው። በሰማይም በምድርም የተፈጠሩት ሁሉ ከእነዚህ ያልተፈጠረ የለም፡ ጠቢባን ነን፤ ፈላስፋ ነን የሚሉ ሁሉ እነዚህን ሥነ ፍጥረቶች በመመርመር ነው፡ ይህም ችሎታቸው በአንዱ አምላክ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋልና ነው። ረቂቁን ፈጣሪ እግዚአብሔርን ማንም ፍጡር ማየት የሚችል ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ «ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እም ቅድመ ዓለም ይትዓወቅ በፍጥረቱ» ረቂቁ እግዚአብሔር የሚታየውና የሚታወቀው በፈጠረው ፍጥረት ነው፤ ሮሜ 1÷21። ከላይ፣ ከታች ከአራቱ ማዕዘን ሁሉ የተፈጠሩትን ስንመለከት ፈጣሪን እናየዋለን፤ አይተንም እናውቀዋለን፤ አውቀንም እናደንቀዋለን፤ አድንቀንም አዲስ ምሥጋና ለስሙ እናቀርባለን። «በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር» በሰማይ እንደተደረገ እንዲሁም በምድር ይሁን ማለት መላእክት በሰማይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው እንዲያመሰግኑ የሰው ልጆችም በምድር ሥነ ፍጥረትን እያዩ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ያመሰግናሉ፤ ከዚህም ሌላ የሚበልጥ ሰላምና ደስታ ለሰው ልጅ የለውምና ዘወትር ሥነ ፍጥረትን

መቅድም

እንመልከት ይህን አክሲማሮስ የስድስት ቀናት ሥነ ፍጥረት ከየገዳማቱና አድባራቱ ከየግለሰቦችም በትጋትና በንቃት በማሰባሰብ ጥንታዊ ይዘቱንም እንደወቅቱ በማስተካከል ማለትም፣ እንዲል፣ እንዳለ፣ እንዲሉ የሚለውን ጥንታዊ አቀማመጥ ጸሐፊውንና ደራሲውን በመለየት እንዲያውም ይህን መጽሐፍ ልዩ የሚያደርገው ጥቅሶችን በያሉበት በማሰባሰብ ትክክል በማስቀመጥ ሊቃውንትን በሚያስደንቅ ሁኔታ አዘጋጅተው ለዚህ ጎትመት በማብቃታቸው ታታሪነታቸውንና የተፈጥሮ ስጦታቸውን በሌላም በኩል «ኩን ገንጻሌ መጻሕፍት» እንደሚለው ሌትና ቀን ቃለ መጻሕፍትን ተመልካችነታቸውን ስለማውቅ በሊቃውንት ፊት ይህን የሥነ ፍጥረት መጽሐፍ አስተካክለው ያቀረቡትን ብልህና አስተዋይ አባት አባ ሠናይ ምስክር የተባሉትን የባሕር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም የስብከተ ወንጌል ኃላፊ የሆኑትን ላመሰግናቸው እወዳለሁ፤ ሰውን ወዳጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ክህነታቸውን ይባርክ፣ እድሜያቸውን ያስረዝም፤ ጤንነታቸውን ይጠብቅ አሜን::

መልአከ ገነት ኃይለ ማርያም ፈንታሁን
የባሕር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም
አስተዳዳሪና የሰበካ ጉባኤ ሊቀ መንበር

፲፱፻፺፬ዓ.ም
ባሕር ዳር

ምስጋና

ይህን አክሲማሮስ መጽሐፍ ለሕትመት እንዲበቃ

- ባላቸው ትርፍ ጊዜ ተጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ ከጎኔ ሳይለዩ በኮምፒውተር ጽሑፍና ለቀማ፣ በማቀነባበርም ለረዱኝ ለተክለ መድኅን ከነቤተሰቦቻቸው፤
- በገንዘባቸው ለረዱኝ ለአቶ ተስፋዬ መንግሥት (ወልደ ትንሳኤ)ና ለባለቤታቸው ወ/ሮ ሐረጓ ወንዱ (ወለተ ኪዳን)፣ ለMr. Jhon (ተ/ዮሐንስ)ና ለባለቤታቸው ለወ/ሮ ትዕግስት ይሄነው (ወለተ ሐና)፣ ለMr. Arto(ሀ/ሥላሴ)ና ለባለቤታቸው ለወ/ሮ አስቴር ትዕዛዙ(ዓፀደ ማርያም)፣ ለአቶ ሀብታሙ ብዙነህ (ሀ/ማርያም)ና ለባለቤታቸው ለወ/ሮ የኔወርቅ ታያቸው (ዓፀደ ማርያም) ከነቤተሰቦቻቸው፤
- ሀሳብና ሞራል እና የተለያየ ድጋፍ በመስጠት ላበረታቱኝ፤ የእመቤታችን የቃል ኪዳን ልጆች ሁሉ፤ ሁሉን ማድረግ የማይሳነው እግዚአብሔር የማቱሳላ እድሜን ሰጥቶ፣ በሕይወት ጠብቆ፣ ሥራቸውን አቃንቶ ገንዘባቸውን ባርኮ ያቆይልኝ ዘንድ እየጸለይሁ በእግዚአብሔር ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::



አዘጋጅና አሳታሚ፡-
አባ ሠናይ ምስክር
የባሕር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ
ገዳም ስብከተ ወንጌል ኃላፊ
ስልክ፡- 058 2200849
» 2204565
ባሕር ዳር

ማውጫ

ገጽ
መቅድም ..... ፩
ታሪክ ..... ፫
አክሲማሮስ ዘእሑድ
- ክፍል አንድ ..... ፱
- ክፍል ሁለት ..... ፲፯
- ክፍል ሦስት ..... ፴፯
- ክፍል አራት ..... ፵፯

አክሲማሮስ ዘሰኑይ
- ክፍል አንድ ..... ፶፫
- ክፍል ሁለት ..... ፷፫

አክሲማሮስ ዘሠሉስ
- ክፍል አንድ ..... ፸፫
- ክፍል ሁለት ..... ፸፱

አክሲማሮስ ዘረቡዕ
- ክፍል አንድ ..... ፰
- ክፍል ሁለት ..... ፰፭፩

አክሲማሮስ ዘሐሙስ
- ክፍል አንድ ..... ፰፴፰
- ክፍል ሁለት ..... ፱፵፩

አክሲማሮስ ዘዓርብ
- ክፍል አንድ ..... ፱፵፯
- ክፍል ሁለት ..... ፱፶፫
- ክፍል ሦስት ..... ፱፷፬
- ክፍል አራት ..... ፱፸፩
- ክፍል አምስት ..... ፱፹፫
- ክፍል ስድስት ..... ፱፺
- ክፍል ሰባት ..... ፪፻፬
- ክፍል ስምንት ..... ፪፻፲፬

መግቢያ

መቅድም

ይህን አክሲማሮስ መጽሐፍ እንዳዘጋጅና እንዳሳትም ያነሳሳኝ ምክንያት

- የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ብዙ ጊዜ በዋቢነት ይጠቅሱታል። ነገር ግን እንደተፈላጊነቱ መጠን ተዘጋጅቶና ታትሞ ሕዝበ ክርስቲያኑ ሊጠቀምበት ባለመቻሉ፤
- ሁለተኛውም ከሌሎች መጻሕፍት በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት የሥነ ፍጥረት መጽሐፍ መሆኑን በማመን ነው።

ከአሁን በፊት ብዙ ነቢያት በተለያየ መልኩ ቢጽፉም አክሲማሮስ የሚል ስም ሰጥቶ የጎደለውን አምልቶ የረቀቀውን አጉልቶ ሀያ ሁለት ሥነ ፍጥረት ብሎ ቆጥሮ የጻፈ ግን ቅዱስ ኤፍሬምዮስ ነው።

ስለዚህ ይህንን መጽሐፈ አክሲማሮስ ቀለል ባለ መልኩ ተዘጋጅቶና ታትሞ ሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲሰቀምበት በነበረኝ ከፍተኛ ፍለጎት

«ሰአሉ ወይትወሀበክሙ ጎሡ ወትረክቡ ጐድጉዱ ወይትረጎወክሙ እስመ ኩሉ ዘይስእል ይነሥእ ወዘኒ የጎሥሥ ይረክብ ወለዘኒ ጐድጐደ ይትረጎዎ። ማቴ ፯፥፯-፱

ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኛላችሁ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችኋል የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልግም ያገኛል መዝጊያንም የሚያንኳኳ ይከፈትለታል። ማቴ 7፥7-9። ብሎ ጌታችን እንዳስተማረን እኔም

- በአንዳንድ ገዳማትና አድባራት እንዲሁም ከአባቶች መጽሐፉን በማፈላለግና የተሻለውንም በመምረጥ፣ አንዱ የተወውን ሌላው ያስተካክላል፤ ይህንን ሁሉ በማቀነባበር፤
- አማርኛው እየቀደመ ግእዙ ይከተል የነበረውን በማስተካከልና ሥርዓት በማስያዝ፤ ግእዙ ተጠቅሶ ሳይተረጐም የታለፈውን በመተርጐምና ምዕራፍና ቁጥሩን በመጥቀስ፤

መቅድም

- እንዳለ እገሌ እያለ ያለፈውን ሁሉ ማስረጃዎችን በየቦታቸው በማስቀመጥና መልክ በመስጠት፤
- የመጽሐፉን ስም ትርጓሜ በመተርጐምና የባለ መጽሐፉን ስምና ታሪክ በመግለጽ
- ለመጽሐፉ የየዕለቱን ርዕስ በመስጠትና ለአንባቢ እንዳይሰለች በማሰብ በክፍል በመክፈል፤ የገጽ ቁጥርና ከግእዙ ላይ የጎን ቁጥር በመስጠት፤
- የፊደላቶችን ሥርዓትም በመጠበቅ ይህንን በመሳሰለው ሁሉ ከብዙ ዓመታት ድካም በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ቅዱስ ፈቃዱ ሆኖ ተዘጋጅቶ ለጎትመት በመብቃቱ «ምንተኑ አዐስዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ኩሉ ዘገብረ ሊተ፤ ስላደረገልኝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ምን እመልሳለሁ» እንዳለ ነቢይ ዳዊት እኔም ምን እመልሳለሁ እያልሁ ይህንን መጽሐፍ አዘጋጅቼና አሳትሜ ለአንባብያን ሳቀርብ ደስታ ይሰማኛል። የረዳኝን የፍጥረታት ፈጣሪንም በፍጹም ልቤ ዘወትር አመሰግነዋለሁ።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ልዑል

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር አሜን።

አዘጋጅና አሳታሚ

አባ ሠናይ ምስክር

መቅድም

መቅድም ማለት ወደ ቤት ለመግባት በሩን መክፈት እንደሚያስፈልግ ሁሉ ከመጽሐፉ ፍሬ ነገር አስቀድሞ የሚገኝ ጽሑፍ ማለት ነው::

«ይደልዎ ለዘያነብብ ቅድመ ይዝክር ስሞ ለበዓለ መጽሐፍ ወእምዝ ያንብብ ወይምህር»
መጽሐፍ የሚመለከት ሰው አስቀድሞ የደራሲውን ስምና ታሪክ ማወቅና መረዳት ከዚያ በኋላ መጽሐፉን ማንበብ፣ መተርጐም ይገባዋል ብሎ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደነገረን ሁሉ መቅድምም የሚዘጋጀው ስለዚህ ነው:: በዚህም መሠረት ለዚህ አክሲማሮስ መጽሐፍ ይህ መቅድም ተሰጠው:: የዚህ መጽሐፍ የስሙ ትርጓሜ ስድስት ቀን ማለት ነው::

የስድስቱን ቀን ሥነ ፍጥረት አምልቶ አስፍቶ የሚናገር ሀያ ሁለት ብሎ የሚቆጥር የቅዱስ ኤጲፋንዮስ መጽሐፍ ስም ነው:: /ኪ/ወልድ ክፍሌ ገጽ 219/
የስድስቱ ቀን ሥነ ፍጥረትስ አፈጣጠር እንደምነው ቢሉ ሥላሴ እምቅድመ ዓለም በአንድነት በሦስትነት ሳሉ አንድነታቸው ሦስትነታቸውን ሳይጠቀልለው ሦስትነታቸው አንድነታቸውን ሳይከፍለው በአንድነት በሦስትነት ሲሠለሱ ሲቀደሱ ሲመሰገኑ ይኖሩ ነበር:: ኋላ ግን ዓለምን እንፍጠር ብለው አሰቡ፤ አስበ ውም አልቀሩ:-

፩. **ዘአምጽአ ኩሎ በቃለ ኃይሉ እምኀበ ኢሀሎ ኀበ ሀሎ**
ይህን ዓለም እምኀበ አልቦ ኀበቦ/ካለመኖር ወደ መኖር/ አምጥ ተው ፈጠሩት::

፪. **እስመ ውእቱ ይቤ ወኮኑ ወውእቱ አዘዘ ወተፈጥሩ::**መዝ ፻፵፰፥፭-፮
እርሱ ብሏልና ሆኑም እርሱም አዝዟልና ተፈጠሩም::መዝ 148፥5-6::

ይህን ዓለም መፍጠራቸው ጉዳይ ኖሯቸው ጉዳይ ሊሞላላቸው አይደለም፤ አንድነታቸው ሦስትነታቸው ጌትነታቸው ባለጸግነታቸው እንዲታወቅ ብለው ነው እንጂ።

፫. እስመ አነ አምላክ ኢይርህብ ወኢይጸምዕ ወኢይደክም።
ኢሳ ፵፥፳፰-፴፩
የሥላሴ ባሕርይ የማይራብ የማይጠማ የማይደክም ነው።
ኢሳ 40፥28-31
የሰው ባሕርይ ግን የሚራብ የሚጠማ የሚደክም የሚሞት ነው። ሰው ልሰወር ባለ ጊዜ አጥር ቅጥር መጋረጃ ይፈልጋል ሥላሴ ግን እንሰወር ባሉ ጊዜ አጥር ቅጥር መጋረጃ አይፈልጉም፤የገዛ ባሕርያቸው ይሠውራቸዋል።

፬. ለሊከ ብከ ተከደንከ ወለሊከ አንጦላዕከ ስውር ብከ ኃይልከ ወክዱን ብከ ዕበይከ።
ገናናነተህ በአንተ የተሠወረ ነው፤ ኃይልህም በአንተ የተሠወረ ነው፤ አንተ ራስህን በራስህ ጋረድክ፤ አንተ ራስህን በራስህ ሠወርህ፡
ቅዳሴ ዮሐ/ ወልደ ነጐድጓድ

፭. እስመ እንዘ ኀቡዕ ክሡት አንተ ወታስተርኢ ለፍቁራኒከ።
የተሰወርህ ሳለህ ግልፅ ነህ፤ ለወዳጆችህ ትገለጣለህ። ሰው ልገለፅ ባለ ጊዜ ብርሃን መብራት ይፈልጋል፤ ሥላሴ ግን እንገለፅ ያሉ እንደሆን ብርሃን መብራት አይፈልጉም። የገዛ ባሕርያቸው ይገልፃቸዋል። ሰው በሕይወቱ ሞት በመንግሥቱ ኀልፈት አለበት፤ ሥላሴ ግን በሕይወታቸው ሞት በመንግሥታቸው ኀልፈት የለባቸውም።

፮. መንግሥቱ ዘለዓለም ወምኩናኑኒ ለትውልደ ትውልድመዝ ፻፵፭፥፲፫
መንግሥትህ የዘላለም መንግሥት ናት፤ ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው። መዝ 144፥13-14

፯. ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ። ሉቃስ ፩፥፴፫-፴፭
ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም። ሉቃስ 1፥33-34

፰. ዘእምቅድመ ዓለም መንግሥቱ ሰፋኒት። ትም/ኀቡዓት

ለዘለዓለም ጸንታ የምትኖር መንግሥት ያለችው፤ ትም/ኅቡዓት ሥላሴ ጉዳይ የለባቸውም ካሉ ይህን ዓለም ስለምን ፈጠሩት ያሉ እንደሆን ፍጡር ፈጣሪውን ያውቅ ዘንድ ረብሁ ጥቅሙ ነውና ስለዚህ ይህን ዓለም ፈጠሩት ፈጣሪያቸውንም ቢያውቁ የሚጠቀሙ ሰውና መላእክት ናቸው። የቀረውን ፍጥረት ለምን ፈጠሩት ያሉ እንደሆን እኛ ልንበላው ልንጠጣው ልንሠራበት ልንማርበት ነው።

፬. ስምዑኬ መድምማቲሁ ለእግዚአብሔር በእንቲአሁ ኩልክሙ ደቂቀ አዳም ያብጽሕ ለክሙ ነገረ ኩሎ ዘኰነ እምጥንቱ እስከ አመ ይትነፋሕ ቀርን በበመትልው፣ ወእመሰ ይትከሀል እምደ ለዎሙ ይስምዑ ዘንተ ኩሉ ፍጥረት ከመ ያእምሩ ኪነኖ ለኬን ያሆሙ እለ ይነቡኒ ወእለ ኢይነቡኒ ኅቡረ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም። መዝ፣ሠለስቱ ደቂቅ ፩፥፴፫-፴፬

እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረቶች ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። እርሱ የተመሠገነ ነው፤ ለዘላለሙም ከፍ ከፍ ያለ ነው። ሠልስቱ ደቂቅ 1፥33-34

እኛ የምንበላቸው የምንጠጣቸው የምንሠራባቸው ምንና ምን ናቸው ቢሉ አዝርዕቱን አትክልቱን ማሩን ወተቱን እንበላዋለን እንጠጣዋለን፤ ላሙን በጉን ፍየሉን አርደን እንበላዋለን፤ ፈረሱን በቅሎውን እንቀመጥበታለን፤ ዕዕዋቱን ሠረገላ መሸጋገሪያ ድልድይ አድርገን በባሕር እንዳንጠልቅ በገደል እንዳንወድቅ እንሻገርባቸዋለን። የምንማርባቸው ምንና ምን ናቸው ቢሉ የፀሐይ የእሳት የውኃ አንድነት ሦስትነት አላቸው በነዚህም እኛ የሥላሴን አንድነት ሦስትነት እናውቅባቸዋለን።

፭. ወኩሉ ተፈጥረ ለመፍቅደ ነባብያን ቦ እምኔሆሙ ለተምህሮ ወቦ እምኔሆሙ ለተገብሮ።

ከተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ የሰውን ፈቃድ የማይፈጽም የለም እንዳለ አረጋዊ መንፈሳዊ።

፲፭.ወለእመ ፈቀድከ ሰማዕተ አማናዌ ታእምር እምአፍአ ብከ መምህር ወመገሥጽ ዘይመርሀከ ኀበ ዝንቱ።ማር ይስ ም.1 አን.2
የእግዚአብሔርን ህልውና ልታውቅ ከወደድህ መምህርና ምስክር ሆኖ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ የሚመራህ ሥነፍጥረት አለልህ ማለት ነው፤ ማር ይስሐቅ፣ ም. 1 አንቀጽ 2

፲፮.ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትዓወቅ በፍጥረቱ በሐልዮ ወበአእምሮ ወከመዝ ይትአመር ኃይሉ ወመለኮቱ ዘለዓለም። ሮሜ ፩፥፳፩-፳፪
የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና። ሮሜ 1፥21-22
ሥላሴ ሰውንና መላእክትን ፈጥረው ምን ይጠቀማሉ ያሉ እንደ ሆነ ሥላሴስ ከምስጋና በቀር ከሰውና ከመላእክት የሚፈልጉት የለም።

፲፯.አኮ ዘብየ መፍቅድ ከመ እርከብ ፩ደ እምእሉ ወእሰአል መባሕተ ዘእንበለ ስብሐት ንጹሕ አነ እሴባሕ ሎሙ ውስተ መዛግ ብትየ ለዓለም።ኄኖክ ፲፯፥፲፯-፲፰
እሱም በሰማያት ያሉ መላእክትን ሁሉ በልዕልና ያሉ ቅዱሳንንም ሁሉ ይጠራል አመስግኑኝ ይላል የእግዚአብሔር ሠራዊት ኪሩቤል፣ ሱራፌል፣ አፍኒን፣ ዕውቀት ያላቸው መላእክትም ሁሉ ሥላሴ የፈጠሯቸው መላእክት ሁሉ ያመሰግናሉ። ኄኖክ 17፥16-18 እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን። መዝ ፻፶፥፮
እኛም ይህን የሥነ ፍጥረት መጽሐፍ አንብበን፣ ተረድተን፣ ፈጣሪያችንን አውቀን በየጊዜውና በየሰዓቱ እንድናመሰግነው እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

ታሪክ

ኤጲፋንዮስ ማለት ከግሪ/ምስጢር ገላጭ/ አርኃዊ/በር ከፋች/ አስተርእዮ /ጸጌቱን ሥነ ፍጥረት ያየና ለሌሎች ጽፎ ያሳየ/ ማለት ነው። በዓለ ኤጲፋንያን ዘውእቱ በዓለ አስተርእዮ እንዲለው። ኪ/ወልድ ክፍሌ ገጽ 250፣ ቅዳ ኤጲፋ. ትርጓሜ

ይህም ቅዱስ ቤቱ በቆጵሮስ ደሴት ከቤተ ገብርኤል ዐፀድ አቅራቢያ ነበር፤ ወላጆቹም በኦሪት ሕግ የጸኑ አይሁድ ነበሩ። እነርሱም ድሆች ነበሩ።

አባቱም ገባር ነበር። ይህን ቅዱስና አንዲት እኅቱን ሳያሳድጋቸው ሞተ። እርሱም አንድ ክፉ አህያ ነበረውና የተወላቸው እርሱን ነው። እናታቸውም የኦሪትን ትምህርት በማስተማር አሳደገቻቸው።
እናቱም አህያውን እንዲሸጠውና ከእርሱም እንዲያርፍ በሺያ ጩም እንዲረዳ ኤጲፋንዮስን መከረችው። ሊሸጠውም ከአህያው ጋር ሲጓዝ አንድ ክርስቲያን ጻድቅ ሰው ስሙ ፊላታዎስ የሚባል ተገናኘው፤ ያንን አህያ ሊገዛ ወዶ ከኤጲፋንዮስ ጋር ቁሞ ሲነ ጋገር፤ አህያው ኤጲፋንዮስን ኩላሊቱን ረገጠው። በምድር ላይ ወድቆ ለመሞት ደረሰ።

አባ ፊላታዎስም በመስቀል ምልክት ከኩላሊቱ ላይ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብሎ ሲያማትብ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ከሕማሙ ድኖ ተነሣ፤ ከቶ ምንም ሕማም እንዳልነካው ሆነ። ከዚህ በኋላ አባ ፊላታዎስ በዚያ ክፉ አህያ ላይ እንዲህ ብሎ ጮኸ፤ ስለ እኛ በተሰቀለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ትሞት ዘንድ ይገባል ቢለው ያ አህያ ወዲያውኑ ወድቆ ሞተ። ቅዱስ ኤጲፋንዮስም እነዚህን ሁለት ተአምራት አይቶ በስሙ ተአምራት የምታደርግበት የተሰቀለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው ብሎ አባ ፊላታዎስን ጠየቀው። እርሱም የክብር ባለቤት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም አይሁድ የሰቀሉት ነው አለው፤ ይህም ነገር በቅዱስ ኤጲፋንዮስ ልብ ተቀረፀ፤ በዚያም ወራት አንድ ባለጠጋ አይሁዳዊ ነበር፤ ኤጲፋንዮስንም ወሰደው የኦሪትንም ህግ በማስተማር አሳደገው። የሚሞትበትም ቀን በቀረበ ጊዜ ልጅ

ስላልነበረው ጥሪቱን ሁሉ አወረሰው የኦሪትንም ሕግ ትምህርት ሁሉ ተማረ።

በአንዲት ዕለትም ስሙ ሉክያኖስ ከሚባል መነኩሴ ጋር ተገናኘ እርሱም የተማረና የእግዚአብሔር ጸጋ ያደረበት ነበር፤ከእርሱም ጋር ተጓዘ። ሁለቱም በአንድነት ሲጓዙ ድኃ ሰው አገኛቸውና ምጽዋት እንዲሰጠው ያንን መነኩሴ ለመነው። ገንዘብ ስለሌለው የሚለብሰውን የጸጉር ዐጽፍ አውልቆ ለድኃው ሰጠው በዚያን ጊዜ ለዚያ መነኩሴ የብርሃን ልብስ ከሰማይ ሲወርድለት ኤጲፋንዮስ አየ።

ስለዚህ ድንቅ ተአምር አደነቀ ከመነኩሴው እግር በታች ሰግዶ አንተ ማነህ ሃይማኖትህስ ምንድን ነው ብሎ ጠየቀው፤ እርሱም ክርስቲያን እንደሆነ ነገረው።ደግሞም ክርስቲያን እንዲያደርገው ለመነው፤ መነኩሴውም ኤጲፋንዮስን ወስዶ ወደ አንድ ኤጲስ ቆጶስ አደረሰው። እርሱም የክርስትና ጥምቀትን አጥምቆ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ሥርዓቷንም ሁሉ አስተማረው። ኤጲፋንዮስም ኤጲስቆጶሱን እኔ መነኩሴ መሆን እፈልጋለሁ አለው። ኤጲስቆጶሱም ብዙ ገንዘብ እያለህ መነኩሴ መሆን አይገባም አለው።

ኤጲፋንዮስም ሐዶ እኅቱንም አምጥቶ የክርስትና ጥምቀትን አስጠመቃት ገንዘቡን ሁሉ ለድኆችና ለምስኪኖች ለባልቴቶችና ለሙት ልጆች ለአብያተ ክርስቲያናትም ሰጠ፤ መጻሕፍትንም ከእርሱ ገዛ። ከዚህ በኋላ መነኮሰ ለእርሱም ለእኅቱም ጥምቀት ምክንያት ወደሆነው ስሙ ሉክያኖስ ወደተባለው መነኩሴ ገዳም ገባ።

ዕድሜውም አሥራ ስድስት ዓመታት ነበረ። ከዚህ በኋላ ታላቁን አባ ኢላርዮስን አገኘው እርሱም በዕድሜው ጎልማሳ በገድልም ሽማግሌ ነበር። ቅዱስ ኤጲፋንዮስንም ተቀብሎ የምንኩስናን ሕግና የክርስትናን ሥርዓት አስተማረው የእግዚአብሔርም ጸጋ አድሮበት የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት የምንኩስናንም ሕግ በጥቂት ቀናት አጠና።

ከዚህ በኋላ ታላላቅ ተአምራቶችን በመሥራት ሙታንን እስከ ሚያስነሣቸው ሰይጣናትን ከሰዎች ላይ እስከሚያስወጣቸው ውኃ ከሌለበት ከደረቅ ቦታ ውኃን እስከሚያፈልቅ ያለ ጊዜውም ብዙ ዝናምን እስከ ማውረድ ደርሶ በገድልና በትሩፋት ፍጹም ሆነ የትሩፋቱም ወሬ አዋቂነቱም ተሰማ ከእርሱ ጋርም ሊከራከሩ ብዙ

አይሁድ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር። ስሕተታቸውንም እየገለጠ ላቸው በእርሱ ትምህርት አምነው የክርስትናን ጥምቀት አጠ መቃቸው እንዲሁም ጥበበኞች ዮናናውያን በትምህርቱ ተመለሱ ወደ ክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖትም ውስጥ ገቡ። መምህሩ ቅዱስ ኢላርዮስም በቆጵሮስ ሀገር ኤጲስቆጶስነት እንደሚሾም ትንቢት ተናገረለት። ወደዚያም ሒዶ ከታዘዘለት ቦታ እንዲኖር አዘዘው። እንዲህም አለው ኤጲስቆጶስነትም ሊሾሙህ በፈለጉህ ጊዜ እምቢ አትበል ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖአልና። ቅዱስ ኤጲፋንዮስም ወደ ቆጵሮስ ሒዶ መምህሩ ቅዱስ ኢላርዮስ በአዘዘው ቦታ ተቀመጠ። የቆጵሮስ ደሴት ኤጲስቆጶስም በአረፈ ሰሞን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ምግቡን ሊገዛ ወደ ገበያ ገባ። ከእርሱም ጋር ሁለት መነኮሳት ነበሩ። ደግሞም በዚያች ገዳም ጻድቅ የሆነ ሽማግሌ ኤጲስ ቆጶስ ነበረ ለእርሱም የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ነገረው።ወደ ገበያም ሒድ በእጁ ሁለት የወይን ዘለላ የያዘ መነኩሴ ታገኛለህ ከእርሱ ጋርም ሁለት መነኮሳት አሉ ስሙንም ጠይቀው፤ ስሜ ኤጲፋንዮስ ነው ይልሃል፤ እርሱን ያዝ በእጁ ያለውንም አስጥለህ ከአንተ ጋር አምጣው።

ያ ኤጲስቆጶስም የክብር ባለቤት ጌታችን እንደ አዘዘው አደረገ፤ ባመለከተውም ቦታ አግኝቶ ይዞት ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስዶ ዲቁና ሾመው። በሶስተኛውም ቀን ኤጲስቆጶስነት ሾመው። ከዚህ በኋላ ሽማግሌው ኤጲስቆጶስ የኤጲፋንዮስን ልብ ደስ ለማሰኘት ሽቶ ስለ ኤጲፋንዮስ ያየውን ራእይ ለሕዝቡ ገለጠላቸው። ስለ እርሱም ታላቅ ደስታ ሆነላቸው።

ይህ ቅዱስ፤ እግዚአብሔር በሚወድለት በሹመቱ ሁኖ በበጎ ሥራ ላይ ጸና። ጥቅም ያላቸውን ብዙ ድርሳኖችን ደርሷል ብዙ ተግሳጽ ጽፏል ከብዙዎቹ አንዱ ይህ አክሲማሮስ ነው።

የቅዱስ ኤጲፋንዮስ ጸሎቱና በረከቱ ከሁላችን ጋር ይሁን።
አሜን።
ስንክሳር ግንቦት ፲፯ ቀን

አክሲማሮስ ዘእሑድ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ

ንቀድም በረድኤተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ

መድኃኒትነ ጽሒፈ መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘቅዱስ

ኤጲፋንዮስ ኤጲስቆጶስ ዘደሴተ ቆጵሮስ ጸሎቱ ወበረከቱ

የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን::

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ በሚሆን

ድኅነት ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ

አጋዥነት የቆጵሮስ ኤጲስቆጶስ የቅዱስ ኤጲፋንዮስ

አክሲማሮስ መጽሐፍን ለመጻፍ እንጀምራለን፤

ጸሎቱና በረከቱ ከእኛ ጋር ይኑር ለዘላለሙ አሜን::

✠

ቅዳሜ ለእሑድ አጥቢያ በጊዜ ሠርክ ሰባት ፍጥረታትን ፈጠረ:: ምንና ምን ቢሉ አራቱ ባሕርያትን፣ ሰማያትን፣ መላእክትን፣ ጨለማን ፈጠረ፤ በባሕርዬ አራት ነገሮች አሉብኝ ሲል አራቱን ባሕርያት ፈጠረ፤ በባሕርዩስ ያሉ አራቱ ባሕርያት ምንና ምን ናቸው ቢሉ

ኃያልነት፣ መንጽሒነት/የሚያነፃ/፣

ፈታሒነት/ፈራጅ/፣ ባዕልነት/ባለጸጋነት/ ናቸው::

ኃያል ነኝ ሲል እሳትን ፈጠረ፤ እሳት ኃያል ነው፤ ውኃ ካልከለከለው ቀላውንም፣ ደጋውንም፣ እርጥቡንም፣ ደረቁንም ልብላ ቢል ይቻለዋል። እንደዚህም ሁሉ ጌታ ከሀሊነቱ ካልከለከለው ታላቁንም፣ ታናሹንም፣ክፉውንም፣መልካሙንም አንድ ጊዜ ላጥፋ ቢል ይቻለዋልና።

፭. እግዚአብሔር መኰንነ ጽድቅ ኃያል ወመስተአግሥ ወኢያ መጽእ መንሱተ ኩሎ አሚረ። መዝ ፺፥፲፩-፲፪

እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ ነው፤ ኃይለኛም ታጋሽም ነው፤ ሁልጊዜም አይቆጣም። መዝ 7፡11-12

ፈታሂ ነኝ ሲል ነፋስን ፈጠረ። ነፋስ ፈታሂ ነው፤ ገለባን ከፍሬ፣ፍሬን ከገለባ ይለያል፤ እንደዚህም ሁሉ ጌታ ጻድቃንን ከኃጥአን፣ ኃጥአንን ከጻድቃን ይለያል። ማቴ 3፡12-13

፮. የአምር እግዚአብሔር ገቢረ ፍትሕ። መዝ ፱፥፲፮

እግዚአብሔር ፍርድን በማድረግ የታወቀ ነው። መዝ 9፥16

መንጽሒ ነኝ ሲል ውኃን ፈጠረ፤ ውኃ መንጽሒ ነው፤ እድፍን ከአካል፣ አካልን ከእድፍ ይለያል። እንደዚህም ሁሉ ጌታ ነፍስን ከኃጢአት፣ ኃጢአትንም ከነፍስ ይለያል።

፫. ወኃበነ ማየ መንጽሔ ዚአነ ትም/ኅቡ/ እልመስሖአግያ፡ም ፪፥፯

ሀብተ ንጽህ ሀብተ ሕይወት የሚሆን የሚያድን ማየ ጥም ቀትን አደለን። በማየ ጥምቀት ከኃጢአት አነጻን። ባዕል ነኝ ሲል መሬትን ፈጠረ ወባቲ በረከት ኩሉ /ብዕል ከመሬት

ይገኛል/ ዳግመኛም ምድር ከሀሊት ናት፤ የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ችላ ትኖራለች::እንደዚህም ሁሉ ጌታ ሁሉን ችሎ ሁሉን ታግሶ ብዕሉን ለፍጥረቱ ሁሉ ሰጥቶት ይኖራል::

፬. ባዕል እግዚአብሔር ከሐሊ እግዚአብሔር:: ኢዮብ ፲፫÷፫-፬

ነገር ግን ሁሉን ለሚችል አምላክ መናገር እፈልጋለሁ::

ኢዮብ 13÷3-4

የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክን ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን?

ኢዮብ 11÷7-8

፭. ይቤ እፈቅድ እፍጥር ፬ተ ፍጥረታተ ከመ ይትዓወቅ ቅድምናየ፣ ወብሕትውናየ፣ ኃይልየ፣ ወክሂሎትየ::ኢሳ ፵፭÷፲፪-፲፫

በባሕርዩ ያሉትን አራቱን ባሕርያት ለማጠየቅ፤ አራቱን ባሕርያት ፈጠረ:: እኔ ምድርን ሠርቻለሁ፤ ሰውንም በእርሷ ላይ ፈጥሬአለሁ፤ እኔ በእጄ ሰማያትን ዘርግቻለሁ፤ ሠራዊታቸውንም ሁሉ አዝዣለሁ:: ኢሳ 45÷12-13

እነዚህንስ አራቱን ባሕርያት አንድ ጊዜ በምልዓት አድርጎ ፈጥሯቸዋልን? ቢሉ አይደለም::

፮. ስምዑኬ መንክራቲሁ ለእግዚአብሔር በቀዳሚ ፈጠረ ንስቲተ እሳተ፤ ወካዕበ ፈጠረ ንስቲተ ነፋሰ፤ ወሣልሰ ፈጠረ ንስቲተ ማየ፤ ወራብዓ ፈጠረ ንስቲተ መሬተ፤ እሉ እሙንቱ ፬ቱ ጠባይዓት:: በመጀመሪያ ጥቂት እሳት፣ ጥቂት ነፋስ፣ ጥቂት ውኃ፣ ጥቂት መሬት አድርጎ ፈጥሯቸዋል::

፮. ወአመ ይቤላ እግዚአብሔር ለይእቲ ንስቲት እሳት ብዙኂ ወተባዝኂ፣ ስፍሒ ወተሳፍሒ፣ በዝኃት ወተባዝኃት፣ ሰፍሐት ወተሳፍሐት፣ ወከዊና መጠነ ፈቀደ ላቲ ሕሊና እግዚአብሔር አኀዘት ርእሳ፤ ቆመት ወጸንዓት በክሂሎቱ።

ይህችንም ጥቂት እሳት ብዙ ተባዝ፤ ስፊ ተስፋፊ ብሎ በሀልዮ ቢያዝዛት በዛች ተባዛች፣ ሰፋት ተስፋፋች፣ ሕሊና እግዚአብሔር የመጠነላትን ደርሳ ቆመች፤ በከሃሊነቱ ጸናች እራሷን ቻለች።

፯. እኒትገት ወኢወሰከት፤ እምዘወሰነ ላቲ ኬንያሃ።
ይህችም ፈጣሪዋ ካዘዘላት ከመጠነላት አልፋ ምንም አልጨመረችም፤ አልጐደለችም።

፰. ወአመ ይቤላ እግዚአብሔር ለይእቲ ንስቲት ነፋስ ብዙኂ ወተባዝሒ፣ ስፍሒ ወተሳፍሒ፣ በዝኀት ወተባዝኀት፣ ሰፍሐት ወተሳፍሐት፣ ወከዊና መጠነ ፈቀደ ላቲ ሕሊና እግዚአብሔር አኀዘት ርእሳ፤ ቆመት ወጸንዓት በክሂሎቱ።

ይህችንም ጥቂት ነፋስ ብኽ ተባኽ ስፊ ተስፋፊ ብሎ በኀልዮ ቢያዝዛት በዛች ተባዛች ሰፋች ተስፋፋች ሕሊና እግዚአብሔር የመጠነላትን ደርሳ ቆመች ራሷን ያዘች። በከሃሊነቱ ጸናች።

፱. እኒትገት ወኢወሰከት እምዘወሰነ ላቲ ኬንያሃ።
ይህችም ፈጣሪዋ ከመጠነላት አልፋ ምንም አልጨመረችም አልጎደለችም።

፲፭.ወአመ ይቤላ እግዚአብሔር ለይእቲ ንስቲት ማይ ብዝሒ ወተባዝሒ፣ ስፍሒ ወተሳፍሒ፣ በዝሐት ወተባዝሐት፣ ሰፍሐት ወተሳፍሐት፣ ወከዊና መጠነ ፈቀደ ላቲ ሕሊና እግዚአብሔር አኀዘት ርዕሳ፤ ቆመት ወጸንዓት በክሂሎቱ።

ይህችንም ጥቂት ውኃ ብዙ ተባዢ፣ ስፊ ተስፋፊ ብሎ በሀልዮ ቢያዝዛት በዛች ተባዛች፣ ሰፋች ተስፋፋች፣ ሕሊና እግዚአብሔር የመጠነላትን ደርሳ ቆመች፤ ራሷን ያዘች በከሃሊነቱ ጸናች።

፲፮.ወአመ ይቤላ እግዚአብሔር ለይእቲ መሬት ብዝኂ ወተባዝሒ፣ ስፍሒ ወተሳፍሒ፣ በዝኀት ወተባዝኀት፣ ሰፍሐት ወተሳፍሐት፣ ወከዊና መጠነ ፈቀደ ላቲ ሕሊና እግዚአብሔር አኀዘት ርእሳ፤ ቆመት ወጸንዓት በክሂሎቱ።

ይህችንም ጥቂት መሬት ብኹ ተባኹ፣ ስፊ ተስፋፊ፣ ብሎ በሀልዮ ቢያዝዛት በዛች ተባዛች፣ ሰፋች ተስፋፋች፣ ሕሊና እግዚአብሔር የመጠነላትን ደርሳ ቆመች፤ ራሷንም ያዘች በከሃሊነቱ ጸናች።

፲፯.ኢነትገት ወኢወሰከት እምዘወሰነ ላቲ ኬንያሃ።

ይህችም ፈጣሪዋ ከመጠነላት አልፋ ምንም አልጨመረችም አልጐደለችም።

፲፰.ወዘንተ ኩሎ ፍጥረታተ ፈጠረ እምእሎንቱ ፬ቱ ባሕርያት ወአልቦ ዘይክል ኀልቆቶሙ ዘእንበለ ውእቱ ባሕቲቱ።

አራቱ ባሕርያት የሚባሉ እነዚህ ናቸው። ከፀሐይ በታች የተደረገውን ሥራ መርምሮ ያገኝ ዘንድ ለሰው እንዳይቻለው የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ አየሁ፤ ሰውም ሊፈልግ እጅግ ቢደክም መርምሮ አያገኘውም፤ ደግሞ ጠቢብ ሰው ይህን አወቅሁ ቢል እርሱ ያገኘው ዘንድ አይችልም። መክ 8÷17

አምስተኛ ጨለማን ፈጠረ፤ ስለምን ፈጠረው ቢሉ ጨለማ በዓይን አይታይም በእጅ አይዳሰስም እንደዚሁም ሁሉ ባሕርየ መለኮቱ አይመረመርም አይተረጎምም ሲል ጨለማን ፈጠረ።

፲፭.ወረሰየ ጽልመተ ምስዋሮ። መዝ ፻፭÷፲፩

መሠወሪያውን ጨለማ አደረገ። መዝ 17÷11

፲፮.በአማን ጽልመት ውእቱ ጎሚሠ መለኮቱ ለፈጣሬ ፍጡራን። የፍጡራንን ፈጣሪ የመለኮትነቱን ባሕርይ ፈልጌ ማወቅ በእውነትም ጥልቅ ነው። እነዚህ አራቱ ባሕርያት ከተፈጠሩ በኋላ የተፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ከእነዚህ ግብር እምግብር ፈጥሮታል።

፲፯.ወአልቦ ዘኢተፈጥረ ምንትኒ ዘእንበለ እምእሉ ፬ቱ ጠባይዓት

ከነዚህም ከአራቱ ባሕርያት ያልተፈጠረ አንድም ፍጥረት የለም። እነዚህም አራቱ ባሕርያት በፈቃደ እግዚአብሔር ይጣላሉ ይሸናነፋሉ፤ መሸናነፋቸውስ እንደምን ነው ቢሉ፦

፲፰.ዝኬውእቱ ትዕዛዙ ለእግዚአብሔር እሳት ይኄይሎ ለማይ፤ ወማይ ይኄይሎ ለእሳት፤ ነፋስ ይኄይሎ ለመሬት፤ ወመሬት

ይኄይሎ ለነፍስ፤ ወነፍስ ይኄይሎ ለማይ። ወይዘብጦ ከመ ከበሮ በማዕበል።

እሳት ውኃን ያፈላዋል፤ ውኃ እሳትን ያጠፋዋል፤ ንፋስ መሬትን ይበትነዋል ይዘረዝረዋል፤ መሬትም ነፋስን ይገድበዋል ይጋርደዋል፤ ነፋስ ውኃን ይመታዋል ያማታዋል እንደ ከበሮ ያስጮኸዋል።

እነዚህንም አራቱን ባሕርያት ለማስታረቅ ለማዛመድ ሦስት ሦስት ግብር ያላቸው እያደረገ ፈጥሯቸዋል፤ ኩፋሌ2÷17

ግብራቸውስ ምንና ምን ነው ቢሉ የእሳት ግብሩ ብሩህነት ሞቃትነት ደረቅነት ነው፤ የነፋስ ግብሩ ሞቃትነት ቀዝቃዛነት ጥቁርነት ነው፤ የውኃ ግብሩ ብሩህነት ርጥብነት ቀዝቃዛነት ነው፤የመሬት ግብሩ ደረቅነት ጥቁርነት ርጥብነት ነው።

እነዚህንስ ሲያስታርቃቸው ሲያዛምዳቸው እንደምነው ቢሉ እሳትን በሙቀቱ ከነፋስ ጋር፣ በብሩህነቱ ከውኃ ጋር፣ በደረቅነቱ ከመሬት ጋር፣ አዋህዶ አስማምቶ ትቶታል፤ ነፋስንም በሙቀቱ ከእሳት ጋር፣ በቀዝቃዛነቱ ከውኃ ጋር፣ በጥቁርነት ከመሬት ጋር፣ አዋህዶ አስማምቶ ትቶታል፤ ውኃንም በብሩህነቱ ከእሳት ጋር፣ በቀዝቃዛነቱ ከነፋስ ጋር፣ በርጥበቱ ከመሬት ጋር፣ አዋህዶ አስማምቶ ትቶታል። መሬትንም በደረቅነቱ ከእሳት ጋር፣ በጥቁርነቱ ከነፋስ ጋር፣ በርጥበቱ

ከውኃ ጋር፣ እንዲህ አድርጎ እነዚህን አራቱን ባሕርያት አዛምዶ አዋህዶ አስማምቶ ትቷቸዋል።

፲፱.ወገብረ እግዚአብሔር ፬ተ ዘመደ።

እግዚአብሔር አራቱ ባሕርያትን አዛመደ አዋሐደ ማለትም በየራሳቸው ሦስት ሦስት ግብር ያላቸው እያደረገ አስማምቶ ፈጠረ ማለት ነው። የአራቱ ባሕርያት የአራቱ ጠባይዓት ሥነ ፍጥረት አፈጣጠር ይህ ነው።



ክፍል ሁለት

፩. ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር በካልአይ ሰዓተ ሌሊት ብርሃነ ዓቢየ እምይእቲ እሳት ወገብረ መንበረ ስብሐቲሁ ነዋኅ ወም ጡቀ ወርኂበ። ኢሳ ፮፥፩-፪

እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር።ኢሳ6፥1-2 ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በሁለተኛው ሰዓተ ሌሊት ይህችን እሳት ከነውዕየቷ ከፍሎ አውጥቶ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ጐዝጉዞ ዘረጋ አነጠፈ።

፪. ሰማይ ውዱድ ዲበዘባናቲሆሙ ለኪሩቤል። ሕዝ ፩፥፳፭-፳፮

ይህም ኪሩቤል የሚሸከሙት ዙፋን ሰማይ ውዱድ ነው። ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ዘረጉ፣ እኔም እያየሁ ከምድር ከፍ

ከፍ አሉ፤ በወጡም ጊዜ መንኮራኩሮች በአጠገባቸው ነበሩ፤ በእግዚአብሔርም ቤት በምሥራቁ በር መግቢያ ቆሙ፤የእሥራኤልም አምላክ ክብር በላያቸው ላይ ነበር። ሕዝ 10÷19 -20

፫. ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር በሣልሳይ ሰዓተ ሌሊት ብርሃነ ዓቢየ እምይእቲ እሳት ወገብረ መንበረ ስብሐቲሁ ነዋኅ ወም ጥቅተ ወርህብተ ዘኢትትሌለይ በሕሊና እኁለ እመ ሕያው ወርኂብት ከመ ሐይመት።

ክዚህም በኋላ እግዚአብሔር በሦስተኛው ሰዓተ ሌሊት ሰማይ ውዱድን እንደ መሠረት አድርጎ መንበረ ስብሐትን በላይ ሠራ፤ የመንበረ ስብሐትስ አሠራሯ እንደምነው ቢሉ እንደ ቤተመቅደስ፤ እንደ ድንኳን አራት ማዕዘን አድርጎ መሥር ቷታል። ይህቺም ከምሥራቅ እስክ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ አትደርስም በመጠን ናት። ሰው የያዘውን ዓለም ታህላለች። በዚህችም ሥላሴ በፈቀዱ ጊዜ ለጻድቃን፣ ለሰማዕ ታት የሚታዩባት ናት።

፬. ወገብረ ላቲ ፮ተ መንጦላዕተ ዘነደ እሳት ወአያደ ዲቤሃ ፮ተ ቅጽራተ ዘነደ እሳት።

ይህችንም ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋረዳት፣ ሰባት የእሳት ቅጽር ቀጸራት። ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ገጽ 251

፭. ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር በራብዓይ ሰዓተ ሌሊት ብርሃነ ዓቢየ እም ይእቲ እሳት፤ ወገብረ አርያመ ወአሰርገዋ ቀለመ እሳት በውእቱ ብርሃን።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በአራተኛው ሰዓተ ሌሊት ይህችን እሳት ከነውዕየቷ ከፍሎ አውጥቶ ከብርሃን ብርሃን ጠምቆ አጥርቶ በመንበረ ስብሐት ላይ ጽርሐ አርያምን እንደ ጣራ እንደ ጠፈር ሠራ፤ ይህችንም በብርሃን ቀለም ሸልሟታል።

፮. አልቦ ሰማይ ዘይጼልል ላዕሌሃ እስመ መልዕልታዊት ወጽን ፋዊት ይእቲ፤ ወኩለንታሃ ብርሃን ፍጹም ዘኢይትነገር በልሳነ ኩሉ ፍጡር፤ ወኩሎሙ ብርሃናት አምሳለ ቀለምጺጸ እሳት በኀቤሃ።

ይህችም ከሰማይ ሁሉ በላይ ናት፤ ከዚያ በላይ ምንም ምን ሰማይ የለም።

፯. ወእምዝ አውጽአ ሎቱ ቅጽረ ከመ እንተ ጽንፍ፤ ወአልዓለ ቅጽሮ ለሰማይ፤ ወደመሮ ምስለ አርያሙ፤ ወቀፈሎ ወነተሞ በማኅተሙ በከመ ውእቱ አእመረ።

ከዚህም በኋላ የሰማይ ውዱድን ቅጽር ከጽርሐ አርያም ቅጽር ጋር አንድ አድርጎ እርሱ ባወቀው ማኅተም አትሞ ገጥሞ ትቶታል።

፰. አልቦ ዘየአምር መጠነ ወወሰነ ዘእንበለ ውእቱ ባሕቲቱ ዘየአምር ርእሰ መለኮቱ።

የጽርሐ አርያምን ዳሯን ድንበሯን መጨረሻዋን ከእግዚአብሔር በቀር የሚያውቀው የለም።

፱. ወእምዝ ነስአ እግዚአብሔር በ፮ቱ ሰዓተ ሌሊት ክፍላ ለይ እቲ ዓባይ እሳት ወገብረ ላቲ ፯ተ ቅጽረ ወ፯ተ መንጠላዕተ ዘነደ እሳት።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በአምስተኛው ሰዓተ ሌሊት ይህችን እሳት፤ ውዕየቷን ለይቶ ትቶ ብርሃኗን አውጥቶ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ጎዝጉዞ ዘርግቶ አንጥፎ ኢዮር የምትባለውን ሰማይ ሠራ፤ ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋረዳት፤ ሰባት የእሳት ቅጽር ቀጸራት።

፲. ወእምዝ አውጽአ ሎቱ ቅጽረ ከመ እንተ ጽንፍ፤ ወአልዓለ ቅጽሮ ለሰማይ፤ ወደመሮ ምስለ ቀዳሚት ሰማይ፤ ወቀፈሎ ውኀተሞ በማኅተሙ በከመ ውእቱ አእመረ።

ከዚህም በኋላ የኢዮርን ቅጽር፣ ከሰማይ ውዱድ ቅጽር ጋር አንድ አድርጎ እርሱ ባወቀው ማኅተም አትሞ ገጥሞ ትቶታል።

፲፩.ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር በ፯ቱ ሰዓተ ሌሊት ክፍላ ለይ እቲ ዓባይ እሳት ወገብረ ላቲ ፯ተ ቅጽራተ ወ፯ተ መንጠላዕተ ዘነደ እሳት።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በስድስተኛው ሰዓተ ሌሊት ይህችን እሳት፤ ውዕየቷን ለይቶ ትቶ፤ ብርሃኗን አውጥቶ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ጎዝጉዞ ዘርግቶ አንጥፎ ሁለተኛ ራማ የምትባል ሰማይ ሠራ፤ እርሷንም ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋረዳት፤ ሰባት የእሳት ቅጽር ቀጸራት።

፲፱.ወእምዝ አውጽአ ሎቱ ቅጽረ ከመ እንተ ጽንፍ፤ ወአልዓለ ቅጽሮ ለሰማይ፤ ወደመሮ ምስለ ዳግሚት ሰማይ፤ ወቀፈሎ ውኀተሞ በማኅተሙ በከመ ውእቱ አእመረ።
ከዚህም በኋላ የራማን ቅጽር፣ ከኢዮር ቅጽር ጋር አንድ አድርጎ እርሱ ባወቀው ማኅተም አትሞ ገጥሞ ትቶታል።

፳፫.ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር በ፮ቱ ሰዓተ ሌሊት ክፍላ ለይ እቲ ዓባይ እሳት ወገብረ ላቲ ፮ተ ቅጽራተ ወ፮ተ መንጠላዕተ ዘነደ እሳት።
ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በሰባተኛው ሰዓተ ሌሊት ይህችን እሳት ውዕየቷን ለይቶ ትቶ ብርሃኗን አውጥቶ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ጎዝጉዞ ዘርግቶ አንጥፎ ሶስተኛ ኤረር የምትባል ሰማይ ሠራ።

፳፬.ወእምዝ አውጽአ ሎቱ ቅጽረ ከመ እንተ ጽንፍ፤ ወአልዓለ ቅጽሮ ለሰማይ፤ ወደመሮ ምስለ ሣልሲት ሰማይ፤ ወቀፈሎ ውኀተሞ በማኅተሙ በከመ ውእቱ አእመረ።
ከዚህም በኋላ የኤረርን ቅጽር፣ ከራማ ቅጽር ጋር አንድ አድርጎ እርሱ ባወቀው ማኅተም አትሞ ገጥሞ ትቶታል።

፳፭.ኑኆን ወራህቦን ለቮቲሆን ዕሩይ ውእቱ፤ እምድር እስከ ሰማይ፣ እምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ እምሰሜን እስከ ደቡብ።
ሦስት ሰማያት፤ የመላእክት አጎበር የሚባሉ እነዚህ ናቸው፤ የእነዚህም ርዝመታቸው ወርዳቸው እኩል ነው።

፲፮.ወኢኃደገ ሎቶን አንቀጸ፣ ወኢስቈረተ፣ ወኢመስኮተ ዘያወጽእ አፍኣ እምቅጽረ ሰማይ እምላዕሉ እስከ ታሕቱ።

እነዚህንም ሰማያት ሲፈጥራቸው ወደ ውጭ የሚያስወጣ /የሚያሳይ/ አንቀጽ/ክፍተት/ የላቸውም፤ ከሰማይ ውዱድ ጀምሮ እስከ ጽርሐ አርያም ድረስ እርሱ ባወቀው ማኅተም አትሞ ገጥሞ ትቷቸዋል።

፲፯.ወገጻቲሆን እንተ ውስጥ ርቡዓት ከመ እንተ ደብተራ ዘመ ድምም ለተናግሮ።

እነዚህንም ሰማያት ሲሠራቸው ፊታቸውን ወደ ውስጥ አድርጎ እንደ ድንኳን ክብ እንደ ቤተ መቅደስ አራት ማዕዘን አድርጎ ፈጥሯቸዋል።

፲፰.ከመ ኢይፃዑ መላእክት እምቅጽር ኀበ አፍኣ ከመ ኢይር አዩ ወከመ ኢያእምሩ ምሥጢሮ እስመ ሥልጣኑ ለባሕቲቱ፤ ወጥበቢሁ ሎቱ።

ስለምን እግዚአብሔር እነዚህን ሰማያት ፈጠራቸው፤ ሲፈጥራቸውስ ወደ ውጭ የሚያስወጣ የሚያሳይ በር፣ መስኮት ሳያወጣላቸው ቀረ ቢሉ፤ ዛሬ ከውጭ የሚመጣ እንግዳ ወደ እልፍኝ ገብቶ ወደ ጓዳ አልፎ ዕቃ ማየት እንዳይገባው ከዚያ ቀጥሎ የሚፈጥራቸው መላእክትና ደቂቀ አዳም ምሥጢሩን እንዳያዩ እንዳያውቁ ነው።

፲፱.ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር በ፷ቱ ሰዓተ ሌሊት ክፍላ ለይእቲ ዓባይ እሳት ወአንበራ መልዕልተ ፫ቱ ሰማያት ወአዕረጋ ኀበ ፬ቱ ገበዋቲሃ ለሰማይ ዲበ ዘባና ለኢዮር።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በስምንተኛው ሰዓተ ሌሊት ይህችን እሳት ከነውዕየቷ ከፍሎ አውጥቶ ከሦስቱ ሰማያት በላይ ከሰማይ ውዱድ በታች አሰፈራት።

፳. ቀለመ መፍቅዱ ይእቲ ለፈጢር ወመልዓት እምጽንፈ ሰማይ እስከ ጽንፈ ምድር ወኮነት ዓለመ እሳት።

ይህቺም እሳት እንደ ደመና ተተርትራ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ደርሳ ረጋች ጸናች፤ የእሳት ሀገር ሆነች።

፳፩.ወዓዲ ገብረ እግዚአብሔር በ፱ቱ ሰዓተ ሌሊት መልዕልተ ይእቲ ዓባይ እሳት ታሕተ መንበሩ ዘትትናጸር ቅድሜሁ ኢየሩሳሌም ሰማያዊተ።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በዘጠነኛው ሰዓተ ሌሊት በዚች በተዘረጋች እሳት ላይ በመንበረ ስብሐት አንፃር ፊት ለፊት ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ሠራ።

፳፪.ወከመዝ ግብረታ ለአርያም ዘዓይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰምዓ ውስተ ሕሊና እጓለ እመሕያው ዘኢየዓርግ ብሔሮ ብሔረ ብርሃን ውእቱ ኑኃ ወግድማ መጠነ ዛቲ ዓለም፤ ወባቲ ፲ቱ ወ፪ቱ አናቅጽ ውሉጣነ ብርሃን። ፩ቆሮ ፪÷፱-፲

ነገር ግን ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበ እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተጻፈ 1ቆሮ 2÷9-10

ይህችም ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ አትደርስም፤ በመጠን ናት፤ አሥራ ሁለት ደጆች አሏት፤ የደጆቿም ብርሃናቸው ልዩ ልዩ ናቸው

፳፫.አዕማዲሃ ዘብርሃን ወጠፈራ ብርሃን ዘመጽሔት ወከመዝ ሕንጽት ይእቲ ከመ መርዓት ሥርጉት ለምታ::ራዕ ፳፩፥፱-፫

ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባሏ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግኢአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ እንዳለ ዮሐንስ ራዕ 21፥2-3::

ይህቺንም ኢየሩሳሌም ሰማያዊት የብርሃን አዕማድ ደግፏታል፤ የብርሃን ክዳን ከፍክፏታል፤

፳፬.ጠፈራ እሳት ወምርዋጸ ከዋክብት የዓውዱ ላዕሌሃ::

በዚችም በሦስት እረድፍ በከዋክብት አምሳል የብርሃን መርገፍ አዙሮባታል፤ የእሳት ቅጽር ቀጽሯታል፤ የእሳት መጋረጃ ጋርዷታል::

፳፭.ወጽሑፍ አስማቲሆሙ ለ፲፪ቱ ወፀቱ ሐዋርያት ወለ፲፪ቱ ወፀቱ ነገደ እሥራኤል በበ፲፪ቱ ወፀቱ አናቅጺሃ:: ራዕ ፳፩፥፲፩-፲፭

በዚህችም በጉበኖቿ የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም፣ በመድረኮቿ የአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ስም፣ በአዕማዶቿ የጻድቃን የሰማዕታት ስም ተጽፎባታል::ራዕ 21፥11-15::

፳፮.ኀበ ዓምደ ወርቅ ተጽሕፈ አስማቲሆሙ በሰማያት::

በመንግሥተ ሰማያት በወርቅ ዓምድ ላይ ስሞቻቸው ተጽፈ ዋል እንዳለ ቅዱስ ያሬድ::

፳፯.ወውስቴታ ታቦት ዘዶር ዘያበርህ በፀዳለ ሥሉስ ቅዱስ::

በዚችም የብርሃን ሳጥን ቁመቷን ወርዷን አስተካክሎ ቀርጾ አንጾ ከሥላሴ ፀዳል፤ ሥዕል ስሎ በውስጧ አኑሮባታል፤ ይህ ችንም ታቦት ዘዶር ብሎ ጠራት፤ የእግዝእትነ ማርያም አምሳል ናት። ቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ገጽ 265

፸፫.ስምዑኬ መድምማቲሁ በእንተ እግዚአብሔር ወእምዝ ነሢአ እምይእቲ ዓባይ እሳት ነበልባለ ወብርሃነ ፈጠረ መላእክተ መንፈሳውያነ።

ከዚህም ቀጥሎ እግዚአብሔር ሰማያትን ከፈጠረ በኋላ መላእክትን ፈጠራቸው።

፸፬.እመሰ ፈጠሮሙ ለመላእክት ቅድመ እምበሀሉ ተራዳዕናሁ አው አኃዝነ ሎቱ ለእግዚአብሔር አው ፈጠርነ ወዘንተ እኩየ ሕሊና ከመ ያብጥል እመላእክት ፈጠሮሙ ድኅረ ሰማያት ተፈጥራ።

ስለምን እግዚአብሔር ሰማያትን ከፈጠረ በኋላ መላእክትን ፈጠራቸው ቢሉ፤ በፊትስ ፈጥሯቸው ቢሆን እኛም አብረነው ፈጠርን፤ ያዝንለት ወይም ተራዳነው ባሉ ነበር፤ አንድም እርሱ ቢመሠርት እኛ ገነባን እርሱ ቢገነባ እኛ መሠረትን ባሉ ነበር። ይህም ይታወቅ ዘንድ ሳጥናኤል እንኳን በኋላ ተፈጥሮ ይህን ሁሉ የፈጠርሁ እኔ ነኝ ብሎ ተነሥቶ ነበር፤ እግዚአብሔርም ይህንን ክፉ፣ ከንቱ ሕሊና ከመላእክት ለማጥፋት፦

፸፬. ለትትፈጸምኬ አፉሃ ኩላ ዐመፃ።

ዓመፅ ሐሰት የምትናገር አንደበት እንድትዘጋ ሲል ሰማያትን ከፈጠረ በኋላ መላእክትን ፈጠረ። መላእክትንስ ከምን ከምን ፈጥሯቸዋል ቢሉ ከእሳትና ከነፋስ።

፴፩.ሰላም ለገጽከ እም ነፋስ ወነድ ዘተሥዕለ ምስለ ማይ ወመሬት ዘኢተሀወለ እንዳለ ደራሲ።

መሬትና ውኃ ያልተቀላቀለበት ከነፋስና ከእሳት ብቻ ለተፈጠረው ገጽታህ ሰላም እላለሁ።

፴፪.ኀድግሰ ባሕርየ ሥላሴ ለመላእክትኒ ኢይትዓወቅ ባሕርዮሙ ወበእንተ ነፍስኒ ከማሁ ይመስለኒ።

መላእክት ከእሳትና ከነፋስ ተፈጠሩ ካልን ስለምን መጻሕፍት የነፍስ ባሕርይዋ፣ የመላእክት ባሕርያቸው፣ የሥላሴ ባሕርይ አይታወቅም ይላሉ ቢሉ ይህንስ ቅዱስ ቄርሎስም እንዲህ ሲል ተናግሮታል። የነፍስ ባሕርይዋ፣ የመላእክት ባሕርያቸው የሥላሴ ባሕርይ አይታወቅም ማለት ግብራቸውን ለማጠየቅ ነው። እንደ እሳት የሚሞቁ፣ እንደ ነፋስ የሚረቁ ስለሆነ ከእሳትና ከነፋስ ተፈጠሩ ይሏል እንጂ ተፈጥሯቸውስ «እም ኀበ አልቦ» ነው።

፴፫.ሰላም ለተፈጥሮትከ በሌሊተ እሑድ ቀዲሙ እምኀበ ወኢምንት ግብር እንተ ኢይትአወቅ ባሕርየ ስሙ እንዳለ ደራሲ

የስሙ ትርጓሜ የማይመረመር ካለመኖር/ከኢምንት/ ግብር በቀዳማይ የእሑድ ሰዓተ ሌሊት ለተከናወነው ሥነተፈጥሮህ ሰላም እላለሁ።

፴፬.ለቀዳሚ ዖታ ስሞሙ አጋዕዝት ወሊቆሙ ሳጥናኤል ወአንበሮሙ በቀዳሚት ሰማይ።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በአሥረኛው ሰዓተ ሌሊት በኢዮር ያሉትን መላእክት አራት አለቃ አርባ ነገድ አድርጎ ከፈላቸው። ፊተኞችን አሥሩን ነገድ ስማቸውን አጋዕዝት አላቸው፤ የአጋዕዝትም አለቃቸው ሳጥናኤል ነው፤ ሳጥናኤ ልስ ማለት ምን ማለት ነው? ቢሉ ቅሩበ እግዚአብሔር፣ አጋዜ መንጦላዕት፣ አቅራቤ ስብሐት ማለት ነው፤ እነዚህ ንም ሲያሰፍራቸው ሲያዘጋጃቸው እንደ ላይ ቤት፣ እንደ ታች ቤት፣ እንደ ምድር ቤት አንድ ከተማ አድርጎ ከፍሎ በኢዮር በላይኛው ከተማ አሥሩን ነገድ አጋዕዝትን አሰፈራቸው።

፴፭.ወለዳግም ዖታ ፲ቱ ስሞሙ ኪሩቤል ካህናተ ቅዳሴ ወውዳሴ እምታሕተ ሐቃሆሙ ፩ዱ ወእምላዕለ ሐቃሆሙ ፬ቱ እለ ግሉፋን በአዕይንት። ሕዝ ፩÷፮-፯ ፣ ፲፰-፲፱

ሁለተኛም አሥሩን ነገድ ስማቸውን ኪሩቤል አላቸው፤ እነዚህም ካህናት ናቸው፤ የቀሳውስት አምሳል ናቸው፤ እነዚህንም ሲፈጥራቸው ከወገባቸው በታች አንድ ከወገባቸው በላይ አራት አድርጎ ፈጥሯቸዋል፤ እነዚህም አራት ገጽ ያላቸው ገጸ ሰብእ፣ ገጸ አንበሳ፣ ገጸ ንስር፣ ገጸ እንስሳ ይባላሉ፤ ከእግራቸው ጀምሮ እስከ ራሳቸው ድረስ በዓይን

የተሸለሙ ናቸው። እንደ ነምር ዝንጉርጉር አንድም እንደ መስታዎት ብሩህ ናቸው። ሕዝ 1÷6-7፣ 18-19

፴፮.ወሊቆሙ ገጸ ሰብእ፣ ወገጸ አንበሳ ዝውእቱ ኪሩብ ወአን በሮሙ በዳግሚት ሰማይ። ሕዝ ፲÷፩-፪

የእነዚህም አለቃቸው ገጸ ሰብእ፣ ገጸ አንበሳ ናቸው፤ ስማቸ ውም ኪሩቤል ይባላሉ፤ እነዚህንም በኢዮር በሁለተኛው ከተማ ከአለቆቻቸው ጋር አስፍሯቸዋል። ሕዝ 10÷1-2

፴፯.ወለሣልስ ዖታ ፲ቱ ስሞሙ ሱራፌል እለ፮ቱ ክነፊሆሙ አንቅዕተ ቅዳሴ ወውዳሴ። ኢሳ ፮÷፪-፬

ሦስተኛም አሥሩን ነገድ ስማቸውን ሱራፌል አላቸው፤ የዲ ያቆናት አምሳል ናቸው፤ እነዚህም ዛሬ ዲያቆናት ተንሥኡ ጸልዩ ብለው እንዲጀምሩ ሁሉ የምስጋና ነቅዕ፣ የምስጋና ምንጭ በነዚያ ይጀመራል፤ ሲፈጥራቸውም ስድስት ስድስት ክንፍ አድርጎ ፈጥሯቸዋል። ኢሳ 6÷2-4

፴፰.ወሊቆሙ ገጸ ንስር፣ ወገጸ እንስሳ ዝውእቱ ሱራፌ ወአንበ ሮሙ በሣልሲት ሰማይ።

የእነዚህም አለቃቸው ገጸ ንስር፣ ገጸ እንስሳ ነው ስሙም ሱራፌ ይባላል። እነዚህንም በኢዮር በሦስተኛው ከተማ አስ ፍሯቸዋል።

፴፱.ወለራብዕ ዖታ ፲ቱ ስሞሙ ኃይላት፤ ወሊቆሙ ሚካኤል፤ ወአንበሮሙ በራብዕ ሰማይ። ሄኖክ ፲÷፪-፮

ከዚህም በኋላ አራተኛ አሥሩን ነገድ ስማቸውን ኃይላት አላቸው፤ እነዚህም የሥላሴ ሰይፍ ጃግሮች ናቸው፤ ከአለቃቸው ጋር በኢዮር በአራተኛው ከተማ አስፍሯቸዋል። የእነዚህም አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው። ሄኖክ 10÷2-6

፴. ለቀዳሚ ዖታ ፲ቱ ስሞሙ አርባብ፤ ወሊቆሙ ገብርኤል መልአከ ታዕካሁ ለሕያው ዘለዓለም፤ ወአንበሮሙ በቀዳሚት ሰማይ። ሄኖክ ፲÷፯-፰

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በአሥረኛው ሰዓተ ሌሊት በራማ ያሉትን መላእክት ሦስት አለቃ ሠላሳ ነገድ አድርጎ ከፈላቸው፤ እነዚህንም ሲያዘጋጃቸው እንደላይ ቤት፣ እንደታች ቤት፣ እንደ ምድር ቤት ሦስት ከተማ አድርጎ ከፈላቸው። ፊተኞችንም አሥሩን ነገድ ስማቸውን አርባብ አላቸው፤ አለቃቸውም ቅዱስ ገብርኤል ነው። ሄኖክ 10÷7-8

፴፩.ወለዳግም ዖታ አሥርቱ ስሞሙ መናብርት፤ ወሊቆሙ ሩፋኤል እሉ እሙንቱ እለይቀልል ሩፀቶሙ እምነፋስ ወእለ ይፀውሩ ወላትወ መብረቅ ወኩናተ እሳት ዘይነድድ ወአንበሮሙ በዳግሚት ሰማይ። ሄኖክ ፲÷፮-፯

ሁለተኛም አሥሩን ነገድ ስማቸውን መናብርት አላቸው። አለቃቸውም ሩፋኤል ነው። እነዚህም የሥላሴ ጋሻ ጃግሮች ናቸው። የመብረቅ ጋሻ፣ የእሳት ጦር ይዘው ዘላለም እንደ ነፋስ ሲበሩ ይኖራሉ። እነዚህንም በራማ በሁለተኛው ከተማ አሥፍሯቸዋል። ሄኖክ 10÷6-7

፳፪.ወለሣልስ ዖታ ፲ቱ ስሞሙ ሥልጣናት ወሊቆሙ ሱርያል መልአክ ወአንበሮሙ በሣልስ ሰማይ፤ እሉ እሙንቱ እለ ይፀውሩ አብዋቀ ብርሃን ወያደምፁ ለመላእክት በጊዜ ቅዳሴሁ ወስባሔሁ ለእግዚአብሔር ለዘክሮቱ ይደሉ ሰጊድ።

ሦስተኛ አሥሩን ነገድ ሥልጣናት አላቸው። አለቃቸውም ሱርያል ይባላል። እነዚህም የሥላሴ ነጋሪት መኾዎች ናቸው፤ መላእክትን ለቅዳሴ ለስባሔ ሲያነቁ ሲያተጉ የሚኖሩ እነዚህ ናቸው። በራማ በሦስተኛው ከተማ አሥፍሯቸዋል።

፳፫.ለቀዳሚ ዖታ ፲ቱ ስሞሙ መኪንንት ወሊቆሙ ሰዳክያል እሉ እሙንቱ እለ ይነድፉ በሐፀ እሳት፤ ወነፋሰ ዘይሰጥቅ ዕብነ ወቀላያተ አድባረ ወአውግረ ወውኩላን ለዓቂበ እጓለ እመሕያው፤ ወያስተጋብኡ አዕዕምተ ሰብእ አመ ትንሣኤ ሙታን በዳግም ምጽአቱ፤ ወአንበሮሙ በቀዳሚት ሰማይ።

ማቴ ፳፬፥፴፩-፴፪

ፊተኞችንም አሥሩን ነገድ ስማቸውን መኪንንት አላቸው። አለቃቸው ሰዳክያል ይባላል። እነዚህም የሥላሴ ቀስተኞች ናቸው፤ ተራራ የሚንድ፣ ድንጋይ የሚሰነጥቅ የእሳት ፍላፃ የእሳት ቀስት ይዘው ሰውን ሁሉ ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሲጠብቁ የሚኖሩ መላእክት እነዚህ ናቸው። ጓላም በትንሣኤ ዘጉባኤ የሰውን ሁሉ አጥንት ሰብስበው ለትንሣኤ የሚያበቁ መላእክት እነዚህ ናቸው፤ እነዚህንም በኤረር በላይኛው ከተማ ከነአለቃቸው አስፍሯቸዋል።ማቴ24፥31-32

እነዚህም በኢዮር ያሉ መላእክት ከራማ መላእክት ጋር ሰባ ነገድ ሰባት አለቃ ናቸው። የእነዚህም የጭፍራ አለቆች የአንዱ ነገድ ከውሉደ አዳም ትክክል ነው።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በአሥራ አንደኛው ሰዓተ ሌሊት በኤረር ያሉትን መላእክት ሦስት አለቃ ሠላሳ ነገድ አድርጎ ከፈላቸው። እነዚህንም ሲያዘጋጃቸው እንደላይ ቤት ፣ እንደታች ቤት፣ እንደ ምድር ቤት ሦስት ከተማ አድርጎ ከፈላቸው።

፴፩.ወለዳግም ዖታ ፲ቱ ስሞሙ ሊቃናት ወሊቆሙ ሰላትያል እለ ይዜዓኑ በአፍራሰ እሳት ወድሩዓን በነደ እሳት ወውኩላን ለዓቂበ ኩሉ ዘሥጋ ወአንበሮሙ በዳግሚት ሰማይ።

ሁለተኛም አሥሩን ነገድ ስማቸውን ሊቃናት አላቸው። አለቃቸውም ሰላትያል ይባላል። እነዚህም የሥላሴ የፈረስ ባልደራስ ናቸው፤ በእሳት ፈረስ ተቀምጠው የእሳት ልብድ ተለብደው በከዋክብት አምሳል የብርሃን ሰላጢን ይዘው፤ በልባቸው የሚሳቡትን፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩትን፣ በክንፋቸው የሚበሩትን፣ በደመ ነፍስ ሕያዋን የሆኑትን ሁሉ ጠባቂ መልአክ ሆነው ሲጠብቁ የሚኖሩ መላእክት እነዚህ ናቸው፤ እነዚህንም ከነአለቃቸው በኤረር በሁለተ ኛው ከተማ አሥፍሯቸዋል።

፴፯.ወለሣልስ ዖታ ፲ቱ ስሞሙ መላእክት ወሊቆሙ አናንያል እሉ እሙንቱ እለ ይዌጽፉ በሞጻፍተ ነጐድጓድ አዕባነ እሳት ዘሐፂን፤ ወውኩላን ለዓቂበ ኩሉ ፍጥረት፤ ፀሐይ ወወር□ ወከዋክበት ዘእምታሕተ ሰማይ ወእምላዕለ ምድር ዘየአቅብዎ መላእክት ወአንበሮሙ በሣልስ ሰማይ። ኩፋሌ ፪፥፯-፰

ሦስተኛም አሥሩን ነገድ ስማቸውን መላእክት አላቸው፤ አለቃቸውም አናንያል ይባላል፤ እነዚህም እንደ ብረት የጸና የእሳት ነጐድጓድን ወደምድር የሚወነጭፉ፤ ፀሐይን፣ ጨረቃን፣ ከዋክብትን፣ አዝርዕትን፣ አትክልትን ዕፅዋትን ከምድር በላይ ከሰማይ በታች የተፈጠሩትን ሁሉ የሚጠብቁ ጠባቂ መላእክት እነዚህ ናቸው። እነዚህንም በኤረር በሦስተኛው ከተማ አስፍሯቸዋል። ኩፋሌ 2፥6-8

፴፰.እሉ እሙንቱ ፲ቱ ሊቃናት ወፀት ዖታ ነገደ መላእክት እለ አፀዎሙ ውስተ ፫ቱ ሰማያት ከመ ይንበሩ ውስቴቶን ለዓለመ ዓለም።

በሦስቱ ሰማያት ያሉ አሥር አለቃ መቶ ነገድ እነዚህ ናቸው

፴፱.ወአመ ፀውያሙ እግዚአብሔር ለመላእክቲሁ የዓርጉ ላዕለ እስከ ጽርሐ አርያም፤ ወእመኒ ለአኮሙ ይወርዱ ታሕተ እስከ በርባሮስ ጽልመት እንተ ይእቲ ጽንፈ ኩሉ ፍጥረት፤ ወአቲዎሙ ይገብኡ ውስተ መካናቲሆሙ ኀበ አልቦ ደዌ

ወኢሕማም፣ ኢሞት ወኢኀዘን ዘእንበለ ሰብሖቱ ለብሁተ ሕሉና ወሥሉጥ ላዕለ ምልክና ወምስፍና። ሄኖክ ፸÷፴፰-፵፪

እነዚህም መላእክት ፈጣሪያቸው ለተልዕኮ ካልጠራቸው ከየቦታቸው አይወጡም። ከየሥፍራቸው አይናወጡም። ፈጣሪያቸው ግን ለተልዕኮ በጠራቸው ጊዜ ወደላይ እስከ ጽርሐ አርያም ድረስ፤ ወደታች እስከ በርባሮስ ድረስ እንደ ዓይን ጥቅሻ ደርሰው መልእክታቸውን ፈጽመው ወደቦታቸው ይመለሳሉ። ሞት ሕማም ወደሌለበት ጥንተ ስፋራቸው ገብተው ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ ይኖራሉ። ከምስጋና በቀር ሌላ ተግባር ወይም ሥራ የለባቸውም። ሄኖክ 20÷38-42

፴፫.ይቤሎ ፩ዱ ለካልኡ ምንት አንተ ወምንት ኩነትከ ወይሰጠዎ ካልኡ ወይብሎ ጎድጎኒ አንሰ ኢየአምር ክዋኔየ ወኩነትየ ወይዴመሙ መላእክት በርዕየ አብያጺሆሙ።

ከዚህም በኋላ ሥላሴ መላእክትን ፈጥረው በሦስቱ ሰማያት አዘጋጅተው ትተው ድምጽ አጥፍተው ተሠወሯቸው።

መላእክትም ተፈጥሮአቸውን፣ ፈጣሪያቸውን፣ ተመራመሩ፤ ምን ብለው ተመራመሩ ቢሉ አንዱ አንዱን ዳሶ ሲያገኘው አንተ ምንድን ነህ ከየት መጣህ ይለዋል፤ እርሱም እኔስ አመጣጤ ከየት እንደሆነ አላውቅም፤ እያሉ እርስ በርሳቸው ይደነቃሉ።

፴፬.መኑ ፈጠረነ ወሚመ በበርዕስነኑ ተፈጠርነ።

ከዚህ በኋላ መላእክት ምንም እንኳ ተፈጥሮአቸውን ጨር ሰው ባያውቁም ፈጣሪያቸውን መረመሩ፤ ምን ብለው መረመሩ ቢሉ ማን ፈጠረን ወይስ እርስ በርሳችን ተፈጣ ጠ ርን ይሆን ብለው ተመራመሩ::

፱. አነ ፈጣሪሆሙ ለፈጡራን አነ ገባሪሆሙ ለግቡራን::

ከዚህም በኋላ መላእክት ተፈጥሮአቸውን ሲመራመሩ ሳጥና ኤል ዙፋኑ ሹመቱ ከሁሉ በላይ ነበረና አሻቅቦ ቢያይ ድምጽ አጣ፤ አቆልቁሎ ቢያደምጥ ግን መላእክት ፈጣሪያቸውን ሲመራመሩ ሰማቸው፤ እንዲህም አለ ይህ ሕዝብ ፈጣሪውን አጥቶ ተጨንቋል፤ እኔ ፈጠርኋችሁ ብዬ ፈጣሪነትን በእጄ ላድርግ ብሎ አሰበ፤ አስቦም አልቀረ እኔ ፈጠርኋችሁ ብሎ ተናገረ::

መላእክትም አሻቅበው ቢያዩት ሠይፉ እንደ ሠይፋቸው፣ ክንፉ እንደ ክንፋቸው ሆኖ አዩትና አንተማ እንደኛ ያለህ አይደለህምን እንደምን ፈጠርኋችሁ ትለናለህ አሉት፤ ሳጥና ኤልም እንዲህ አላቸው እናንት ምቀኞች ተመቅኝታችሁኝ ነው እንጂ ከእናንት በላይ ስታዩኝ እንደምን አልፈጠር ከንም ትሉኛላችሁ ይልቅስ እኔ ነኝና ፈጣሪያችሁ እመኑብኝ ስገዱልኝ አላቸው::

መላእክትም አዋቂዎች ናቸውና በቦታ ከፍታማ ከሆነ በኢ ዮር ያለኸው በራማ ያሉትን ብትፈጥር፤ በራማ ያለነው

በኤረር ያሉትን ባልፈጠርን ነበርን?፤ አንተስ እንደምን ፈጠርኋችሁ ትለናለህ አይሆንም አሉት፤ ሳጥናኤልም እናንት ምቀኞች ፈጣሪያችሁ ነኝና እመኑብኝ ስገዱልኝ አላቸው፤ መላእክትም ምቀኞች አይደሉምና በል ከሆነልህማ ፈጣሪ በፍጥረቱ ይታወቃልና እኛ እያየንህ እንግዳ ፍጥረት ፈጥረህ አሳየን አሉት፤ ሳጥናኤልም እፈጥራሁ ብሎ እጁን ወደ እሳት ቢሰድ ያች እሳት እንደ ወጥመድ እንቅ አድርጋ ይዛ እንደ ጅማት አኮማተረችው፤ አስጓጎረችው፤ ሳጥናኤልም መፍጠር አልተቻለውምና ሐሰቱ፣ ታወቀ::

፶፩.ዓመጻ ወጽአት እመዛግብቲሃ ወአቡሃ ለሐሰት::ሄኖክ ፲፩፥፭፣ ዮሐ ፰፥፵፬-፵፭

ሐሰት የተባለ ሁሉ ከሳጥናኤል ተገኝቷል «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፤ያባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ፤ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም፤ ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፤ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና::»

ዮሐ 8፥44-45 ፣ ሄኖክ 11፥5-6

፶፪.ወበዕለተ ፈጠሮሙ እግዚአብሔር ለመላእክቲሁ ተሐውሰ እመንበሩ ወአንበሰበሳ ለአርያሙ እስከ ያድለቀልቃ ፯ቱ ሰማያት::

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ይህ ሐሳዊ መስሐቲ ስቶ ሳያስታቸው ክዶ ሳያስክዳቸው ብሎ በዙፋኑ ላይ ሁኖ ቢንቀሳቀስ ሰባቱ ሰማያት ተንቀጠቀጡ ተነዋወጡ ለመናድ

ለመሰበር ለመፍረስ ደረሱ።

፱፫.ወደንገፁ መላእክት ወኮኑ ከመ አእዋፍ እለ ይነብሩ ዲበ ዕፀው፤ ወከመ አንህብት እለ ይሰፍሩ ዲበ ቀዕል፤ ሶበ ይትነሣእ ላዕሌሆሙ ነፋሰ ዓውሎ ጽኑዕ እስመ አኀዘሙ ፍርሃት ወድንጋፄ ሶበ ሰምዑ ድምፆ ለግርማ ሕይወት።

ከዚህም በኋላ ዛሬ በዛፍ ቅጠል ላይ የሰፈሩ አእዋፍና ንቦች ዓውሎ ነፋስ በተነሳባቸው ጊዜ እንዲጨነቁ፣ እንዲጠበቡ፣ ሁሉ መላእክትም መሸሻ መድረሻ አጡ።

፱፬.ንቁም በበ ህላዌነ እስክ ንረክቦ ለእግዚእነ ወአኀድአሙ መልአከ ሰላም ገብርኤል በቃሉ ለሠራዊተ መላእክት መን ፈሳውያን።

ከዚህም በኋላ ዛሬ መልካም ኅልማሳ ጦር ሲፈታ ድል ሲመታ አይቶ አይዞህ በያለህበት ቁም ብሎ ጦሩን እንዲያ ጸና፤ እንዲያረጋጋ ሁሉ ቅዱስ ገብርኤልም በመላእክት ሽብር ሲጸናባቸው ባየ ጊዜ አይዟችሁ ፈጣሪያችን ፈጥሮ አይጥለንምና እስክናገኘው፣ እስክናውቀው ድረስ በያለንበት እንቁም ብሎ አረጋጋቸው አጸናቸው፤ መላእክትም የቅዱስ ገብርኤልን ቃል ሰምተው በያሉበት ጸንተው ቆመዋል። ከዚህም በኋላ መላእክት በዚህ ዝንጋዔ፣ ድንጋፄ ሳሉ ሥላሴ ገና በአርምሞ ነበሩ። እስከዚህ ድረስ የአሥራ ሁለቱ ሰዓተ ሌሊት ሥነ ፍጥረት ነው።

ክፍል ሦስት

፩. ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ብርሃን ማዕከለ ጽልመት።

ዘፍ ፩፥፫–፬

እግዚአብሔር እሑድ ጠዋት ከቀኑ በመጀመሪያው ሰዓት ብርሃን ይሁን ብሎ ቢያዝዝ በምሥራቅ በኩል ብርሃን ተፈጠረ። ዘፍ 1፥3–4

፪. ወአስተርአዮሙ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወረሰዮሙ ለመላእክቲሁ ከመ አንቆቅሆ ውስተ ሕፅኑ።

ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ ሰማይን መላእክትን እንደ ዕንቁላል በክንፉ እቅፍ አድርጎ ያዛቸው።

፫. ወይቤሎሙ መንፈስ ቅዱስ ለመላእክቲሁ በግሩም ቃል ዝኩሉ ሰማይ ቤትየ ውእቱ እምአይቴ አንትሙ፤ ወምንት ኩነትክሙ፤ ወመኑ አብአክሙ ውስተ ቤትየ።

መንፈስ ቅዱስም መላእክትን እንደ ዕንቁላል በክንፉ እቅፍ አድርጎ ይዞ በግሩም ቃል ጠየቃቸው፤ምን ብሎ ጠየቃቸው ቢሉ ይህ ሁሉ ሰማይ የእኔ ነው፤ ከቤቴ ማን አገባችሁ ከወዴትስ መጣችሁ አላቸው።

፬. አ ግሩም እምግሩማን መኑ አንተ ዘወሰድከነ በድንጋፄ።

መላእክትም አቤቱ ከግሩማን በላይ ያለህ ግሩም አንተ ነህ፤ በዚህን ያህል ድንጋፄ ያራድኸን ያንቀጠቀጥኸን እናውቅህ ዘንድ አንተ ማን ነህ አሉት።

፷. አነ ሕይወቱ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ። ሄኖክ ፲፫÷፳፩-፳፪

መንፈስ ቅዱስም ሰማይን፣ እናንተንም ለፈጠረ ለአብ ሕይወቱ እኔ ነኝ አላቸው። ሄኖክ 13÷21-22

፷፩. ኦ እግዚእነ እስመ አንተ ተአምር ዘፈጠረነ ወአምጽአነ ወአብአነ ውስተ ቤትከ።

መላእክትም አቤቱ ጌታችን የፈጠረንንስ፣ ያመጣንንስ፣ ከቤትህስ ያገባንን አንተ ታውቃለህ እንጂ እኛ ምን እናውቃለን አሉት፤ ፈጣሪነቱ የባሕርዩ እንደሆነ አመኑለት መሰከሩለት።

፷፪. ወአመ አዘዛ እግዚአብሔር ለይእቲ ዓባይ እሳት ዘታውኢ ከመ ትለድ ብርሃነ፤ ወለደት ብርሃነ ወሰመዮ ለውእቱ ብርሃን መዓልተ። ዘፍ ፩÷፫-፮

ሳጥናኤልም መላእክትና መንፈስ ቅዱስ ሲነጋገሩ ቢሰማ አፈረ ደነገጠ፤ ወዲያውም ያ በምሥራቅ የተፈጠረ ብርሃን እንደ ምንጭ እየፈሰሰ እንደ ጎርፍ እየጎረፈ ደርሶ አጥለቀ ለቃቸው፣ ዋጣቸው፤ ያ ብርሃን ከወዴት ተገኝቷል ቢሉ ያቺ የተዘረጋች እሳትን ብርሃን ውለጂ ብሎ ቢያዝዛት ብርሃንን ወለደች፤ ያንንም ብርሃን በምሥራቅ በኩል መንገድ ሠራለት ስሙንም መዓልት አለው፤ መዓልትም ማለት ብርሃን ማለት ነው፤ አንድም ሥራኅ ማለት ነው። እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው፣ ጨለማውንም ሌሊት አለው ማታም ሆነ፣ ጠዋትም ሆነ። ዘፍ 1÷5-6

፰. ወተናጸሩ መላእክት እለ በታሕቲት ሰማይ ምስለ መላእክት ላዕላውያን፤ ወነጸሩ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ አንድ ክንፉን ወደ ላይ ወደ ጽርሐ አርያም በአብና በወልድ ላይ ጭኖ አንድ ክንፉን ወደታች ዘርግቶ ቢታያቸው የላይኞች መላእክት ከታች ኾቹ መላእክት ጋር ተያዩ፤ የማያቋርጠውን፤ የማይቆጠረውን፣ የማይሰፈረውን የሥላሴን ክብር አዩ።

፱. ወወድቁ መላእክት በገጸሙ ወተነግፉ ከመ ቆጽል በሰጊድ ወዝንቱ ብርሃን ኮኖሙ ጥበበ ወይቤሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባኦት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ። ኢሳ ፮÷፫-፬

ከዚህም በኋላ መላእክት በዚህ ብርሃን ምክንያት ጥበብ ተገልጾላቸው ሦስት ጊዜ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ብለው አመሰገኑ እንደ ቅጠል ረገፉ፤ እንደ ሻሽ ተነጠፉ፤ በግንባራቸውም ተደፉ፤ ስለምን መላእክት ሦስት ጊዜ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ብለው አመሰገኑ ቢሉ ጠላታቸው ሳጥናኤል ስላፈረላቸው መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ስለታያቸው ለይኩን ብርሃን ብሎ ቃሉን ስላሰማቸው ፤ስለዚህ ሦስት ጊዜ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው አመሰገኑት ፤አንድም መላእክት ሦስት ጊዜ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ማለታቸው የሦስትነታቸውን ነገር ሲናገሩ ነው። ኢሳ 6÷3-4

ያውስ ቢሆን ስለምን ሦስት ጊዜ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው አመሰገኑ እኩት ስቡህ ብለው አላመሰገኑም ቢሉ የሥላሴ ባሕርይ አይለወጥም ሲሉ ሦስት ጊዜ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው አመሰገኑ፤ እግዚአብሔር ማለታቸውም የአንድነታ ቸውን ነገር ሲናገሩ ነው፤ ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፤ ክቡር፣ ንጹህ፣ ጽኑ፣ ልዩ፣ ማለት ነው፤ ስለምን ሥላሴ ሰባት ፍጥረትን በአርምሞ፤ ስምንተኛ ብርሃንን በተናግሮ ፈጠሩ ቢሉ የሚሰማ ፍጥረት አልተፈጠረም ነበርና ሰባት ፍጥረትን በአርምሞ ፈጠሩ፡፡ ኋላ ግን ሰማዕያን መላእክት ተፈጥረው ነበርና ብርሃንን በተናግሮ ፈጠሩ፡፡

፲. ኢትትናገሩ ነገረ ፅሩዓ ዘአልቦ ባቁዕ ኢለነባቢሁ ወኢለሰ ማዒሁ ወኩሉ ዘይነብብ ንባበ ጽሩዓ ያገብኡ ሎቱ ቃለ በዕለተ ደይን፡፡ እንዳሉ ፫፻፡፡

ዛሬም ለነፍስ ለሥጋ የማይረባ የማይጠቅም ነገር አትናገሩ አትጫወቱ ብለው መጻሕፍት ተናግረዋል፡፡ ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት በሃይማኖተ አበው፡፡

፲፩.ወነበሩ መላእክት ድኑናኒሆሙ መጠነ አሐቲ ሰዓት በኀቤሁ ወበኀቤነሰ ፹ወ፫ቱ ዓመት ወ፬ቱ አውራኅ፡፡

ስለምን ሥላሴ ጨለማን በፊት ብርሃንን በኋላ ፈጠሩ ቢሉ ጨለማ የኦሪት አምሳል ሲሆን ብርሃን የወንጌል አምሳል ነው፤ አንድም ጨለማ ያለማወቅ አምሳል ሲሆን ብርሃን

የማወቅ አምሳል ነው፤ አንድም ጨለማ የገሃነመ እሳት አምሳል ሲሆን ብርሃን የመንግሥተ ሰማያት አምሳል ነውና ጨለማን በፊት ብርሃንን በኋላ ፈጠሩ፤ ከዚህም በኋላ መን ፈስ ቅዱስ በሁለተኛው ሰዓተ መዓልት ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ጠቅልሎ ወጣ።

በዚህቺም አንዲት ሰዓት መላእክት ከነግህ ጀምሮ እስክ ሠለስት እየሰገዱ ቆይተዋል፤ ኤጲፋንዮስም ይህች አንዲት ሰዓት በእግዚአብሔር ዘንድ አንዲት ሰዓት ናት፤ በእኛ ግን ሰማንያ ሦስት ዓመት ከአራት ወር ነው ብሏል።

፲፪.ወእምዝ ወረደ መንፈስ ቅዱስ ወቦአ ውስተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወቀደሰ ኩለንታሃ ወኩሎ ዘውስቴታ ይእቲኒ ሰብሐቶ ወአእመረቶ ለኬንያሃ።

መንፈስ ቅዱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወጥቶ ሁለን ተናዋን ቀባት፣ አነጻት፣ አከበራት፤ እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች፣ አመሰገነች።

፲፫.ወአቀመ እመላእክት ዘኃረየ ውስተ መንጠዋልዕ ዘመንበረ ስብሐት ቦዘይበርቅ፣ ወቦዘይነድድ፣ ወቦዘይነጉድ።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ከመላእክት እንደ መብረቅ የሚነጉዱ፣ እንደ እሳት የሚነዱትን መርጦ አቁሟቸዋል፤ ዙሪያውን ገጥሞ በመንበረ ስብሐት በመኃረጃው ውስጥ ክንፍ ለክንፍ አያይዞ ትታቸዋል።

፲፬.ወነሥአ እግዚአብሔር እምይእቲ እሳት ወገብረ አልባሰ መላእክቲሁ በመጠነ ጎልቆሙ፤ ወቅናታተ ዘብርሃን፣ ወመጽሔታተ ዘፀዳል፣ ወአክሊላተ ዘብርሃን፣ ዘእምጳዝዮን::

ዛሬ መኳንንቱ፣ መሳፍንቱ፣ ነገሥታቱ ለአዳራሻቸው፣ ለእልፍኛቸው ጠባቂ፣ ዘበኛ እንዲያቆሙ፣ እንዲያሰፍሩ ሁሉ፤ ለአርበኞች አሽከሮቻቸውም ግምጃውን፣ ቀሚሱን፣ መታጠቂያውን፣ የወርቁን ሾተል እንዲሠሩ እንዲያሰናዱ ሁሉ እግዚአብሔርም ለመላእክት የሚሸልማቸው ከዚያች ከተዘረጋች እሳት የብርሃን ግምጃ፣ የብርሃን ቀሚስ፣ የብር ሃን መታጠቂያ፣ የብርሃን አክሊል፣ የብርሃን ዘውድ አሰናዳ

፲፭.ወዘአዝፋረ አልባሲሆሙ በዕንቁ እሳት ሥርግው::
የዚህም የልብሳቸው ዘርፍ፣ የቀሚሳቸው ቁልፍ ከላይ እስከ ታች ድረስ እንደ ቀሚስ ቁልፍ በእሳት ዕንቁ የተከበበ ነው

፲፮.ወእምዝ ወረደ መንፈሰ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ ቀዳሚት ሰማይ ወቀደሰ ኩለንታሃ ወኩሎ ዘውስቴታ፤ ይእቲኒ ሰብሐቶ ወአእመረቶ ለኬንያሃ::
ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በሦስተኛው ሰዓተ መዓልት ወርዶ ኢዮርን ያለቆችን ዙፋን ሁለንተናዋን ቀባት፤አነጻት፣ አከበራት፣ እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች::

፲፯.ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለመላእክቲሁ ተንሥኡ እለ በአማን ሰጋድያን ለአምላክ፤ ነዋ በጽሐት ዕለተ ትፍሥሕ ትክሙ ከመ ዕቅባዕክሙ ለሕይወት ዘለዓለም::

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር መላእክትን እንዲህ አላቸው፤ እናንተ በእውነት ለፈጣሪያችሁ ያገለገላችሁ የሰገዳችሁ መላእክት የዘለዓለም ሕይወት የሚሆናችሁ ቅብዓት እቀባችሁ ዘንድ የደስታችሁ ቀን ደርሷልና ተነሱ አላቸው።

፲፮.ወተንሥኡ ፵ ዖታ መላእክት ወ፬ቱ ሊቃነ መላእክት ወቆሙ ቅድሜሁ ወይቤሉ ሰጊደሰ ሰገድነ ለከ ወባሕቱ ኢበጸሐነ ወኢርኢነ ጽንፈ ዕበይከ አ ሥለስ ቅዱስ።

ከዚህም በኋላ ሰማንያ ሦስት ዓመት ከአራት ወር እንደ ቅጠል ረግፈው እንደ ሻሽ ተነጥፈው ይኖሩ የነበሩ አራት አለቆች አርባ ነገደ መላእክት ተነሥተው በፊቱ ቆመው አቤቱ መስገድስ ሰገድንልህ፤ ነገር ግን የጌትነትህን ዳሩን ድንበሩን አልደረስንበትም፣ አላወቅነውም አሉት።

፲፯.ወቀደሰ ቅብዓ መዓዛሁ ዘታሐዩ ወታሌቡ ወበ፫ቱ ሰዓት ቀደሶሙ ለአጋዕዝት ወበ፬ቱ ሰዓት ቀደሶሙ ለኪሩቤል ወበ፭ቱ ሰዓት ቀደሶሙ ለሱራፌል ወበ፮ቱ ሰዓት ቀደሶሙ ለኃይላት ምስለ ሊቆሙ ሚካኤል።

ከዚህም በኋላ አእምሮ፣ ዕውቀት የሚሆናቸውን ቅብዓት አጣፍጦ፣ አከናውኖ በሦስተኛው ሰዓተ መዓልት አጋዕዝትን ቀባቸው፤ በአራተኛው ሰዓተ መዓልት ኪሩቤልን ቀባቸው፤ በአምስተኛው ሰዓተ መዓልት ሱራፌልን ቀባቸው፤ በስድስ ተኛው ሰዓተ መዓልት ኃይላትን ቀባቸው፣ አለቃቸውም

ሚካኤል ነው፤ ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ለመላእክት የብርሃን መጎናጸፊያ አጎናጸፋቸው፣ የብርሃን ዝናር አስታጠቃቸው፣ የብርሃን ዘንግ ማኅተሙ መስቀል የሆነ አስያዛቸው፣ የብርሃን ጫማ አጫማቸው፣ የብርሃን መነፀር አስያዛቸው፣ የብርሃን አክሊል፣ የብርሃን ዘውድ ደፋላቸው::

ስለምን እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ለመላእክት አደረገላቸው ቢሉ ፍጡሮች ናችሁ ሲል የብርሃን መጎናጸፊያ አጎናጸፋቸው፣ ተገዥዎች ናችሁ ሲል የብርሃን ዝናር አስታጠቃቸው፣ ሠራዊት ናችሁ ሲል የብርሃን ዘንግ አስያዛቸው፣ መውጣት መውረድ አለባችሁ ሲል የብርሃን ጫማ አደረገላቸው፤ እኔን ማየት በፈለጋችሁ ጊዜ ያለምክንያት ማየት አትችሉም ሲል የብርሃን መነፀር፣ የብርሃን መስታዎት አስያዛቸው፣ የፀጋ መንግሥት አንግሻችኋለሁ ሲል የብርሃን አክሊል የብርሃን ዘውድ ደፋላቸው::

፳. ወእምዝ ወረደ መንፈሰ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ ጸግሚ ት ሰማይ ወቀደሰ ኩለንታሃ ወኩሎ ዘውስቴታ፤ ይእቲኒ ሰብሐቶ ወአእመረቶ ለኬንያሃ::

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በሰባተኛው ሰዓተ መዓልት ወደ ራማ ወርዶ ያለቆችን ዙፋን ሁለንተናዋን ቀባት፤ አነጻት፣ አከበራት፣ እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች::

፳፩.ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለመላእክቲሁ ተንሥኡ እለ በአማን ሰጋድያን ለአምላክ፤ እስመ ነዋ በጽሐ ዕለተ ትፍሥሕትክሙ ከመ ዕቅባዕክሙ ለሕይወት ዘለዓለም::

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር እናንት በእውነት ለፈጣሪያ ችሁ ያገለገላችሁ የሰገዳችሁ መላእክት የዘለዓለም ሕይወት የሚሆናችሁን ቅብዓት ዕቀባችሁ ዘንድ የደስታችሁ ቀን ደርሷልና ተነሱ ብሎ አስነሣቸው::

፳፪.ወበ፯ቱ ሰዓት ቀደሶሙ ለአርባብ ወበ፰ቱ ሰዓት ቀደሶሙ ለመናብርት፣ ወበ፱ቱ ሰዓት ቀደሶሙ ለሥልጣናት ምስለ ሊቆሙ ሱርያል ::

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር አእምሮ፣ እውቀት፣ ፍቅር፣ ትህትና፣ የዋሃት፣ ትዕግሥት የሚሆናቸውን ቅብዓት አጣ ፍጦ በሰባተኛው ሰዓት አርባብን ቀባቸው፣ በስምንተኛው ሰዓት መናብርትን ቀባቸው፣ በዘጠነኛው ሰዓት ሥልጣና ትን ቀባቸው:: አለቃቸውም ሱርያል ነው::

፳፫.ወእምዝ ወረደ መንፈሰ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ ሣል ሲት ሰማይ ወቀደሰ ኩለንታሃ ወኩሎ ዘውስቴታ፤ ይእቲኒ ሰብሐቶ ወአእመረቶ ለኬንያሃ::

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በአሥረኛው ሰዓተ መዓልት ወደ ኤረር ወርዶ የአለቆችን ዙፋን ሁለንተናዋን ቀባት፤ አነጻት፣ አከበራት፣ እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች

፳፬.ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለመላእክቲሁ ተንሥኡ እለ በአማን ሰጋድያን ለአምላክ፤ ነዋ በጽሐት ሰዓተ ትፍሥሕ ትክሙ ከመ እቅባዕ ለክሙ ለሕይወት ዘለዓለም::

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር እናንት በእውነት ለፈጣሪያችሁ ያገለገላችሁ የሰገዳችሁ መላእክት የዘለዓለም ሕይወት የሚሆናችሁን ቅብዓት እቀባችሁ ዘንድ የደስታችሁ ቀን ደርሷልና ተነሱ ብሎ አስነሳቸው።

፷፭.ወተንሥኡ ፫ ሊቃናት ወ፴ ፪ታ ነገደ መላእክት፣ ወቆሙ ቅድሜሁ ወይቤሉ ሰጊደሰ ሰገድነ ለከ ወባሕቱ ኢበጻሕነ ወኢርኢነ ጽንፈ ዕበይከ አ ሥሉስ ቅዱስ።

ከዚህም በኋላ መላእክት ሰማንያ ሦስት ዓመት ከአራት ወር እንደ ቅጠል ረግፈው እንደ ሻሽ ተነጥፈው ይኖሩ የነበሩ ሦስት አለቆች ሠላሳ ነገደ መላእክት ተነሥተው በፊቱ ቆመው አቤቱ ጌታችን መስገድስ ሰገድንልህ፤ ነገር ግን የጌትነትህን ዳሩን ድንበሩን መጨረሻውን አላወቅነውም አልደረስንበትም አሉት።

፷፮.ወበ፲ቱ ሰዓት ቀደሶሙ ለመኳንንት ወበ፲ቱ ወ፩ ሰዓት ቀደሶሙ ለሊቃናት፣ ወበ፲ቱ ወ፪ቱ ሰዓት ቀደሶሙ ለመላእክት ምስለ ሊቆሙ አናንያል።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ለመላእክት አእምሮ፣ እውቀት ፣ፍቅር፣ ትህትና፣ የዋሃት፣ ትዕግሥት የሚሆናቸውን ቅብዓት አጣፍጦ፣ አከናውኖ በአሥረኛው ሰዓተ መዓልት መኳንንትን ቀባቸው፣ በአሥራ አንደኛው ሰዓት ሊቃናትን ቀባቸው፣ በአሥራ ሁለተኛው ሰዓት መላእክትን ቀባቸው። አለቃቸውም አናንያል ነው።

፷፯.ወእምዝ ዓርገ መንፈሰ እግዚአብሔር ወቦአ ውስተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወቀደሰ ኩለንታሃ ዓዕማዲሃኒ ወአናቅጺሃኒ ወኩሎ ዘውስቴታ፤ ይእቲኒ አእመረቶ ወሰብሐቶ ለኬንያሃ::

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአሥራ ሁለተኛው ሰዓት ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወጥቶ በውስጧ ያለውን ሁሉ ብርሃን ቀባት አነጻት፣ አከበራት፣ እርሷም ፈጣሪዋን አወቀች አመሰገነች::

፷፰.ነዋ ተፈጸመ ቅዳሴ ፯ቱ ሰማያት ወቅዳሴ ፲ቱ ሊቃናት፣ ወቅዳሴ ፻ት ጸታ ነገደ መላእክት በበነገዶሙ፤
የሰባቱ ሰማያት የአሥሩ ሊቃናት የመቶው ነገድ ቅብዓት እነሆ ተፈፀመ::



ክፍል አራት

፩. እምቅድመ ቅብዓትሰ ነበሩ መላእክት ከመሕፃናት በዝንጋዔ ወሰበ ተቀብዑ መልዓ ላዕሌሆሙ አእምሮ፣ ውኂሩት፣ ፍቅር ወትዕግሥት ትህትና ወየዋሃት::
ይህ ቅብዓት ምንድን ነው ቢሉ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ የቅብዓት ጣዕሙ ምሥጢሩ ምንድን ነው ቢሉ መላእክት ሳይቀቡ

አእምሮ፣ እውቀት እንደሌላቸው ሕፃናት ነበሩ፤ ከተቀቡ በኋላ ግን አእምሮ፣ ፍቅር፣ ትህትና፣ የዋሃት፣ ትዕግሥት አደረባቸው፤ ምስጋና እንደ ምንጭ እየፈሰሰ እንደ ጎርፍ እየጎረፈ ከአፋቸው የማይለይ ሆነ።

፪. ወሶበ ረከቡ መላእክት ስመ ስባሔሆሙ ለሥሉስ ቅዱስ በሰሌዳ መብረቅ ዘተጽሕፈ ተፈሥሑ ዓቢየ ፍሥሓ ወውዑ ይሴብሕዎ ለፈጣሪሆሙ እስከ ያድለቀልቃ ፯ቱ ሰማያት እምድምፀ ማኅሌቶሙ።

ከዚህም በኋላ መላእክት በተሰጣቸው እውቀት በየመነፀራቸው ቢያዩ፦

፫. ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ዋህድ ቅዱስ እግዚአብሔር ወልድ ዋህድ ቅዱስ መንፈስ እግዚአብሔር ዋህድ ዘፈጠረነ ወባረከነ፣ ወቀደሰነ፣ ወወህበነ ሕይወተ ዘለዓለም። የሚል ምስጋና ተጽፎ አገኙ።

ከዚህ በኋላ በአገኙት ምስጋና ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ቢያመሰግኑ ከድምጻቸው ምልዓት የተነሳ ሰባቱ ሰማያት ተነዋወጡ።

፬. ወእምዝ ወፅአ መንፈሰ እግዚአብሔር እም ኢየሩሳሌም ሰማያዊት እንዘ ይሴባሕ በአፈ መላእክቲሁ ወነበረ በመንበረ ስብሐቲሁ።

ከዚህም በኋላ ዛሬ ንጉሥ ከዘመተበት ሲመለስ በልልታ በደስታ እንዲቀበሉት ወደ ግንቡ እንዲያገቡት ሁሉ እግዚአብሔርም በአፈ መላእክት እየተመሰገነ ከኢየሩሳሌም

ሰማያዊት ወጥቶ መንበረ ስብሐት ገባ።

፩. ወነሥአ እግዚአብሔር እምሥራዊተ ኪሩቤል ፪ተ አርእስተ ዘውእቶሙ ገጸ ሰብእ፣ ወገጸ አንበሳ፤ ወዓዲ ነስአ እግዚአብሔር እምሥራዊተ ሱራፌል ፪ተ አርእስተ ዘውእቶሙ ገጸ ንስር፣ ወገጸ እንስሳ ወለክአሙ መልዕልተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት በማዕዘንተ መርህባ ለአርያም።

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ከኪሩቤል ሁለት ገጸ ሰብእ፣ ገጸ አንበሳን ከሱራፌል ሁለት ገጸ ንስር ገጸ እንስሳን አንስቶ ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት በላይ፤ ከሰማይ ውዱድ በታች አቆማቸው።

፪. ወሰፍሐ ዲበ ዘባናቲሆሙ ሰማየ ዘጎብሩ በረድ።

በእነዚህም ላይ ሰማይ ውዱድን እንደ መረሻት ጫነባቸው፣ በላይም ህብሩ በረድ የመሰለውን ዙፋን እንደ ኮረቻ ጫነባቸው። እነዚህንም በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን፣ በደቡብ በአራቱ ማዕዘን ጀርባቸውን ወደ ውስጥ፣ ፊታቸውን ወደ ውጭ፣ እያደረገ አቁሟቸዋል። ገጽ ለገጽ ሳይተያዩ ሥላሴ ወደአሰቡት መንገድ አንዱ በሄደበት ሦስቱ እየተከታተሉ ይሄዳሉ።

፫. ወገጸሙኒ ከመ ገጸ ፬ቱ ብሔር፤ ገጸ በገጽ ኢይትናጸሩ ጎበ አንጸረ ቀዳማዊ የሐውሩ። ሕዝ ፩፥፲፪-፲፫

እያንዳንዱም ወደፊት ቀጥ ብሎ ይሄድ ነበር፤ መንፈስም ወደሚሄድበት ይሄዱ ነበር ሲሄዱም አይገላመጡም ነበር።

ሕዝ 1፥12-13

«በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙሪያ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሏቸው አራት እንስሶች ነበሩ፤ ፊተኛውም እንስሳ አንበሳን ይመስላል፣ ሁለተኛውም እንስሳ ጥጃን ይመስላል፣ ሦስተኛውም እንስሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው፣ አራተኛውም እንስሳ የሚበረውን ንስር ይመስላል፤ አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሏቸው፤ በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፤ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው፣ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ፣ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም።» የዮሐ.ራዕ 4÷6-9

፷. ወአክናፊሆሙ እምድር እስከ ሰማይ ወአዕጋሪሆሙ እስከ በርባሮስ ጽልመት። ሕዝ ፩÷፳፯-፳፰

እነዚህም ከወገባቸው በላይ አሥራ ስድስት ከወገባቸው በታች አራት ናቸው፤ ክንፋቸውም ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ ይሆናል። ሕዝ 1÷27-28

፷፩. ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር እምሠራዊተ ሩፋኤል ፳ወ፩ተ ሊቃናተ ወአቀሞሙ አውደ መንበሩ። ሕዝ ፩÷፲፩-፲፪

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ከሠራዊተ ሩፋኤል ሀያአራት ሊቃናትን መርጦ በመንበረ ስብሐት በመጋረጃዋ ውስጥ ዙርያዋን ክንፍ ለክንፍ ገጥሞ አቁሟቸዋል። ሕዝ 1÷11-12

፷፪. ወሰመዮሙ ለእሙንቱ ካህናተ ሰማይ ወወሀቦሙ ማዕጠንታተ ዘእምወርቀ እሳት ወአክሊላተ ብርሃን ዘእምጳዝዮን

ወአብትረ ዘከተማሆን መስቀል ወአልበሶሙ አልባሰ ክህነት ዘጎብሩ መብረቅ። ዮሐ. ራዕ ፩፥፩-፭

እነዚህንም ስማቸውን ካህናተ ሰማይ አላቸው፤ የእሳት፣ የወርቅ ጽና አስያዛቸው፤ የብርሃን አክሊል ጻዝዮን ከሚባል የብርሃን ዘውድ ደፋላቸው፤ የብርሃን ዘንግ ማጎተሙ መስቀል የሆነ አስያዛቸው፤ የብርሃን ካባ ላንቃ ጎብሩ መብረቅ የመሰለ አለበሳቸው፤ «በዙፋኑ ዙሪያ ሀያአራት ዙፋኖች ነበሩ፤ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሀያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር፤» ዮሐ. ራዕ 4፥4-5

፲፩.ወይወጽእ እምውስተ ማዕጠንቶሙ መብረቅ ወነጎድጓድ ወፀዓዕ ዘመዓዛሁ ሠናይ። የዮሐ ራዕ፰፥፫-፭

እነዚህም በአንድ ላይ በዓጠኑ ጊዜ ከማዕጠንታቸው የሚወጣው ጢስ መልኩ መብረቅ፣ ድምጹ ነጎድጓድ፣ መዓዛው መልካም የሆነ ነው። «ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው፤ የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ» የዮሐ ራዕ 8፥3-5

፲፪.ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ለካህናቲሁ ጸሎተ ኩሎሙ ቅዱሳን ይኩን ውስተ ማዕጠንትክሙ ከመ ይዕርግ ኀቤየ።

የሚያጥኑትስ ምንድን ነው ቢሉ የጻድቃን ጸሎት፣ የሰማዕታት ገድል፣ የደጋግ ሰዎች ምግባር በእናንተ እየታጠነ ወደ እኔ ያርግ/ይድረስ/ ብሏቸዋል።

፲፫.ወይገለብቦ ለሰማይ ወለአርያሙ ጢሰ ዕጣኖሙ ዘመዓዛሁ ሠናይ ዛሬ በክረምት ተራራውን ኮረብታውን ጉም እንደሚሸፍነው እንደሚጋርደው ሁሉ ካህናተ ሰማይም የሚያጥኑት ማዕጠንት ጽርሐ አርያምን መንበረ ስብሐትን ይሸፍናል፣ ይጋርዳል።

፲፬.ወቦ ኪሩቤል ይቀውሙ በየማን በአምሳለ ቀሳውስት ወሱራፌል ይቀውሙ በጸጋም በአምሳለ ዲያቆናት ወድኅሬሆሙ ካህናተ ሰማይ።

የኪሩቤልና የካህናተ ሰማይ ያቋቋማቸው ማዕርግ እንደምን ነው ቢሉ ኪሩቤል በቀኝ እንደ ቀሳውስት፤ ሱራፌል በግራ እንደ ዲያቆናት ከፍ ብለው፤ ካህናተ ሰማይ ዝቅ ብለው ክንፍ ለክንፍ ገጥመው ቁመው ይኖራሉ።

፲፭.ወቦ እልፍ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት መብረቅ፣ወነጎድጓድ፣ ሠረገላሆሙኒ ምሉዓነ አዕይንት።

በዚህም በሰማይ ውዱድ ዙሪያ እልፍ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት መብረቅ፣ ነጎድጓድ፣ ሠረገላ እንደ መስታዎት ብሩህ የሆነ አለበት።

፲፮.ወሲሳዮሙ ለመላእክት ቅዳሴ ወስብሐት ወስቴሆሙ ፍቅረ መለኮት።

የመላእክት ምግባቸው ምንድን ነው ያሉ እንደሆን ዛሬ ግዙፋኑ ግዙፍ መብል/ምግብ/ በልተን ውኃ ጠጥተን እንድ

ዲያብሎስም ከዚህ ሁሉ ከሚወጣው ከሚወርደው በላህይና በደም ግባት በርዕይና በመልክ ከእንስሳት ከአራዊት አንቺን □ሚመስል የለም። አሁን እኔና አንቺ ባንድ ብንዋሀድ ብንተ ባበር □□ኔ ክፋት በአንቺ በጐነት ይሰወራል። የ□ኔ ጽሉምነት በአንቺ ብሩህነት ይጸትላል። □□ኾቴ □ሠሩ ምልክቱ አይገኝም አይታወቅምና ይዘሽኝ ሂጅ አላት።

፲፬.ወትቤሎ አርዌ ምድር □መሰ ይከውን ዘከመ ትቤ አንተ ንሑ ርኬ ወባሕቱ እስመ ዘተደመረ ምስለ ጽሉዕ ጽሉዓ ይከውን።

□ርሷም ጆህንን ከንቱ ውዳሴ ሲጸቀምሳት ጊዜ እንደ ተናገር ኸውስ ቢሆን መልካም ነው ነገር ግን ከጽሉም □□ለ □ሉም ከክፉ □□ለ □ፉ ነውና በአንተ □ፉት አዳም እኔን ጨምሮ ቢታላኝ ምን ይበጃኛል አለችው።

፲፭.□ጹቤላ □እቱኒ ሰማዕኪኑ ከመ ይጸልዓኒ ወሚመ በትሕዝብት እርሱም እኔን እንደጠላኝ ሰምተሻልን □ጹስ እንዲያው ጠርጥ ረሽ ነው አላት።

፲፮.ወትቤሎ አርዌ ምድር ለዲያብሎስ አልቦ ፍቅር ማዕከሌክሙ እስከ ለዓለም።
እርሷም መስማትስ አልሰማሁም ነገር ግን ጨለማነትህ ከበር ባሮስ ጆፊ ልማል ብርሃንና ጨለማ ይስማማሉን እንደዚህም ሁሉ አንተና አዳምም እስከ ምፅአት ድረስ ስምምነት የላች ሁም አለች□።

፲፯.ወይቤላ ዲያብሎስ ለአርዌ ምድር ዘንተሰ ዝንጋዔ ኀድጊ እስመ ፍቅረ ዚአነ ኢየኃልቅ እስከ ለዓለም።

ዲያብሎስም እንዲህ ያለውን ዝንጋዔ ተዪው አሁንስ ቢሆን እርሱ ቢጠላኝ እኔ ግድ አለኝን ያንችና የኔ ተዋህዶ ግን እስከ ምጽአት ድረስ አያልቅም አላትና ይልቅ ይህን ተራራ ስንወጣ አንች ትሸከሚኝ ወይስ እኔ ልሸከምሽ አላት?

፲፮.ወትቤሎ አርዌ ምድር ለዲያብሎስ አንተ ውረኒ አንሰ እደክም ወኢይክል ዕውርከ።

እርሷም እኔንስ ትከብደኛለህ አንተ ተሸከመኝ እንጂ አለችው

፲፱.ወሶበ በጽሑ ኀቡረ ማዕከለ ገነት ይቤላ ንዒ ውርኒ እስመ በጽሐ ሰዓተ ተባርዮ። መቅ. ወንጌል ገጽ 23።

ከዚህም በኋላ አርዌ ምድርና ዲያብሎስ በዚህ ስምምነት ተስማምተው ተማምለው የገነትን ተራራ ጨርሰው ከገነት መካከል ሲደርሱ ነዪ ፈንታሽን ተሸከሚኝ አላት።

፳. ወትቤሎ አርዌ ምድር ለዲያብሎስ ነዓ ተዐግን ላዕሌየ ወአመ አብሐኖ ቦአ እንተ ውስጠ አባላ።

እርሷም ፈንታዬስ ከደረሰ ና ልሸከምህ ነገር ግን እንዳትከ ብደኝ ቶሎ ብለህ ትወርድልኛለህ ብላ ብትፈቅድለት ዘሎ ከሜንቃዋ ላይ ተቀመጠ በሰውነቷ ሁሉ ተዋህደ።

፳፩.ወይቤላ ዲያብሎስ ለአርዌ ምድር እስመ ንኩ ለኪ አነ ከመ ነፍስ ወአንቲ ኩንኒ ከመ ሥጋ እምይእዜሰ ኢትትና ገሪ አንቲ ወአነ እትናገሮ ለመስፍነ ኩሉ ዓለም ቅድመ ዘይኤድሞ ወድኅረ ዘይሜርዎ እምገነት።

እርሱም እንግዲህ የአንቺ እና የእኔ ተዋህዶ እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ ይሁን ከዚያም ከመስፍኑ ስንደርስ ለጊዜው ደስ የሚያሰኘውን ኋላ ግን ከገነት ነቅሎ የሚጥለውን እኔ አናግረዋለሁ እንጂ አንች አትናገሪው አላት።

ክፍል አራት

፩. ወበዘከመዝ ስንዕ ቦኡ ዲያብሎስ ወአርዌ ምድር ውስተ ገነት ወእንዘ ይጌጥዕ አዳም ለጸሎት እስመ መላእክት ይጠቅዑ መጥቅዓ ወሶበ ሰምዓ አዳም ዘንተ ቃለ ምስለ አዕዋፍ ወአንስርት ወዕፀዊሃ ለገነት ያቄርቡ ስብሐተ ለፈጣሪሆሙ በበጊዜሁ።

እንዲህም በአለ ሁኔታ ተስማምተው እባብና ዲያብሎስ በጊዜ ቀትር /ስድስት ሰዓት/ ሲሆን አዳም ካለበት ደረሱ አዳምም ጊዜያት ደርሶበት ለጸሎት ሲቸኩል ነበር። ጸሎቱስ ምንድር ነው ቢሉ መላእክት ጊዜያት አይተው መጥቅዕ /ደወል/ ይደውላሉ ከዚህም በኋላ በገነት ያሉ አእዕዋፍ አንስርት ከአዳም ጋር ጸሎተ ማኅበር ያደርጉ ነበር።

፪. ወይቤሎ ዲያብሎስ ለአዳም በአፈ አርዌ ምድር ሰላም ለከ ኦ አዳም ፈጣሬ ኩሉ ዓለም ወንጉሠ ኩሉ ዓለም በሰማይ በላዕሉ ወበምድር በታሕቱ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌከ አነኒ መጻእኩ ኀቤከ ከመ ትስሚ ሊተ ስመ።

ከዚህም በኋላ ዲያብሎስ በዚህች እባብ ተጭ ሂዶ እንዴት አለህ አዳም የዚህ ሁሉ ጌታ የዚህ ሁሉ ንጉሥ ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ሌላ ፈጣሪ የለም። አንተ ነህ ፈጣሪ እኔም ይህን ሰምቼ እሰግድልህ አመሰግንህ ዘንድ መጥቻለሁ ብሎ የሐሰት ምስጋና አቀረበለት።

፫. ወይቤሎ አዳም ለዲያብሎስ ይኩን ስምከ ከይሲ ወባሕቱ አንስ ኢ ንኩ አምላከ አላ መሬታዊ አነ።

አዳምም ስምህ ከይሲ ይሁን አለው፤ ነገር ግን እኔ አምላክ አይደለሁም ሰማይን ምድርን እኔን መላእክትን የፈጠረ አምላክ አለ አለው።

ዲያብሎስም ባታውቅበት ነው እንጂ አምላክነትስ ተሰጥቶህ ነበር። ለመሆኑ ባልንጀራ አለህን ወይስ ብቻህን ፈጥሮሃል? አለው። አዳምም ሔዋን አለችኝ እንጂ አለው።

፬. ወይቤሎ ዲያብሎስ ለአዳም አይቴ ሀለወት ሔዋን ንግሥተ ኩሉ ዓለም ከመ እትአምኃ።

ዲያብሎስም አዳምን የዓለም ሁሉ ንግሥት ሔዋን ከወዴት አለች? አሳየኝና ተገናኝቻት ልሂድ አለው። አዳምም እርሷስ

ንግሥትም አይደለች የእግዚአብሔር ባሪያ ናት እንጂ፤ ያቻት ከዕፀ ሕይወት ሥር አለችልህ አለው።

፮. ወይቤላ ዲያብሎስ በአፈ ከይሲ ሰላም ለኪ ኦ ሔዋን ንግሥተ ኩሉ ዓለም ፈጣሪተ ኩሉ ዓለም ብእሲተ ንጉሠ ኩሉ ዓለም።

ዲያብሎስም በአፈ ከይሲ ተጭ ሄዶ እንዴት አለሽ ሔዋን የሁሉ እመቤት የሁሉ ንግሥት የሁሉ ንጉሥ ሚስት እኔም ይህን ሰምቼ እሰግድልሽ አመሰንግሽ ዘንድ መጣሁ ብሎ ሐሰት ምስጋና ከንቱ ውዳሴ ደረሰላት/አቀረበላት/።

እርሷም ነገሩ ደስ ብሏት ሳለ ሴቶች ውዳሴ ከንቱ ይወዳሉና እኔስ ንግሥትም አይደለሁ ሰማይን፣ ምድርን፣ እኛን፣ መላእክትን የፈጠረ አምላክ አለ አለችው። ዲያስሎስም ባታውቁ በት ነው እንጂ አምላክነትስ ተሰጥቷችሁ ነበር። ነገር ግን ከዚህ ዓለም ምን ሰጥቷችኋል? ምንስ ነስቷችኋል? ኑሯች ሁስ እንዴት ነው? አላት።

፯. ወትቤሎ ሔዋን ለዲያብሎስ ንሕነሰ ሀሎነ በትፍሥሕት ወበተድላ ወኢከልእነ ምንትኒ ዘእንበለ አሐቲ ዕፅ እንተ ሀለወት ውስተ ማዕከለ ገነት። ዘፍ ፫÷፩-፫

እርሷም ኑሯችንስ በተድላ በደስታ ነው። ከምድር በላይ ከሰማይ በታች የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ብሉ ጠጡ ግዙ ንዱ እዘዙ ብሎ ሰጥቶናል ከአንዲት ዕፅ በቀር የከለከለን ነገር የለም አለችው። ዘፍ 3÷1-3

ዲያብሎስም ያችን ዕፀ በለስ ብትበሉ ምን ትሆናላችሁ ብሏችኋል አላት። እርሷም ይህችን ቁዕለ በለስ ብትበሏት የሞት ሞት ትሞታላችሁ ከእኔ ትለያላችሁ ገሃነመ እሳት ትወርዳላችሁ ብሎናልና አንነካትም አለችው። ዘፍ 3÷3-4

፭. ወይቤላ ዲያብሎስ ለሔዋን መኑ ዘሞተ በእንተ መብልዕ መብልዕስ ኢይቀትል አላ ዘንተሰ ዘይቤ ከመ ኢትኩኑ አማልክተ ወኢታእምሩ ሠናየ ወእኩየ ወኢትፍጥሩ ካልአ ፍጥረተ። ዘፍ ፫÷፬-፭

መብልስ ያድናል እንጂ አይገድልም አንች ሞኝ መብል ማንን ገድሎ ያውቃል። ነገር ግን ከእኔ የተሻለ እንግዳ ፍጥረት ፈጥረው ፍጥረቴን ሁሉ ያስንቁታል ብሎ ተመቅኝታችሁ ነው እንጂ እውነት መብልስ የሚገድል ሁ አይደለም አላት። ዘፍ 3÷4-7

ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለዓይንም እንደሚ ያስጐመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች። ዘፍ 3÷6-7

፮. ወይቤላ ዲያብሎስ ለሔዋን ኢትብልዒ ባሕቲተኪ እምዛቲ ቁጽል አላ ሰዲዮ ኀበ ምትኪ ውእቱ ያፍዕምኪ ወአንቲኒ አፍዕሚዮ ሎቱ። ዐቂ ከመ ኢይቅድምኪ ወአንቲኒ ኢትቅድሚዮ።

እርሷም አማልክትማ ከሆንን አሁኑ አንበላውምን አለችው። እርሱም በልቡናዋ እንደበላችው አውቆ ስትበዱውም ለብቻሽ

አትብዱ። ለቅመሽ ይዘሽ ሄደሽ በቀኝ እጅሽ ለእርሱ በግራ እጅሽ ለአንቺ በአንድ ላይ ጉረሱት። እርሱም ቀድሞሽ ቢበላ እርሱ አምላክ ይሆናል አንቺ ይቀርብሻል፤ አንቺም ቀድመሽ ብትበዱ አንቺ አምላክ ትሆኛለሽ እርሱ ይቀርበታልና በአንድ ላይ ጉረሱት አላት።

፱. ወሶበ ዓለው ትእዛዘ እግዚአብሔር አምላክ ኀደጎሙ ጸጋ እግዚአብሔር ወተሰልበ እምኔሆሙ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ። ዘፍ ፫÷፭-፯

እርሷም ለቅማ ይዛ ሂዳ በቀኝ እጇ ለእርሱ በግራ እጇ ለእራሷ አንድ ጊዜ ጉርሰው አላምጠው ሳይውጡት እንደ ክረምት ነጐድጓድ ተንጓጉቶ ጸጋቸው ተገፈፈ ክብራቸው አለፈ። በአርባና በሰማንያ ቀን የተቀበሉት ልጅነት ተነሣ ቸው ዕርቃን ለዕርቃን ተያዩ። ዘፍ 3÷7-8

፲. ወይቤ አዳም ምንተ ገበርክኒ አብእሲቶ ወይ ለነ አሌ ለነ ወረከበነ ወይሌ ዘለዓለም።

አዳምም ጉሮሮውን እንቅ አድርጐ ይ ወዬው አንች ሴት ምን አበላሽኝ ይሆን እንዴት ለዘላለም የማያልቅ መከራ አገኘኝ እያለ ምርር ብሎ አለቀሰ። አዳምም ጉሮሮውን እንቅ አድርጐ የያዘው ዛሬ በወንድ ልጅ ላይ ምልክት ሆ ቀርቷል።

፲፩.ወነሥአ አዳም እምዕፀ ገነት ከመ ይዝብጣ ለሔዋን ወደገና ወተመይጠ ምዕረ።

አዳምም ተቆጥቶ አልቀረም ከገነት እንጨት አንስቶ እማ ታለሁ ብሎ ሲል ዘልላ ከአትክልት ውስጥ ተሠወረች /ተሸሸገች/። አዳምም ተመለሰ እንጂ ተከታትሎ ገብቶ አልመታትም። ይህም ልማድ ሆ ቀርቷል። ዛሬ ሴቶች ከባሎቻቸው ተጣልተው ወደማጀት በገቡ ጊዜ በዚያ ልማድ ተመልሶ ይወጣል እንጂ ተከታትሎ ገብቶ አይማ ታም። እምቢ ብሎ ገብቶ ቢመታት ግን ይፈረድበታል እንጂ አይፈረድለትም።

አዳምም ሔዋንን መትቷት ቢሆን ሔዋንም በአበሳዬ ነው ብላ ተቀብላው ቢሆን ሁለቱም ንስሐቸው ይቀልላቸው ነበር። ለዚህም ምሳሌ ያስረዳል። እንደምን ቢሉ ሙሴ እስራኤልን ከግብጽ አውጥቶ በምድረ በዳ አሰፈራቸው እርሱም ወደ ደብረ ሲና ወጣ። እስራኤል ግን አሮንን፤ ሙሴን ምን እንዳገኘው አናውቅም ጠፋ አሁንም አንተ አማልእክት ሥራልን አሉት። አሮንም እስራኤል ክፉ ሰዎች ናቸውና በድንጋይ ወግረው ይገድሉኛል ብሎ እሽ ያላችሁን ብር ወርቅ ሰብስባችሁ አምጡልኝ ቢላቸው እስራኤል ወትሮ ገንዘብ ወዳጆች የነበሩት ሰይጣን አትግቷ ቸው ብር፣ ወርቅ፣ መሣሪያቸውን ሁሉ ሰብስበው አመጡ ለት። አሮንም እሳት ከበላው እኔ ምን ላድርግ እላቸዋለሁ ብሎ እሳት አንድዶ በእሳት ላይ ጣለው።

ያን ጊዜም በወይፈን በጊደር አምሳል ቀንዳቸው የወርቅና የብር ጅራታቸው የሐር አምሳል ያላቸውን ሁለት ዕንላተ ጣዖት /የጥጃ ምስል/ ሰይጣን አቆመላቸው፤ እስራኤልም ወንዶች ለወንዱ ጣዖት ሴቶቹ ለሴቲቱ ጣዖት ይሰግዱ ጀመር። ጌታም ሙሴ ሙሴ ብሎ ጠርቶ እስራኤል ወገ ችህ በድለውኛልና መቅሠፍት አምጥቼ ልፍጃቸው አለው። ሙሴም ብእሴ እግዚአብሔር /የእግዚአብሔር ሰው/ ነውና አቤቱ ጌታዬ እስራኤልንማ አንተ ካጠፋሃቸው ማን ያተር ፋቸዋል። አሁንም እነን ላከኝና በደለኛውን ልቅጣ አለው። ጌታም ከቀጣህማ አይህ የለምን ብሎ ሁለቱን ጽላቶች ሰጥቶ ሰደደው። ሙሴም ቢደርስ እስራኤል ፍሪዳ አርደው ጠጅ ጥለው ለጣዖት ሲሰግዱ አገኛቸው። ዘጸ 32÷1-20

ሙሴም ተቆጥቶ በሁለቱ ጽላቶች ሁለቱን ጣዖታት መታቸው ጽላቶቹም ጣዖቶቹም ተሰበሩ። ሙሴም ይህን ነገር የጀመረውስ ያደረገውስ ማን ነው አለ? እስራኤልም ሐሰተኞች ናቸውና እኛስ አንዳችም ነገር አላደረግንም አሉት። ሙሴም አዋጅ ነግሮ ሴቶችን፣ ወንዶችን ሰብስቦ ያን ጣዖት ስልቅ አድርጉ አሰልቆ በጥብሙ በአድራጊ ያድርገው ብሎ ቢረጨው ፍቅረ ጣዖት ያደረባቸው ሰዎች በከንፈራቸው የወርቅ ቀሰም እየተቀረጸባቸው ተገኘ። ሙሴም ያን ጊዜ ለፈጣሪው ቀንቶ ከእስራኤል ሦስት ሽህ በሰይፍ ቀጣ። ዘጸ 32÷28-29

፻፸፰

፲፪.ሶበሰ ዘበጣ አዳም ለሔዋን እም ሙ ንስሐ ለ፪ኤሆሙ በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አመ ቀተሎሙ ለ፴፻ት እለ ስብ ላህም አፍቀሩ እስከ ይቤሎ አስተንፈስካ ለልብየ። ዘጸ ፴፪÷፳፰-፴።

ጌታም ሙሴን ልቤን አበረድሐት አስተነፈስሐት አሁንም የቀሩትን ምሬልሃለሁ ብሎ የአሰበውን መቅሠፍት መልሶለ ታል። ዘጸ 32÷28-30። እንደዚህም ሁሉ አዳም ሔዋንን መትቷት ቢሆን ሔዋንም በአበሳዬ ነው ብላ ብትቀበለው ንስሐቸው ይቀልላቸው ነበር።

፲፫.ወወፅአ ከይሲ ወቆመ ከመ ይርአይ ዘይከውን።

ከዚህም በኋላ አዳም ክብሩ ካለፈ ጸጋው ከተገፈፈ ዲያብ ሎስም ለአዳም ክብሩን ጸጋውን ቢሰጠውም ቢነሣውም አያለሁ ብሎ ከገነት ወጥቶ ከውጭ ቁሞ ያይ ጀመር።

፲፬.ወከዊ ፍና ሠርክ ወረደ እግዚአብሔር ምስለ ሠራዊቱ ወይቤ አይቴ ሀሎከ አዳም። ዘፍ ፫÷፱-፲

ይህ ነገር በጊዜ ቀትር ከተደረገ በኋላ በጊዜ ሰርክ ጌታ እልፍ አዕላፋት ወትዕልፊተ አዕላፋት መላእክትን ይ ወርዶ አዳም ከነበረበት ማዕከለ ገነት ደርሶ አዳም አዳም ወዴት ነህ አለው። ዘፍ 3÷9-10

፲፭.ወይቤ አዳም ሶበ ሰማዕኩ ድምፀከ እግዚኦ ፈራኅኩ ወተሀ ባዕኩ ውስተ ተክለ ገነት ተከዲንየ ቈፅለ በለስ።ዘፍ ፫÷፰-፲፩

አዳምም ጌታ በአምሳለ ሰብእ/በሰው አምሳል/ ጫማውን ተጫምቶ ሲመጣ ቴውን ሰምቶ ነበርና አቤቱ ጌታዬ በአምሳለ ሰብእ ስትመጣ ሰምቼ አፍሬ ጐስቁዬ ቅጠል ለብሼ ቅጠል ታጥቄ ከአትክልት ውስጥ ቁሜአለሁ አለው። ዘፍ 3÷8-11

፲፪.ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአዳም ምንተ ንከ ወመኑ ነሥአከ ዘወሀብኩከ አልባሰ ብርሃን። ዘፍ ፫÷፲፩-፲፪

ጌታም የሰጠሀህን የብርሃን ቀሚስ የብርሃን መጐናጸፊያ ማን ወሰደብህና እራቁቴን ሆኖለሁ ትለኛለህ ወይስ ከዚያች ቁዕለ በለስ በልተህላት ይሆንን አለው። ዘፍ 3÷11-12

፲፫.ወይቤ አዳም አንተ ዘወሀብከኒ ብእሲት ትንበር ምስሌየ ይእቲ አስሐተተኒ ወአብልዓተኒ ቁጽለ በለስ። ዘፍ ፫÷፲፪-፲፫

አቤቱ ጌታዬ ሆይ ያች አብራህ ትኑር ብለህ የሰጠኸኝ ሴት አሳተችኝ፤ ቁጽለ በለስን አብልታ ጸጋዬን አስገፈፈችኝ ክብሬን አሳለፈችብኝ አለው። ዘፍ 3÷12-13

፲፬.ወይቤላ እግዚአብሔር ለብእሲት አማንኑ አንቲ ገበርኪ ወቦኑ ባዕድ ዘነገረኪ። ዘፍ ፫÷፲፫-፲፬

ጌታም ሔዋን እውነት አንቺ አድርገሽው ይሆን ወይስ ሌላ የነገረሽ አለ? አላት። ዘፍ 3÷13-14

፲፬. ወትቤ ሔዋን አርዌ ምድር አስፈጠተኒ። ዘፍ ፫÷፲፫-፲፬

ሔዋንም አርዌ ምድር አሳተችኝ እንጂ እኔ ምን ላድርግ አለች። ዘፍ 3÷13-14

፳. ቀዳሚሰ ተሐውር በፅቱ እገሪሃ ወተአክል ዕጕለ ገመል ወዕፀብ ውእቱ አርአያሃ።

በዚህ ጊዜ ሦስቱን ረገማቸው። በፊት እባብን ረገማት ምን ብሎ ረገማት ቢሉ እባብ ቀድሞ እንዲህ አልነበረችም የግመል ወኀብሬ/ጊደር/ ታህል ነበረቺ፤ በአራት እግሯ ትሄድ ነበር። መልኳም ዕፁብ ድንቅ ነበር።

፳፩.ርግምተ ኩኒ እምኩሉ አራዊተ ምድር ሑሪ በእንግድዓኪ ወብልዓ መሬተ። ዘፍ ፫÷፲፬-፲፭

እባብንም ሲረግማት እንዲህ አላት ቁመትሽን አስረዝማ ከእንስሳት ከአራዊት አብልጬ ብፈጥርሽ አንቺ ከጠላቴ ከዲያብሎስ ጋር አንድ ሆነሽ ምክንያተ ስሕተት ከሆንሽ እርሱን ያመጣሽባቸው እግሮችሽ በሆድሽ ይግቡ መሬት ለብሰሽ መሬት በልተሽ ኑሪ ብሎ ረገማት። ዘፍ 3÷14-15

፳፪.አነ አስተጻርር ማዕከሌኪ ወማዕከለ ዘርአ ብእሲ ውእቱ ይቀጥቅጥ ርእሰኪ ወአንቲኒ ዕቀቢ ሰኰናሁ። ዘፍ ፫÷፲፭-፲፮

ባንቺና በሰው መካከል ፀብ ቂም በቀል አይለያችሁ። የሰው ልጆች ቢያገኙሽ ራስ ራስሽን ይቀጥቅጡ አንችም ስታገኛቸው እግር እግራቸውን ውጊያቸው አላት።ዘፍ 3÷15-16

፳፫.ወይቤላ እግዚአብሔር ለሔዋን በከመ አድመውኪያ ለእን ተኩ ዕፅ ከማሃ ድምዊ አንቲኒ ለለወርኑ። በሕማም ወበፃዕር ለዲ ወወሊደኪ ይኩን ምግባዕኪ ኀበ ምትኪ ወውእቱ ይቅንይኪ ለዓለም። ዘፍ ፫÷፲፮-፲፯

እባብን ከረገማት በኋላ ሔዋንን ረገማት። ምን ብሎ ረገማት ቢሉ ያችን ዕፀ በለስ ቈርጠሽ እንዳፈሰስሻት በእየወሩ ደምሽ ይፍሰስ። በሕማም በመከራ ውለጅ ወልደሽም አትመረሪ ወደባልሽ ተመለሽ ብሎ ረገማት። ዘፍ 3÷16-17

ከዚህም ቀጥሎ እግዚአብሔር ሔዋንን ከረገማት በኋላ አዳምን ርግማን ተቀበል አለው። አዳምም አቤቱ ጌታዬ እኔ ከነገሩ ያልነበርሁ ከምክሩ ያልተጨመርሁ ሔዋን በአመጣቺው እዳ አኔ እንዴት ርግማን ልቀበል አለው። ጌታም አዳም ሆይ ሥጋዋ ከሥጋህ አጥንቷ ከአጥንትህ ነፍሷ ከነፍስህ ተከፍሎ ተፈጥራለችና አይቀርልህም ተቀበል አለው። አዳምም አቤቱ ጌታዬ ሆይ ጌታና ሎሌ ተሟግቶ ድንጋይና ቅል ተማቶ እንዲሉ ሁሉ እኔ ከአንተ ጋር ተሟግቼ እችላለሁን ብሎ ርግማኑን በትህትና ተቀበለ።

፳፬.ኦ አዳም መሬት አንተ ወትገብዕ ውስተ መሬት።ዘፍ ፫÷፲፱-፳

ሲረግመውስ ምን ብሎ ረገመው ቢሉ አዳም እኔ ቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ አክብሬ በብርሃን ሸልሜ ብፈጥርህ ነው እንጂ ቀድሞ መሬት ነበርህ አሁንም ተመልሰህ መሬት ግባ ብሎ ረገመው። ዘፍ 3÷19-20

፳፭.ብላዕ በሀፈ ገጽከ ኅብስተከ፤ ሶክ ወአሜከላ ይብቁልከ ወርግምተ ትኩን ምድር በተግባርከ። ዘፍ ፫÷፲፯-፲፱

አዳም እኔ እንዳትወጣ እንዳትወርድ እንዳትማስን የምትበላ ውን የምትጠጣውን አንድ ጊዜ አዘጋጅቼ ብፈጥርህ አንተ

አምላክነቴን ከፈለግህ እየወጣህ እየወረድህ እየማሰንህ ብላ አሳብህ በምግብህ ይሁን። ምድርህ እሾህ አሜከላ ያብቅል ሆድህ ወስፋት ሶ ያብቅል እግርህን እሾህ ሆድህን ወስ ፋት እየወጋው ስትሣቀቅ ኑር ብሎ ረገመው። ዘፍ 3÷17-19

፳፮.ወሶበ ሰረብካሃ ለጽዋዓ ሞት መራር ለትርዓድ አባልከ ወት ትመሰው ከመ ሰምዕ ወእምድኅረ ይቤሎ ዘንተ እግዚአብሔር ለአዳም። ርዕደ አካሉ ወተመስወ ኩለንታሁ።

ዳግመኛም አዳም ሆይ ይህችን ጽዋዕ ሞት ስትቀምሳት አካልህ ይራድ እጅህ እግርህ ይንቀጥቀጥ አለው። ከዚህም በኋላ አካሉ ራደ እጁ እግሩ ተንቀጠቀጠ እንደ ሰም ቀለጠ። ቀድሞ አካሉ እንዲህ አልነበረም እንደፋና የበራ እንደ ብርሌ የጠራ የማይወጋ የማይበጣ ሽንት አሠር የማይወጣው ጥሩ አካል ነበረው።

የሚበላውም የሚጠጣውም በእሳት ላይ እንደ ጣሉት ሰም እየቀለጠ ይቀር ነበር። ይህም ይታወቅ ዘንድ ቅዱሳን በዚህ ዓለም ሲ ሩ በቅተው እየበሉ እየጠጡ ሽንት አሠር የላቸ ውም። እመቤታችንም በዚህ ዓለም ስድሳ አራት ዘመን ስት ር፤ ጌታም ክብር ምስጋና ይግባውና በዚህ ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ሲ ር እየበሉ እየጠጡ ይህ ሁሉ አልነበረባቸውም።

፳፯.ወ ነ ሰብአ ከማነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ።

ከኃጢአት በቀር እንደኛ ሰው ሆነ እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም

፳፰.ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአዳም ወይኬ አዳም አመ ተጸዋዕከ ውስተ መቃብር ትወርድ ነፍስከ ውስተ ሲኦል ወትከውን ገብሮ ለዲያብሎስ ወትሣቀይ በህየ ወኢትወፅእ ዘእንበለ ጊዜሁ።

እስከዚህ የሥጋው ርግማን ነው። ከዚህ ቀጥሎ ግን የነፍሱን ርግማን ነው። እግዚአብሔር አዳምን በነፍሱ ረገመው ምን ብሎ ረገመው ቢሉ አዳም ይህስ የሥጋ መከራ አላፊ ነው አላቂ ነው። ደግሞም በነፍስህ የማያልፍ የማያልቅ ብዙ መከራ አለብህና ርግማን ተቀበል አለው።

አዳምም አቤቱ ጌታዬ ነፍሴማ የአንተ እድል ፈንታህ ጽዋ ተርታህ አይደለችምን እንዴት ርግማን ልቀበል አለው። ጌታም አዳም እኔ ነፍስና ሥጋ አንድ ሁነው ቢመጡብኝ አንድ አድርጌ እቀበላለሁ እንጂ ለየብቻ እቀበላለሁን አይቀ ርልህምና ተቀበል አለው። አዳምም ርግማኑን በአኰቴት ወይም በጸጋ ተቀበለ። ሲረግመውስ ምን ብሎ ረገመው ቢሉ አዳም ሥጋህ መቃብር ስተገባ ነፍስህ ደግሞ ሲኦል ትውረድ ከዚያም ወርዳ በዲያብሎስ እጅ ትያዝ በሲኦል ትጋዝ ብዙ መከራ ብዙ ሥቃይ ትቀበል የዲያብሎስ ባሪያ ተገዥ ትሁን ከዚያም ካለቀኗ አትውጣ አለው።

ዳግመኛም አዳም እኔ በመንፈስ ቅዱስ አክብሬ በብርሃን ሸልሜ ብፈጥርህ አንተ አምላክነቴን ከፈለግህ ልብስህ ዳባ ይሁን ያም እያለቀ እያደፈ ዘለዓለም ስትሣቀቅ ኑር ብሎ

ረገመው። እንዲህ ብሎ ረግሞ አውሬ የሰበረው እንስሳ ነበረ የዚያን ቁርበት አለበሰው። ይህም ሐሰት ነው ያን ጊዜ ዳባ ተፍቆ ቁርበት ተዘፍቆ አልነበረም ያለበሰውስ ግምጃ ነው።

ስለምን ግምጃውን ዳባ አለው ቢሉ በቀደመ ልብሱ በዚያ የብርሃን መጐናጸፊያ አንጻር አይቶ ግምጃውን ዳባ አለ እንጂ፤ ያለበሰውስ ግምጃ ነው። ያን ጊዜም ግምጃ ተሠርቶ ተሰፍቶ አልነበረም ዳባ ያለውስ የገዛ ቁርበቱን ነው። ስለምን የገዛ ቁርበቱን ዳባ አለው ቢሉ አካሉ እንዲህ አልነበረም እንደፋና የበራ እንደ ብርጭቆ የጠራ የማይወጋ የማይበጣ ሽንት ዓሠር ደም ወዝ የማይወጣው ጽሩይ አካል ነበረው።

፳፱.ወይኩን ልብስከ አነዳ። ዘፍ ፫÷፳፩-፳፫

ወእምዝ አልበሶሙ አዕዳለ ዘማዕስ። ኩፋ ፬÷፳፬-፳፭

ልብስህ ዳባ ይሁን ብሎ በረገመው ጊዜ ግን አጥንቱ ከጅማቱ ሥጋው ከቁርበቱ አንድ ጊዜ የሚገፈፍ ሆነ።

ክፍል አምስት

፩. ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአዳም ፃዕ እምገነተ ተድላ ወረድ ውስተ ምድር ኀበ ይትበዓሱከ እንስሳት ወአራዊት ኀበ አልቦ ዕረፍት ዘእንበለ መከራ ወኢፍሥሐ ዘእንበለ ኀዘን አሐተ ሰዓተ።

ጌታም አዳምን እንግዲህ ጸጋህ ካለፈ ክብርህ ከተገፈፈ በኋላ በዚህች ጸጋ ክብር ካለባት ከገነት መ ር አይገባህምና ከመከራ በቀር ዕረፍት ከኀዘን በቀር ደስታ ወደ ሌለበት ምድር ውረድ አለው። ከዚያም ወርደህ ከአራዊት ከእንስሳት ጋር ከአጋንንትም ጋር ተጣላ ተዋጋ ባላጋራ ይሁኑህ አለው።

፪. እፎ ይትከሀለኒ እግዚእየ እትበዓስ ምስለ አጋንንት ረቂቃን ይክልኑ ይትበዓስ ሣዕር ምስለ እሳት ወእሳት ምስለ ማይ።

አዳምም አቤቱ ጌታዬ እንስሳት አራዊት ግዙፋን ናቸው ታይተው ይመጣሉ ቢወጓቸው ይሞታሉ እንደ እኔ መሬታ ውያን ናቸው። ከአጋንንት ከረቂቃኑ ጋር መጣላት እንዴት ይቻለኛል። ሣር ከእሳት ጋር እሳት ከውኃ ጋር መጣላት ይችላልን አለው።

፫. ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአዳም ይመስለከኑ ዘንተ ገነተ ዘነደገ ለከ አቡከ ርስተ ወሚመ ዘተሣየጥ በወርቅከ አ ኑ አነ ቀዲሙ ዘወሀብኩከ።

ጌታም አዳምን ይህችን ገነት ርስት ትሁንህ ብሎ የሰጠህ ሌላ ጌታ አለን ወይስ አንተ በወርቅህ ገዝተሃታልን ቀድሞ የሰጠሁህ እኔ አይደለሁምን አሁንስ ውረድ ብዬ ሳዝዝህ ውረድ እንጂ። ጥንቱንስ መወረድህ ለመከራ ነው እንጂ ለደስታ ነውን አለው።

፬. ወአመ አውፅአሙ እግዚአብሔር ለአዳም ወለሔዋን ውስተ ገነተ ተድላ በከዩ አዕዋፍ ወአንስርት ወዕፀዊሃ ለገነት እንዘ ይብሉ ወይኬ ለነ አጋዕዝቲነ ወመሳፍንቲነ መኑ ሠረወክሙ እማዕከሌነ ንሕነሰ አቅረብነ ለክሙ ፍሬ አጥባቲነ ዘይጥዕም እመዓር ወሦከር አንትሙሰ መነንክሙ ዘንተ ወአብደርክሙ ትብልዐ ፍሬሃ ለዕፀ ሞት መኑ መከረክሙ ወመኑ ነገረ ክሙ ዘንተ።

ከዚህ በኋላ አዳምና ሔዋን ከገነት ወጥተው ሲሄዱ ቅጠል ለብሰው ቅጠል ታጥቀው እጃቸውን በራሳቸው ላይ ጭነው ወዬው ሀገራችን ወዬው ተድላችን እያሉ እያለቀሱ ሲወርዱ በገነት ያሉ አዕዋፍ አንስርት ወዬው የገነት መኳንቶች መሳፍንቶች ከዚያ የብርሃን መጋረጃ ማን አስወጣችሁ ከመካከላችንስ ማን ነው የለያችሁ የነጠላችሁ እያሉ ተከተሏቸው። ዕዕዋቱም እኛስ ከማር ከወተት የሚጣፍጥ የጡታችን ፍሬ አቅርበንላችሁ ነበር እናንተ ግን ይህን ትታችሁ ያችን ሞት ያለባትን የእንጨት ፍሬ በልታችሁ ይህ ሁሉ መከራ አገኛችሁ። ይህንን የመከራችሁ የነገራችሁ ማን ይሆን እያሉ እያለቀሱ ሸኝተዋቸው ተመለሱ።

፮. ወባሕቱ እግዚአብሔር ይሣሃልክሙ በሣህሉ ወያጽግብክሙ በብዕሉ ወያብዕክሙ ውስተ ርስቱ ዘለዓለም በሰላም።

ከዚህም በኋላ የአዳምና የሔዋን ከገነት መውጣታቸው ቁርጥ ሆ በታወቀ ጊዜ አዕዋፍ አንስርት ዕፅዋት በባለጸግነቱ ይመግባችሁ በቸርነቱ ወደ ዘለዓለም ርስቱ ይመልሳችሁ ብለው ሸኝተዋቸው ተመለሱ፤ ይህም ልማድ ሆ ቀርቷል። ዛሬ ሰው ከአገሩ ተሰዶ ሲሄድ ደህና ያግባህ በደህና ይመልስህ ብለው ሸኝተውት እንደሚመለሱ ሁሉ።

፯. ወአዘ እግዚአብሔር ለሱራፊ መልአክ ዘውስተ እዴሁ ሰይፈ እሳት እንተ ትትመያየጥ ወዓቀሞ በአንቀጸ ገነት ከመ ኢይግባዕ አዳም ተሀቢሎ። ዘፍ ፫÷፳፬
ከዚህም በኋላ ጌታ አዳምን ተደፋፍሮ ገነት እንዳይገባ ብሎ ሱራፊ የሚባል መልአክ ሰይፉን አስመዝ በገነት ደጅ አጋፋሪ አቆመበት። ዘፍ 3÷24

፯. ወይቤ አዳም ወይ ሊተ አሌ ሊተ እንዘ ንጉሥ አነ ንኩ ሥዑረ ወእንዘ ባዕል አነ ንኩ ነዳየ ወእንዘ ጻድቅ አነ ንኩ ኃጥአ ወእንዘ ልዑል አነ እምልብሰ ብርሃን ንኩ ዕሩቀ።

አዳምም ወዮልኝ ወዮታ ይገባኛል እያለ ያለቅስ ይጨነቅ ጀመር።

ቀድሞ እንስሳት አራዊት በመንገድ እየቆዩ ብላን ጠጣን ይሉት ይሰግዱለት የነበረ እንበላሃለን እንወጋሃለን እያሉ ይፈልጉት ጀመር፤ አዳምም መከራ ቢጸናበት የክረምት

ዝናም ያህል እያለቀሰ ከአንዱ ዱር ወደ አንዱ ዱር፣ ከአንዱ ዋሻ ወደ አንዱ ዋሻ፣ ሲ ር አይቶ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ አዳም ተው መከራህ እንዲህ በቶሎ የሚያልቅ አይደለም ብሎ ደብር ቅዱስ ወደሚባል ተራራ ወስዶ አ ረው።

፰. ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ኀዘ ለአዳም ይቤሎሙ ለመላእ ክቲሁ እመሰ ነ ልቡ መጠነ ሰማይ ወምድር ሊተኒ ሀለወተኒ እሳት ዘኢያገምርዋ ፫ቱ ሰማያት።

ጌታም መላእክትን የዚህ የዲያብሎስን ክፋት ታዩታላችሁን ቀድሞ ከሠራው ሥራ የዛሬው ይበልጣል። ይህ ሁሉ የአዳም መከራ የመጣ በርሱ አይደለምን ምን ላድርገው ፍረዱ አላቸው መላእክትም አቤቱ ጌታችን የዲያብሎስማ ክፋት ከሰማይና ከምድር እንዲበልጥ እናውቅ የለምን አሉት። ጌታም ክፋቱስ ከሰማይና ከምድር ከበለጠ ሰማይና ምድር ሦስቱ ሰማያት የማይችሏት እሳት አለችኝና ከዚያች አግብቼ እቀጣዋለሁ አላቸው።

፱. ወአዘ ሙ እግዚአብሔር ለ፬ቱ መላእክቲሁ ጽኑዓን ወኃያ ላን ወይቤሎሙ ዕሥርዎ ለዲያብሎስ በ፭፻ ፻ ሰናስለ እሳት ። በ፭፻ ፻ መዋቅሕተ እሳት። በ፭፻ ፻ ስጉንጥረ እሳት በ፭፻ ፻ መሐፒለ እሳት ወዕሥሩ እደዊሁ ወእገሪሁ ምስለ ክሣዱ ወረስይዎ ዓምደ ለገሃነም ከመ ኢይፃዕ እስከ ለዓለም።

ጌታም እንዲህ ብሎ አልቀረም ከመላእክት አራት ኃያላኑን ጽኑዓኑን መርጦ አንሥቶ ሂዱ ዲያብሎስን በአምስት መቶ ሺህ የእሳት ሰንሰለት በአምስት መቶ ሺህ የእሳት ችቦ በአምስት መቶ ሺህ የእሳት ዛንጀር በአምስት መቶ ሺህ የእሳት መሐፒል አምጥታችሁ እጁን ከእግሩ እግሩን ከአንገቱ አሥራችሁ በገሃነመ እሳት ተክላችሁ እንደ አምድ እንደ ግንድ ገልብጣችሁ ለዘለዓለም እንዳይወጣ አድርጋችሁ ተውት ብሎ አዘዘ።

፲. ወካዕበ አዘ ሙ እግዚአብሔር ለፀቱ መላእክት ጽኑዓን ወኃያላን እንዘ ይብል ዕሥርዎሙ ለሠራዊተ ዲያብሎስ ወደምርዎሙ ምስሌሁ።

ዳግመኛም ጌታ ሠራዊቱንም እንደርሱ አድርጋችሁ በገሃነም ዙሪያ አስፍሩለት ብሎ ለአራቱ ጽኑዓን ኃያላን መላእክት አዘዛቸው።

፲፩.ወሰአለ ዲያብሎስ ኀበ እግዚአብሔር እንዘ ይብል እለ ያፈቅሩኒ ወይገብሩ ትእዛዝየ ይትልውኒ።ፎኛ መቃብ ፩÷፲፯-፲፰

ዲያብሎስም አቤቱ ጌታዬ እኔ ከአዳም የበለጠ በደል ምን በደልሁና ብቻዬን ታወርደኛለህ አሁንም ከአዳም ልጆች እኔን ያፈቀሩ አብረውኝ እንዲወርዱ አድርግልኝ ብሎ ለመነው። 3ኛ መቃብ 1÷17-18

፲፪.ወይቤሎ እግዚአብሔር ለዲያብሎስ ዘአፍቀሩሰ ኪያከ ይትልውከ ባሕቱ በስምየ እከው ሙ ረዳኢ ከመ ኢታስ ፍጦሙ አንተ። ፫ኛ መቃብ ፩÷፳፪-፳፫

ጌታም እንዳታስታቸው እንዳትሸፍጣቸው በስሜ እረዳቸዋ ልሁ እንጂ ከእኔስ አንተን ከወደዱ ይሁኑልህ አለው። 3ኛ መቃብ 1÷22-23

፲፫.ወይቤሎ ዲያብሎስ ለእግዚአብሔር ፍታሕ ሊተ ፩ደ ጾታ እምሠራዊትየ ከመ ይትፋተንዎሙ ለፍቁራኒከ።

ዲያብሎስም እኔ ከዚያ ሆኜ እንዳልፈታተን ከሲኦል እሳት ታሥሬ ወድቄአለሁ። አሁንም አንዱን ነገድ ፍታልኝና ከዚያ ሆነው እየተፈታተኑ የእኔን ጠላቶች የአንተን ወዳጆች መላእክቶችህ ወደ አንተ ያምጡልህ፤ የእኔን ወዳጆች የአንተን ጠላቶች ሠራዊቶቼ ወደ እኔ ያምጡልኝ አለው።

፲፬.ወእምዝ ፈነዎሙ ዲያብሎስ ለሠራዊቱ ውስተዝ ዓለም ከመ ይትፋተኑ ወይትዓቀብዎሙ ለአጽራረ እግዚአብሔር።

በዕለተ ረቡዕ የዲያብሎስ ሠራዊቶች ከሦስት ተከፍለው ነበር። ሲሶው ይሆን አይሆን ብለው የተጠራጠሩት ናቸው። ሲሶው አንተ ከፈጠርህ እኛም እንፈጥራለን ያሉት ናቸው። ሲሶው በአማን/በእውነት/ ፈጣሪ ነህ ብለው የሰገዱለት ናቸው። ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር በአማን/በእውነት/ ፈጣሪ ነህ ብለው የሰገዱለትን ፈታለት። ሲፈታለትም ጊዜ

በዚህ ዓለም በሣሩ በእንጨቱ በውኃው በድንጋዩ በአዝርዕቱ በአትክልቱ በምሥራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ በየአለ ቃው ሹሞ ሰደደ። እነዚያም ወደዚህ ዓለም መጥተው ክደው ሲያስክዱ ስተው ሲያስቱ የሚ ሩ አጋንንት እነዚህ ናቸው።

፲፭.ወበእንተዝ ይቤ ነቢይ ከመ ኢይትዓፀው እለ ፍቱናን ከመ ብሩር ጽሩይ ንጡፍ ወፍቱን እምድር ዘአፅረይዎ ምስብዒተ መዝ ፳፩÷፮-፯

በምድር ላይ እንደተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደተጣራ ብር፤ መዝ 11÷6-7

፲፮.ከመ ወርቅ ዘይትፈተን በምንሐብ ፈተ ሙ ወከመ ጽንሐሓ መሥዋዕት ተወክፎሙ ዝኬ በእንተ ጻድቃን እለ ይደልዎሙ ጥበብ ፫÷፭-፯

ዛሬ ብር ወርቅ በከውር ሆ በእሳት ተፈት ጽሩይነቱ ሲታወቅ ለንጉሥ እንደሚቀርብ ሁሉ፤ የአዳም ልጆችም ስመ ሥላሴን አጋዥ ጠበቃ ይዘው ከፀብዓ አጋንንት ተዋግ ተው ድል ካልነሱ መንግሥተ ሰማያትን የሚገባባት የለም ብሎ ነቢዩ ተናገሯል። ጥበብ 3÷5-7

፲፯.አልቦ እምደቂቀ አዳም ወሔዋን ዘይበውዕ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ዘእንበለ ሕጻናት ባሕቲቶሙ።

ከአዳም ልጆች ስመ ሥላሴን አጋዥ ጠበቃ ይዘው ከፀብዓ አጋንንት ተዋግተው ድል ካልነሱ ከሕጻናት በቀር መንግሥተ ሰማያትን የሚያገኛት የለም።

፲፮.ወይቤሎ ዲያብሎስ ለእግዚአብሔር እመሰ ወሀብከኒ እምደ ቂቀ አዳም እለ አፍቀሩኒ ዘኢተፈትነ እምኔየ በ፡ነቤሆሙ ኢይበውዕ ውስተ መንግሥተ ሰማያት እስመ አልቦ አድልዎ በ፡ነቤከ።

ዲያብሎስም ጌታን አቤቱ ጌታዬ ከአዳም ልጆች እኔን ያፈቀሩኝን ከሰጠ፡ኸኝ ወዲያ በአንተ ዘንድ ሁለት ነገር አድልዎ የለምና አታድላብኝ ብሎ ነገሩን አጸና።

፲፯.ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአዳም ሰማዕከኑ ዘይቤ ዲያብሎስ ጸላኢከ ተጋደል ፈድፋደ ወጽናዕ በምልዓ ዕድሜከ።

ጌታም አዳምን ጠላትህ ዲያብሎስ ያለህን ሰማ፡ኸውን አሁንም በእኔ ዘንድ ሁለት ነገር አድልዎ የለምና እስከ ጊዜህ ድረስ ጠንክረህ ተዋጋ ተጋደል አለው።

፲፰. ወይቤልዎ አዳም ወሔዋን ንሕነሰ አላግዒከ በልዓነ ነምር ወለአርጋቢከ ነሥአነ አንቄ። ወረከበነ ለአልህምቲከ አንበሳ ዐቢይ ሰበረነ ወዘርዘረ አዕፅምቲነ።

አዳምና ሔዋንም አቤቱ ጌታችን እኛስ የሰጠ፡ኸንን እህል በልተን የሰጠ፡ኸንን ውኃ ጠጥተን ከመ ር በቀር ምን እናውቃለን። አሞራ ይነጥቀናል፣ አንበሳ ይሰብረናል፣ ነብር ያንቀናል እንጂ አንችልም አሉት።

ክፍል ስድስት

፩. ወይቤልዎ አዳም ወሔዋን ተዘከር እግዚኦ ፅዕለተነ ወኃፍረ ተነ ነዋ ነሥአነ ውኂዘ ሲኦል ወተርኅወ ለነ አንቀጸ ሲኦል ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ ለዓለመ ዓለም አሜን። ወነበሩ በዝንቱ ጸሎት እንዘ የኃዝኑ በንስሐ እስከ ይትጌመድ ሥጋሆሙ።

ዳግመኛም አዳምና ሔዋን አቤቱ ጌታችን እነሆ እኛን የሲኦል ሙላት ዋጠን፣ የሲኦል አንቀጽ ተከፈተብን፣ አንተ ግን ይህን መከራችን አይተህ ፈጥነህ ይቅር በለን እያሉ አጥንታቸው እስኪከሰክስ ሥጋቸው እስኪቄረስ ደማቸው እስኪፈስ ድረስ እያዘኑ በደብር ቅዱስ ተቀመጡ።

አዳምም ሔዋንን ከዚህ እህል እየበላን ውኃ እየጠጣን የጸለይነው ጸሎት ከእግዚአብሔር ዘንድ አልደረሰልንምና ከእህል ከውኃ ተለየተን ለየብቻ ሆነን አርባ ቀን ሱባኤ እንግባ አላት። ሔዋንም እሽ ብላ እርሱ ከአንዱ ባሕር እርሷ ከአንዱ ባሕር ገቡ። በገቡ በሠላሳ አምስተኛ ቀናቸው፦

፪. ወመጽአ ሰይጣን በአምሳለ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤሎ ለአዳም ናሁ ተሰምዓት ጸሎትከ ወገዳርከ ቅድመ እግዚአ ብሔር ነዋ ፈነወኒ ከመ አብፅኅሙ ውስተ ገነት።

ዮ፯፩

ዲያብሎስ መልአከ እግዚአብሔር መስሎ መጥቶ አዳምን ይህ ሁሉ ጸሎትህ ጋርህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ደርሶልሃልና ገነት አግባቸው ብሎ ሰዶኛል። ሔዋንን ጥራት ልውሰዳችሁ አለው።

፫. ወተጋደሎ አዳም ለዲያብሎስ እንዘ ይብል አንሰ ኢይወፅእ ዘእንበለ እፈጽም ፶ ዕለተ እስመ ብፅዓት ብየ።

አዳምም እኄስ ያሰብኩት ቀ ና አርባ ቀን ነውና ያንን ሳል ጨርስ አልወጣም ብሎ ተከራከረው።

፬. ወይቤሎ ዲያብሎስ ለአዳም ለእመ መሀረከ እግዚአብሔር አንተኑ ኢትምህር ርእሰከ ቅድመኒ በላዕከ እምዕፅ ዘኢ አዘዘከ እግዚአብሔር ወ ንከ ለመከራ።

ዲያብሎስም አንተስ ቀድሞም ትዕቢተኛ በደለኛ ነህ። በፊት አትብላ ያለህን በለስ በልተህ ከገነት ወጣህ ከክብርህ ተዋረ ድህ አሁን ደግሞ እርሱ ቢምርህ አንተ ራስህን አልምርም ትላለህ። አሁንም እኄ ትቻችሁ መሄዴ ነው። እናንተም የሰይጣን መጫወቻ ሆናችሁ መቅረታችሁ ነው። ነገር ግን ሔዋን የት ናት አሳየኝና ተገናኝቻት ልሂድ አለው። አዳምም እኄ ንዴት መከራ ቢበዛብኝ ክብር ጸጋ ይበዛልኛል እንጂ ምን ይቀርብኛልና፤ ሔዋንም ያቻት ከዚያ አለችልህ አለው።

፭. ወቦአ ሰይጣን ኀበ ሔዋን ወሶበ ይቤላ ንዒ ዋዒ ወፅእት ፍጡነ እስመ ገራህቱ ይእቲ ወነሥአ ከመ ክንፈ ጉዛ።

ዲያብሎስም ሔዋን ከአለችበት ሄዶ ሔዋን ሔዋን ብሎ ጠራት እርሷም የጥንት ማሳው ናትና አልተከራከረችውም እንደ ጭላት አሞራ መዘዝ ብላ ወጣች።

ዲያብሎስም ስትወጣለት ጊዜ ታይዋለሽ የባልሽን ነገር ቀድሞ አትብላ ያለውን ዕፅ በልቶ ከክብሩ ተዋረደ ከገነት ወጣ። አሁን ደግሞ ገነት አስግባቸው ብሎ ቢልከኝ አይሆ ንም አለ። እኔም እንግዲህ አልመጣም ትቻችሁ መሄዴ ነው እናንተም የሰይጣን መጫወቻ ሆናችሁ መቅረታችሁ ነው። ስለዚህ ይህን ነገር እወቂበት አላት።

እርሷም አዳም የዋህ ነው አታውቀውም እንጂ አሁንም የእርሱ ነገር አይጐዳም ብላ ወደ አዳም ይዛው ሄደች። ሄዳም አዳም እንዲህ ያለውን ነገር ለምን ታደርጋለህ፤ ጥንቱንስ ሱባኤ መግባታችን እንዲምረን አይደለምን። እንኳን በሠላሳ አምስት ቀን በሦስት በአራት ቀን ቢምረን አይቻለውም ትላለህን። አሁንም እባክህ ከዚህ መልአክ ተለይተን አንቅር አለችው። አዳምም በሔዋን መንገድ ድል መነሣት ልማዱ ነውና እሽ እንዳልሽው ይሁን አላት።

፮. ወወሰዶሙ ዲያብሎስ ለ፪ኤሆሙ ወአብጽሖሙ ኀበ እግረ ገነት ወይቤሎሙ አእመርክሙኒኑ መኑ አነ።
ከዚህም በኋላ ዲያብሎስ ፊት ፊት አዳምና ሔዋን ከኋላ ኋላው ሲሄዱ ከእግረ ገነት ደረሱ ዲያብሎስም እኔ ማነኝ አወቃችሁኝን አላቸው።

፯. ወይቤሎ አዳም ለዲያብሎስ አ ኑ አንተ ትቤ መልአከ እግዚአብሔር አነ ንሕነሰ ኢነአምረከ፡፡
አዳምም መልአከ እግዚአብሔር ገብርኤል ነኝ አልኸን እንጂ እኛ የት እናውቅሃለንና አለው፡፡

፰. ወይቤሎሙ ዲያብሎስ ለአዳም ወለሔዋን አነ ውእቱ ዘአው ጻእኩክሙ እምገነተ ተድላ ወተናገርኩክሙ በአፈ ከይሲ ወይእዜኒ ጠሰይክዋ ለንስሐክሙ ወ ንክሙ ኅጉላነ ወቀበ ፅክሙ ተስፋ ዘለዓለም፡፡
ዲያብሎስም እኔማ እኔ ነኛ ቀድሞ አትብላ ያለህን በለስ አስበልቼ ከክብርህ አዋረድኩህ ከገነት አስወጣሁህ፡፡ አሁንም ፈጣሪዬን እፈልጋለሁ ብለህ ቀ ና ብትገባ ናብሎሃል ብዬ አስተጓጐልሁህ ከእንግዲህ ወዲህ ምንም ተስፋ የለህም ብሎ መጥፎ ሽታውን አሸተተው ጸዋግ/ክፉ/ መልኩን አሳየው፡፡ አዳምም ደንግጦ ወደቀ ዲያብሎስም ጠላቴ ሳይነሳብኝ ብሎ ቤት ያህል ድንጋይ አንሥቶ ጫነበት፡፡

፱. ወተደብተረት ሎሙ ይእቲ ዕብን፡፡ ደንገጸ አዳም ወወድቀ ወኢተንሥአ እስከ ፫ቱ ዕለት፡፡
ያችም ድንጋይ አንደ ድንኳን ተተርትራ ተዘርግታለት አዳምም በውስጧ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት ሰነበተባት፡፡
አዳምም በሦስተኛው ቀን ቢነሳ ሥጋው ተቈርሶ ደሙ ፈስሶ አጥንቱ ተከስክሶ አገኘው፡፡ አዳምም ፍሬ ዕፅ አምጥቶ በደሙ

ለውሶ ስንዴ በምትመስል ዕብነ በረድ በትእምርተ መስቀል መስዋዕት ለፈጣሪው ዓሳረገ።

፲. ወእምዝ ወረደ እሳት ሕያው ዘይትለአክ ቅድመ እግዚአብሔር ወበልዓ መስዋዕቶ ምስለ ዕበኒሁ እስከ ይልሀስ መሬተ።

ከዚህም በኋላ ከእግዚአብሔር የታዘዘ እሳት ወርዶ መስዋዕቱን ከድንጋዩ ጋር በልቶ መሬቱንም ጨምሮ ላሰ አደረገለት። ጌታም ተጋፍቶ ቢጠሩት ፈጥ ቶሎ አቤት ይላልና በብርሃን ደመና ተጭ ወርዶ አዳም አዳም ብሎ ጠርቶ ምን ሆንህ፣ ምን አገኘህ አለው። አዳምም እኔ ያልሆንሁኝ ማን ይሁንልኛ ያየቀደመ ጠላቴ ዲያብሎስ ቀድሞ አትብላ ያልኸኝን በለስ አብልቶ ከገነት አወጣኝ ከክብሬ አዋረደኝ። አሁን ደግሞ አንተን እፈልጋለሁ ብዬ ቀ ና ከገባሁበት ና ብሎሃል ብሎ አውጥቶኝ ሥጋዬ ተቁርሰ፣ ደሜ ፈሰሰ፣ አጥንቴ ተከሰከሰ እኔም ግፌ ይታይህ ብዬ ደሜን መሥዋዕት አድርጌ አሣረግሁልህ አለው።

፲፩.ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአዳም በከመ አዕረገ ሊተ አንተ መሥዋዕተ በደምከ ከማሁ አነኒ አዓርግ መሥዋዕተ በደምየ ለአቡየ ወእትቤዘወከ በሞትየ ወበመስቀልየ አለው።

ጌታም አዳም አንተ ደምህን መሥዋዕት አድርገህ እንዳሣረ ግህልኝ እኔም ከሰማየ ሰማያት ወርጄ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በመስቀል ተሰቅዬ ሥጋዬን ቁርሼ ደሜን አፍስሼ ለባሕርይ

፻፯፰

አባቴ ክሼ ከጠላትህ ከዲያብሎስ እዋጅሃለሁ። ከሲኦል እሳት አወጣሃለሁ ገነት አስገባሃለሁ ብሎ ተስፋ ሰጠው።

፲፪.እስከ ማዕዜኑ ትገብር ሊተ እግዚእየ ዘትቤ እሣሀለክመ።

አዳምም አቤቱ ጌታዬ ይህንን የሰጠኸኝን ቃል ኪዳን እስከ መቼ ድረስ ትፈጽምልኛለህ አለው።

፲፫.በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድህክ ውስተ መርህብከ ወእከውን ሕፃነ በእንቲአከ ወእትቤዘወከ በሞትየ ወበመስቀልየ።

ጌታም ለአዳም በአምስት ቀን ተኩል ከሰማየ ሰማያት ወርጄ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በመስክህ ድኼ በመስቀል ተሰቅዬ ሥጋዬን ቁርሼ ደሜን አፍስሼ ለባሕርይ አባቴ ክሼ ከጠላትህ ከዲያብሎስ አገዛዝ ነፃ አደርግሃለሁ፤ ከሲኦል አወጣሃለሁ ገነት አስገባሃለሁ ብሎ ቁርጥ ቀጠሮውን ነገረው።

፲፬.እስመ ፲፬ ዓመት በቅድሜከ ከመ ዕለት እንተ ትማልም ኃለፈት። መዝ ፹፱÷፬-፭

ይኸውም በአምስት ቀን ተኩል ያለው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ቀን የምትባለው በኛ ዘንድ አንድ ሽህ ዘመን ናት። መዝ 89÷4-5

፲፭.ወባሕቱ ኢትግበር መሥዋዕተ በደመ ሰብእ እስመ ኢይት ሜጠው ለከ።

ጌታም አዳምን ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ደም አትሠዋልኝ አልቀበልልህምና አለው።

፲፮.ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአዳም ግበር መሥዋዕተ በአልህምት ወበአባግዕ፣ ወበአጣሊ፣ በፍሬያት፣ ወበጽጌያት።
አዳምም አቤቱ ጌታዬ ምን ልሰዋልህ ቢለው ጌታም ላም፣ በግ፣ ፍየል፣ ፍሬያት፣ ጽጌያትን ሠዋልኝ አለው።

፲፯.ወካዕበ ይቤሎ ኢትግበር መሥዋዕተ በዓሣ እስመ ኢይት ኀለቁ ኅበ አልህምት ወአባግዕ ወአጣሊ ወኢኅበ ፍሬያት ወጽጌያት አላ ይኩንክ ከመ ሐምል ዘባሕር ለሰላይክ።

ዳግመኛም ከእነዚህ ከቁጠርሁልህ ለዓሣ ቁጥር የለውምና ለአንተ የባሕር ጉመን ይሁንህ እንጂ ለእኔ መሥዋዕት አድርገህ አትሠዋልኝ አልቀበልህምና አለው። ጌታም ይህን ቃል ኪዳን ሰጥቶት ወደ ሰማየ ሰማያት አረገ።

፲፰.ወወረደ ገብርኤል መልአክ ወወሰዶ ለአዳም ወአግብኦ ኀበ መብዝኅተ በዓት።
ከዚህም በኋላ ቅዱስ ገብርኤል ወርዶ ወደ ረጅም ተራራ አሥራ ሁለት ዋሻ ከአለበት ወስዶ አዳምን እንደ እልፍኝ እንደ አዳራሽ ይሁንህ ከዚህ ተቀመጥ አለው።

፲፱.ወይቤሎ አዳም ለገብርኤል ምንተ እሴሰይ ዝየ እስመ አልቦ ዘአንበለ ዕብን ወከመ ኢይፃዕ አፍአ ይትበዓሱኒ እንስሳት ወአራዊት።

ከዚህም በኋላ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ውጭ ወጥቶ እሄዳለሁ ብሎ ሲል አዳም ጌታዬ ከዚህ ከባዶ ዋሻ በቀር ምንም የለም። ወደ ውጭ ወጥቼ ምግቤን እንዳልፈልግ እንስሳት አራዊት ይጣሉኛል የምግቤን ነገር እንዴት አድርገኸኝ ትሄዳለህ አለው። ቅዱስ ገብርኤልም የምግብህንማ ነገር ከፈጣሪህ ተነጋገር እንጂ እኔ ምን ልበልህ አለው። አዳምም ከፈጣሪዬ ጋርማ ጥለኛ አይደለሁምን አንተ ንገርልኝ እንጂ አለው።

፳. ወተራኅራኃ ሎቱ ገብርኤል ወቦአ ውስተ ገነት።

ቅዱስ ገብርአልም የአዳምን ጦም ማደር አይቶ አዝ ለት ራርቶለት ወደሰማይ መሄዱን ትቶ ወደገነት ሄደ።

፳፩.ወይቤሎሙ ገብርኤል ለአዕዋፈ ገነት ነዋ ንጉሥክሙ አዳም ይመውት በረሀብ ሰዱ ሎቱ ሲሳዮ ወለእመ ኢወሰድክሙ ሲሳዮ ድኅረኒ ይትቤቀሉክሙ ደቂቁ ወይሰድዱክሙ እም አብያቲክሙ።

ወደ ገነትም ሄዶ መጥቅዕ/ደወል/ በደወለ ጊዜ አዕዋፍ አንስርት ተሰበሰቡ። እርሱም ከዚያ ከባዶ ዋሻ ጌታችሁ አዳም ወድቆ ረሃብ ጸንቶበት ቀጠና ይ ታልና ቀድሞ ይመገባቸው ከነበሩት ፍሬያት ጽጌያት ምግቡን ወስዳችሁ አግቡለት አላቸው። ይህን ግን እንቢ ብትሉ ኋላ ልጆቹ የልጅ ልጆቹ ገነትን ሳይገቡባት አይቀሩምና ይበቀሏችኋል።

ዕንቁላላችሁን ይሰብሩባችኋል። ጫጩቶቻችሁን ይገድሉባች ኋል። ጐጆዎቻችሁን ያፈርሱባችኋል። እያስወጡ ይሰዷች ኋል አላቸው።

፳፪.ወሶበ ሰምዐ አዕዋፈ ገነት ቃሌ ለገብርኤል ወሰዱ ሎቱ ሲሳዮ ለአዳም ፍሬሃኒ ወጽጌሃኒ ወቁዕላኒ ለገነት ወመልዐ ፲ተ ወ፪ተ በዓታተ አፈ እስከ አፍ።

ከዚህም በኋላ አእዋፍ አንስርት የቅዱስ ገብርኤልን ቃል ሰምተው የሚበላውን ዘለላውን የሚያሸተውን አበባውን የሚያነጥፈውን ቅጠሉን ወስደው አሥራ ሁለት ዋሻ አፍ እስከ አፍ ሞሉለት።

፳፫.ወይቤልዎ አዕዋፈ ገነት ለአዳም ኦ እግዚእነ ጊዜ ጸዓትከ ወስደትከ እስመ አቅረብነ ለከ ለሲሳይከ ፍሬሃኒ ወጽጌሃኒ ወቁዕላኒ ለገነት ወይእዜኒ ጸሐፍ ለነ ተዝካረ ከመ ይስምዑ ደቂቅከ ወኢይግፍዑነ በደኃሪ መዋዕል።

የዚህም የዋሻው ስፋቱ አንድ ምንዳፈ ሐፅ/የቀስት ውርወራ ያህል ርቀት/ ይሆናል። ከዚህም በኋላ አዕዋፍ አንስርት አዳምን አቤቱ ጌታችን በጊዜ ስደትህ የምትበላውን ዘለላ ውን የምታሸተውን አበባውን የምታነጥፈውን ቅጠል አመ ጣንልህ፤ ልጆቹ የልጅ ልጆቹ ገነት ሳየገቡ አይቀሩም ብሎናልና፤ ልጆችህ እንዳይበቀሉን ጫጩቶቻችን እንዳይገ ድሉብን ዕንቁላላችንን እንዳይሰብሩብን እኛን እያስወጡ እንዳይሰዱን አድራጐታችንን ጸፍልን አሉት።

፪፻፪

፳፬.ወጸሐፈ ሎሙ አዳም በዕብን ለአዕዋፈ ገነት ወተባረኩ እምኔሁ።

ከዚህም በኋላ አዳም የእኔ ወገን የሆናችሁ የነዚህን አዕዋፍ አንስርት ጫጩቶቻቸውን የገደላችሁ ዕንቁላላቸውን የሰበራችሁ ጐጆዎቻቸውን ያፈረሳችሁ ርጉማን ሁኑ ብሎ በድን ጋይ ላይ ቀርጾ ጽፎ ሰጣቸው እነዚያም ያን ተቀብለው ከአዳም ተባርከው ሄዱ።

አዳምም በገነት ሳለ የአዕዋፍ የአንስርት ቋንቋቸውን ያውቀ ዋልና እንሂድ እንሂድ ሲባባሉ ሰምቶ ዛሬ ከሀገሩ የወጣ ሰው የሀገሩን ሰው ሲያገኝ እንዲናፍቅ ሁሉ አዳምም አዕዋፈ ገነትን ተከትሏቸው ሄደ። እነዚያም በክንፋቸው እየበረሩ ሄዱ።

፳፭.ሰኰየ አዳም ውስተ ገዳም።

አዳምም ዱር ለዱር ዋሻ ለዋሻ በረሀ ለበረሀ ሲቅበዘበዝ ያ የቀደመ ጠላቱ ዲያብሎስ አገኘው።

፳፮.ወዘበጦ ዲያብሎስ ለአዳም በዕብን እስከ ወድቀ በገጹ ወው ኀዘ ደም እምኔሁ።

ዲያብሎስም አንተ ከገነት የወጣህ ዕለት ልብህ የጠፋ አትደርሰበት የለ ከዚህ ማን አመጣህ ብሎ በድንጋይ ራሱን መቶ ጣለው። አዳምም ወደቀ ዲያብሎስም ገደልኩት ብሎ ሄደ።

፳፯.ወይቤሎ ገብርኤል ለአዳም ከመዝ ይቤለከ እግዚአብሔር ንበር እስከ ዕለተ ሞትከ ውስተ ዝንቱ በዓት ወአእምራ ለሔዋን በግብር ብዙኑ ወተባዝኑ ወምልዕዋ ለምድር። ዘፍ ፩÷፳፰-፳፱

ከዚህም በኋላ ቅዱስ ገብርኤል የአዳም ጠባቂ መልአኩ ነውና አንስቶ ዳሶ ፈውሶ አንተስ ሁልጊዜ ምን ያዘናጋሃል ምግብህን ነው አስግብቼልሃለሁ። አሁንም እስከ ጊዜ ሞትህ ድረስ ከዚህ ዋሻ አትውጣ። ሔዋንንም በግብር እወቃት ክበዱ ውለዱ ምድርንም ምሏት ብሏችኋል እግዚአብሔር አለው።ዘፍ 1÷28-29

አዳምም አቤቱ ጌታዬ ፈጣሪዬስ እኔን በአምስት ቀን ተኩል እመጣልሃለሁ ብሎኝ ነበር። ምንስ ከዚያ ላይ ሆ ቢያነጋ ግረኝ ያ የቀደመ ጠላቴ ዲያብሎስ ይሆንን አለው። ቅዱስ ገብርኤልም ጠላትህ ዲያብሎስ አይደለም ወዳጅህ እግዚአ ብሔር ነው እንጂ አለው። ይኸውም አምስት ቀን ተኩል ያለው አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን ነው። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ከልጅ ልጅህ እወለዳለሁ ብሎሃልና ዛሬ ልጅን ወልደሃልን ከማነኛይቱ ልጅህ ይወለድ ይመስልሃል፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ይቅርታው ቸርነቱ ያለጊዜው አይሆንምና አይ ሀ አለው።

ክፍል ሰባት

፩. ሣህሉ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ እንዘ ብዙኅ ሣህልከ
መዝ ፷፰÷፲፫-፲፬
አቤቱ በምሕረትህ ብዛት በማዳንህም እውነት አድምጠኝ
መዝ 68÷13-14

፪. ወቦአ አዳም ውስተ በዓቱ ወገብረ ከብካበ ፍሬሃኒ ወጽጌሃኒ ወቈጽላኒ ለገነት ወወሀባ ለሔዋን ኅፄሃ ወርቀ ከርቤ ወስኒነ።

አዳምም ከቅዱስ ገብርኤል ተሰናብቶ ከበዓቱ ገብቶ አዕዋፍ አንስርት ካመጡለት ፍሬያት ጽጌያት ሠርግ አደረገ፤ መልአኩም ቅዱስ ገብርኤል ወርቅ ከርቤ ስኒን /ዕጣን/ ሰጥቶት ነበርና ይኸንም ለሔዋን ማጫ ሰጣት።

፫. ወእምዝ አእመራ አዳም ለሔዋን ወፀንሰት ወወለደቶሙ ለቃየል ወለሉድ። ዘፍ ፬÷፩-፫
ከዚህም በኋላ አዳም ሔዋንን በግብር አወቃት ፀነሰች ቃየልንና ሉድን ወለደች። ዘፍ 4÷1-3

፬. ወእምዝ ዳግመ አእመራ አዳም ለሔዋን ወፀንሰት ወወለደቶሙ ለአቤል ወለአቅሌማ። ዘፍ ፬÷፩-፫
ዳግመኛም አዳም ሔዋንን በግብር አወቃት አቤልና አቅሌማን ወለደች። ዘፍ 4÷1-3

፭. ወአመ አብጽሑ ውርዛዌ ይቤሎሙ አዳም ለደቂቁ አቤል ያውስባ ለሉድ ወቃየል ያውስባ ለአቅሌማ ወተዋሰቡ በሥርዓተ ሕግ።

እነዚህም ተወልደው አድገው አካለ መጠን ሲደርሱ አዳም ትውልድ ያራራቀ መስሎት ከአቤል ጋር የተወለደችውን አቅሌማን ቃየል ያግባ፤ ከቃየል ጋር የተወለደችውን ሉድን አቤል ያግባ በሥርዓተ ሕግ ተጋቡ ብሎ አዘዛቸው።

፮. ወዝ ውእቱ ምክንያተ ጽልዐ ለቃየል ምስለ አቤል እስመ ይቤሎሙ አዳም ለደቂቁ አቤል ያውስባ ለሉድ ወቃየል ያውስባ ለአቅሌማ ወይቤ ቃየል ዘንተሰ ኢይገብር እግዚአ ብሔር ከመ አህብ ሠናይትየ ለካልእ ወእንግእ ክፍዕተ ዘካልእ።

ከዚህም በኋላ በአቤልና በቃየል መካከል ፀብ ቂም ተነሣ። ጠቡስ ምንድን ነው ቢሉ ከአቤል ጋር የተወለደችው አቅሌማ መልከ ክፉ ናት ከቃየል ጋር የተወለደችው ሉድ መልከ መልካም ቆንጆ ናት ሔዋንን እናቷን ትመስላለች። አዳምም ትውልድ ያራራቀ መስሎት እንዲህ ብሎ ቢያዝዝ ቃየል እንዲህስ ያለውን ነገር እንኳን አንተ እግዚአብሔርም ቢሆን አያደርገውም የእኔን መልከ መልካም ለሰው ሰጥቼ የሰው መልከ ክፉ ለእኔ እወስዳለሁን ብሎ ፀብ ቂም በቀል አነሣ።

፯. ወይቤሎሙ አዳም ለደቂቁ ሑሩ ወግበሩ መሥዋዕተ ውስተ ደብር ወዘሠምሮ እግዚአብሔር ያውስባ ለሉድ።

አዳምም ከተጣላችሁስ በየራሳችሁ ከተራራ ላይ ወጥታችሁ መሥዋዕት ሠው እና መሥዋዕቱን እግዚአብሔር የተቀበለ ለት መልካሚቱን ሉድን ያግባ አለ።

፰. ወነጸረ እግዚአብሔር መሥዋዕተ አቤል ወተወክፈ ሎቱ፡፡ ዘፍ ፬÷፬-፭

ከዚህም በኋላ አቤልና ቃየል ከተራራ ላይ ወጥተው በየራ ሳቸው መሥዋዕት አሠመሩ እግዚአብሔርም የአቤልን መሥዋዕት አይቶ ተቀብሎለት ከሰማየ ሰማያት ወርዶ እሳት መሥዋዕቱን አቃጥሎ ሣሩን እንጨቱን ድንጋዩን ወኃውን ላስ አድርጐ ወደ ሰማየ ሰማያት አረገለት ከእግዚአብሔር ዘንድ ደረሰለት፡፡ ዘፍ 4÷4-5

፱. ወሮፀ አቤል በፍሥሐ እንዘ ያንፈርዕፅ ከመ ይርአያ ለሉድ፡፡

አቤልም የመሥዋዕቱ ነገር ደስ ደስ እያሰኘው ሉድን ለማ የት ከፊት ከፊት እየሮጠ ሄደ፡፡

፲. ወተራከቦ ሰይጣን ለቃየል ወይቤሎ ኦ ኃያል ወሬዛ ዘኢይደ ልወከ ኀዘን ወኢምንተኒ ዘእንበለ ፍሥሐ አሐተ ሰዓተ፡፡ ዘፍ ፬÷፭-፮

ቃየልም በመሥዋዕቱ እያዘነ እየተከዘ ከኋላ ከኋላ ሲሄድ ሰይጣን በመንገድ ቆይቶ አንተ ኃያል ወሬዛ ምን ሆነሃል ምን ያሳዝንሃል ከመግዛት በቀር መገዛት ከማዘዝ በቀር መታዘዝ የማይገባህ አለው፡፡ ዘፍ 4÷5-6

ቃየልም እኔ አላዝን ማን ይዘን አባቴ አድልቶብኝ ወንድሜ ጐልብቶብኝ እግዚአብሔርም ተጨምሮብኝ የእኔን መልከ

መልካም ለሰው ሰጥቶ የሰውን መልከ ክፉ ለእኔ ሰጥቶኝ በዚህ አዝኖለሁ አለው።

፲፩.ወይቤሎ ዲያብሎስ መኑ ዘይበለከ ብከኑ ካልእ አብ ወሚመ ዝንቱ ዘጠፍዓ ልቡ አመ ወፅአ እምገነተ ንግሡ ወይነብር ከመ ግሔ ውስተ በዓት እንዘ ያስከሀክህ።

ዲያብሎስም እንዲህ ያለውን ነገር ማን ያደርገዋል ያ ከገነት የወጣ ዕለት ልቡን ያጣ በባዶ ዋሻ እንደ እሽ እያሸካካ አሥሩን የሚናገር አባትህ ነውን ወይስ ሌላ አባት አለህ? አለው። ቃየልም አዎን እርሱ ነው ሌላም አባት የለኝ አለው።

፲፪.ወይቤ ዲያብሎስ መሐል ሊተ ከመ ትግበር ፈቃድየ ወኪያ ሁሰ እመ ኢረሰይክዎ ዓዘቅተ አንብዕ በሞተ ወልዱ ዘያፈ ቅሮ ኢትበለኒ አርክየ።

ዲያብሎስም የእኔን ምክር ስማ ፈቃዴን ፈጽም እጄን በእጅህ ጸፍተህ/መትተህ/ ማልልኝ እንጂ በዚያ በሚወደው በልጁ ሞት የዕንባ ዓዘቅት አድርጌ ባላሳይህ ወዳጄ አትበ ለኝ አለው።

፲፫.ወእምዘ ዘይኤይስ ምክር አልቦ ዘትረክብ እመኒ ዓረገ ሰማየ ወእመኒ ወረድከ ውስተ ምድር ወታወስቦን ለፀሐን።

ቃየልም ምክሩን ሊሰማ ፈቃዱን ሊፈጽም እጁን በእጁ ጸፍቶ/መትቶ/ ማለለት። ሲምልለትም ጊዜ እንካ ይህችን

ድንጋይ ይዘህ ሄደህ ከወንድምህ ከአቤል ሩጠህ ድረስበት፤ ተጐንብሶ ውኃ ሲጠጣ ታገኘዋለህ ያን ጊዜ በዚህ ድንጋይ ጆሮ ጥላውን መተህ ጣለው ሲሞትልህም ሁለቱንም ታገባ ቸዋለህ እንዲህ ያለ ምክር ወደ ሰማይ ብትወጣ ወደ ምድር ብትወርድ አታገኝም አለው።

፲፬.ወሰበ ሰምዓ ዘንተ ቃየል ነሥአ ዕብነ እምዕደ ሰይጣን ወሮፀ ወረከቦ ለአቤል እንዘ ያስተበርክ ከመ ይስተይ ማየ ወሶቤሃ ዘበሠ ማዕከለ ክሳዱ ወሥርወ ዕዝኑ ወሞተ ጻድቅ አቤል በእደ ቃየል እኁሁ። ዘፍ ፬፥፰-፱

ቃየልም ይህንን ምክር ሰምቶ ከዲያብሎስ እጅ ያችን ድን ጋይ ተቀብሎ እየሮጠ ሄዶ ከአቤል ከወንድሙ ዘንድ ደረሰ። አቤልም እንስሳት አራዊትን ሲፈራ ነበርና እሰይ ወንድሜ ሊቆምልኝ መጣ ብሎ ተጐንብሶ ውኃ ሲጠጣ ሳለ አንገት ሥሩን ጆሮ ጥላውን መቶ ጣለው አቤልም በወንድሙ በቃየል እጅ ሞተ። ዘፍ 4÷8-9

፲፭.ወሐረ ቃየል ኀበ እመ ወትቤሎ እመ ወልድየ ቃየል አይቴኑ ሖረ አቤል እኁከ።ወይቤላ ለእመ ቦኑ አነ ዓቃቤሁ ለአቤል ወይቤ ሀብኒ በትርየ።

ቃየልም ወንድሙን አቤልን ገድሎ እናቱ ከአለችበት ዋሻ ሄዶ ገባ። ሔዋንም ልጄ ቃየል እንካን በደህና ገባህ ወንድ ምህ አቤልስ የት ቀረ አለችው። ቃየልም እኔ ለአቤል

አውሬ ቢጐትተው አሞራ ቢበትነው ጠባቂው ነኝን ከዚያ ሁሉ በትሬን ስጪኝ ብሎ ተቆጥቶ ወጥቶ ሄደ።

፲፯.ወሐረት ሔዋን ወነገረቶ ለአዳም ብእሲሃ

ሔዋንም ሄዳ አዳምን ቃየል መጣ አቤል ቀረ አለችው። ቃየልንም ወንድምህ አቤል የት ቀረ ብዬ ብጠይቀው ተቆጥቶ ወጥቶ ሄደ እስኪ አንተ ወጥተህ ፈልገው አለችው።

፲፰.ወይቤሎ አዳም ለቃየል ወልድየ ቃየል አይቴኑ ሖረ አቤል እኁከ።

አዳምም ቃየል ወደአለበት ሄዶ ልጄ ቃየል እንኳን ደህና ገባህ ወንድምህ አቤል ወዴት ሄደ አለው።

፲፱.ወይቤሎ ቃየል ለአዳም አቡሁ አቤልሰ ሖረ ውስተ ገዳም ከመ ያስተጋብዕ ፍሬያተ ወጽጌያተ ለሉድ ዘፈጋርከ ሎቱ።

ቃየልም ለአጨህለት ለሉድ ፍሬያቱን ጽጌያቱን ሊሰበስብ ወደዱር ሄዶ መሰለኝ አለው። አዳምም እንስሳት አራዊትን ሲፈራ ነበርና አንተ ክፉ የት ትተኸው መጣህ ይሆን ብሎ ጮኸበት።

፳፬.ኦ አብ እኩይ ዘአፍቀረ ወልዶ እምወልዱ ቦኑ አነ ዓቃቢሁ ለአቤል። ዘፍ ፬÷፬-፲

ቃየልም አንተ የአባት መድሎኛ እኔ አቤልን አውሬ ቢጐት ተው አሞራ ቢገትነው ጠባቂው ነኝን ብሎ አውጥቶ አውርዶ አየው ከፍ ዝቅ አድርጐ ተናገረው። ዘፍ 4÷9-10

፳. ወተመይጠ አዳም እምድኅሬሁ ወርእያ ለማይ ከዊና ደመ ወአእመረ ሶቤሃ ከመ ሞተ ወልዱ ወገዓረ በቃሉ።
አዳምም ከመንገዱ በስተኋላ ውኃ ነበረችና ዙሮ ቢያያት ደም መስላ አያት አዳምም ልጁ አቤል እንደ ሞተ ጠረጠረ።

፳፩.ወሖረ አዳም ምስለ ብእሲቱ ሔዋን ወረከቦ ለአቤል ግዱፈ በገጹ ወኃቀፎ ክሳዶ ወይቤሎ አዳም ለአቤል ወልድየ አንተ መኑ ቀተለከ።
ከዚህም በኋላ አዳምና ሔዋን እየተጯጯሑ ቢሄዱ አቤል ሞቶ በአፍንጫው ተደፈቶ አገኙት። አዳምም አንገቱን በአንገቱ እቅፍ አድርጐ ይ ልጄ አቤል ማን ተጫወተ ብህ ማን ገደለህ እባክህ ንገረኝ እያለ ያለቅስ ይጨነቅ ጀመር።

፳፪.ወተናገረት በድኑ ለአቤል እንዘ ትብል ቃየል እኁየ ቀተለኒ።
ዘፍ ፬÷፱-፲፩
የአቤልም በድኑ ቃየል ወንድሜ ገደለኝ ብላ ተናገረች።
ዘፍ 4÷9-11።
የአቤልም በድኑ እንደተናገረች ጳውሎስ እንዲህ ሲል ተናግሯል።

፳፫.ወበእንተአሁ ሰማዕተ ከመ ጻድቅ ውእቱ ወሰማዕቱ እግዚአብሔር በተወክፎ መሥዋዕቱ ወበእንተአሁ መዊቶ ዓዲ ተናገረ። ዕብ ፲፩÷፬-፭

በዚህም እግዚአብሔር ስለ ስጦታው ሲመሰክር እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ተመሰከረለት፤ ሞቶም ሳለ በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል። ዕብ 11÷4-5

፭፬.ወነደገ አዳም ረጊሞቶሙ ለእንስሳት ወለአራዊት እስመ መሰሎ ዘተጸብዕዎ ወልዶ።

አዳምም እንስሳት አራዊት የተጣሉት መስሎት ይራገም ነበርና መራገሙን ተወ።

፭፭.አ ሔዋን እንተ አፍዓምክኒ እምይእቲ ዕፅ አዕዳውኪ ይትመተራ። ወእምዝ አኀዘ ይብኪ አዳም ምስለ ሔዋን ብእሲቱ እፎ ዘአፍቀርኩ ወአውረስኩ ሞተ ለደቂቅየ ለትውልደ ትውልድ።

አዳምም ሔዋንን ያችን ቁጽለ በለስ ቁርጠሽ በአፌ ያደረግ ሽልኝ ቀን ምነው እጆችሽ አብረው ተቁርጠውልኝ ቢሆን እንዴት ቤት፣ ከብት፣ ንብረት እንደማውረስ ለልጅ ልጅ ሞት አወረስሁ ለዘለዓለም የማያልቅ መከራ አገኘኝ እያለ ያለቅስ ይጨነቅ ጀመር።

፭፮.ወይቤ አዳም ንዑ ብክዮኒ በእንተ እግዚአብሔር ለእኁክሙ አቤል ኦ ማኅበረ መላእክተ ሰማይ ወፍጥረታተ ምድር እለ ነበርኩ ምስሌክሙ እስመ ንኩ ተፈጢርየ ከመ ዘኢተፈጠርኩ።

ከዚህም በኋላ ዛሬ በዚህ ዓለም ያለ ሰው እናቱ አባቱ ሞቶበት የራቀ የቀረበውን ዘመድ ሰብስቦ እንዲያለቅስ እንዲጨነቅ

ሁሉ አዳምም እባካችሁ በምድር ያላችሁ ፍጥረታት በሰማይ ያላችሁ መላእክት በእንተ እግዚአብሔር ለወንድማችሁ ለአቤል አልቅሱለት ተፈጥሬ እንዳልተፈጠርሁ የሆንሁ እኔ ነኝ እያለ ያለቅስ ይጨነቅ ጀመር።

፳፯.ወይቤልዎ መላእክት ለአዳም ብሥራትከ ኦ አዳም ወልድ ከሰ አቤል ተሳለማ ለዕፀ ሕይወት በነፍሱ ወዓርገ በፍሥሐ ከመ መሥዋዕት ውክፍት ወአዕረፈት ነፍሱ ውስተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት።

ከዚህም በኋላ ዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት ወርደው አዳምን ልጅህ አቤል ገነት ገብቶ ዕፀ ሕይወትን ተሳለማት በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ተወደደች መሥዋዕት በኢየሩሳሌም ሰማያዊት አረፈባት አሉት።

፳፰.ወሶበ ሰምዓ አዳም ዘንተ ቃለ ተናዘዘ ወቀበሮ ለአቤል ወልዱ።

አዳምም ይህን ሰምቶ ልጁን አቤልን ቀበረው፤ ኩነዘኑም ተረጋጋ።

፳፱.ወጐየ ቃየል እምገጸ አቡሁ ወኢተርእየ ዳግመ ኀ ርቱመ ወውጉዘ በዝ ዓለም ወበዘይመጽእ ዓለም። ዘፍ ፬፥፲፩-፲፫

ቃየል ወደ ኦት ደረሰ ቢሉ ቃየልንስ እንኳን በዚህ ዓለም በወዲያኛውም ዓለም ከሰው አትገናኝ ርጉም ውጉዝ ሁን

ብሎ አዳም ረግሞታልና አባቱም እናቱም አላገኘትም ዕለቱን ወጥቶ ሄደ። ዘፍ 4÷11-13

፴. ወረገሞ እግዚአብሔር ለቃየል እንዘ ይብል ኩን ርዑደ ወድንጉፀ ወቅጥቋጠ ወበቅድመ ኩሉ ሰብእ ለትርዓድ ብረኪከ ወኩሎሙ እለ ይተልው ግብረከ።ዘፍ ፬÷፲፩-፲፫

ቃየልንስ አዳም ብቻ ረግሞት አልቀረም ጌታም ረግሞታል። ምን ብሎ ረገመው ቢሉ አካልህ ይራድ እጅህ እግርህ ይንቀጥቀጥ የአንተን ሥራ የሠሩ ሁሉ የአንተ ርግማን ይደርባቸው ብሎ ረገመው። ዘፍ 4÷11-13

፴፩.ዮምኒ ከማሁ ዘይገብር እኩየ ላዕለ ሰብእ እመኒ በሐሜት ወእመኒ በቀቲል ኢይፈጽም ነገሮ ዘእንበለ ይትመያየጥ ለፈ ወለፈ።

ይህም ይታወቅ ዘንድ ዛሬ ሰው በሐሜትም ቢሆን ነፍስ በመ ግደልም ቢሆን ወዲያና ወዲህ ሳያይ ፈቃዱን አይፈጽምም።

፴፪.ወአማዕሰበ አዳም ፱ተ ዓመተ ሰብእናሁ በ፱ዘን።ኩፋ ፭÷፲፪-፲፫

ከዚህም በኋላ አዳም በ፱ዘን ተመክሮ ሰባት ዓመት ተቀመጠ። ኩፋ 5÷12-13

ክፍል ስምንት

፩. ወእምዝ አእመራ አዳም ለሔዋን ወጸንስት ወወለደቶ ለሴት በከመ አምሳሊሁ ለአቤል ምስለ ካልእቱ። ዘፍ ፬÷፳፭-፳፮

ከዚህም በኋላ አዳም ሔዋንን በግብር አወቃት ፀነሰችም ሴት የሚባል ልጅ አቤልን አስመስላ ከነመንትያው ወለደች። ዘፍ 4÷25-26

፪. አዳም ወለዶ ለሴት፤ ወሴት ወለዶ ለሄ ስ፤ ወሄ ስ ወለዶ ለቃይናን፤ ወቃይናን ወለዶ ለመላልኤል፤ ወመላልኤል ወለዶ ለያሬድ፤ ወያሬድ ወለዶ ለሄ ክ፤ ወሄ ክ ወለዶ ለማቱሳላ፤ ወማቱሳላ ወለዶ ለላሜህ፤ ወላሜህ ወለዶ ለ ኅ፤ ወበ ኅ ነ ማየ አይኅ። ዘፍ ፭÷፩-፴፪

ከዚህም በኋላ የአዳም ልጅ እየበዛ ሄደ። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከአዳም መወለዱ እንደምን ነው ቢሉ፡-

አዳም ሴትን ወለደ፤ ሴት ሄ ስን ወለደ፤ ሄ ስ ቃይናንን ወለደ፤ ቃይናን መላልኤልን ወለደ፤ መላልኤል ያሬድን ወለደ፤ ያሬድ ሄ ክን ወለደ፤ ሄ ክ ማቱሳላን ወለደ፤ ማቱሳላ ላሜህን ወለደ፤ ላሜህ ኅን ወለደ፤ በዚህም በ ኅ ዘመን የጥፋት ውኃ ሆነ ፍጥረቱ ሁሉ አለቀ። ዘፍ 5÷1-32

፫. ወእስከዝ ነ ትውልድ ፲ተ ወዘመኑሂ ነ ፳፻ተ ወ፪ተ ፻ተ ፵ወ፪ተ ዘመነ።

እስከዚህ ድረስ ትውልዱ አሥር ነው። ዘመኑ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሁለት ዘመን ነው።

፬. ኅ ወለዶ ለሴም፤ ወሴም ወለዶ ለአርፋክስድ፤ ወአርፋክስድ ወለዶ ለቃይንም፣ ወቃይንም ወለዶ ለሳላ፤ ወሳላ ወለዶ ለኤቦር፤ ወኤቦር ወለዶ ለፋሌቅ፤ ወፋሌቅ ወለዶ ለራግው፤ ወራግው ወለዶ ለሤሩህ፤ ወሤሩህ ወለዶ ለና ር፤ ወና ር ወለዶ ለታራ፤ ወታራ ወለዶ ለአብርሃም። ዘፍ ፲፩፥፲-፳፰

ከዚህም ከጥፋት ውኃ በኋላ ኅ ሴምን ወለደ፤ ሴምም አርፋክስድን ወለደ፤ አርፋክስድም ቃይንምን ወለደ፤ ቃይንም ሳላን ወለደ፤ ሳላም ኤቦርን ወለደ፤ ኤቦርም ፋሌቅን ወለደ፤ ፋሌቅም ራግውን ወለደ፤ ራግውም ሴሮሕን ወለደ፤ ሴሮሕም ና ርን ወለደ፤ ና ርም ታራን ወለደ፤ ታራም አብርሃምን ወለደ። ዘፍ 11፥10-28

፭. ነዋ ተወጥነ በአብርሃም ተውህቦተ ግዝረት ወማኅረስ በእን ስሳ ወእምቅድመ ዝ ነበሩ አበው እንዘ ኢየሐርሱ።

በዚህም በአብርሃም ዘመን እያረሱ መብላት፣ በስምንት ቀን ግዝረት ተሰጠ። ከአብርሃም በፊት የነበሩ አባቶች እንደምን ይ ሩ ነበረ ቢሉ እንዲያው እየዘሩ እየበቀለላቸው እየበሰ ለላቸው ሲበሉ ይ ሩ ነበረ። በአብርሃም ጊዜ ግን እየዘሩ ሲተውት አዕዋፍ እየለቀሙ ይበሉባቸው ጀመር።

አብርሃምም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ በዚያም ጊዜ መልአኩ ወርዶ በሬዎችን፣ ማረሻውን፣ ወገሉን አስተካክሎ ሰጥቶት

አንድ ጊዜ እያለበሳችሁ ተውት አላቸው። አንድ አንድ ጊዜ እያለበሱት እየበቀለላቸው ሲበሉ ይ ሩ ነበር። ኋላ ግን ኃጢ አት በዛች ምድር ጸናች ሰባት ጊዜ ስምንት ጊዜ ትታረስ ጀመረች።

የግዝረትስ ነገር እንደምን ነው ቢሉ አሥምር በቅድሜከ አለው እንዲህም ማለቱ ልጅህን በስምንት ቀን ግዘረው ሲል ነው። ዘፍ 17÷11-13

ይኸውም የጥምቀተ ክርስትና አምሳል ነው። ወንድ በአርባ ቀን ሴት በሰማንያ ቀን ክርስትና ካልተነሱ ክርስቲያን አይባሉም እናት አባታቸው ለካህናቱ ሳይናገሩ ያሳለፉት እንደሆን ከምዕመናን ተለየተው ሦስት ዓመት ይጹሙ። ካህናቱም እናት አባት ነግረዋቸው አናነሳም ብለው ያሳለ ፉት እንደሆን ሦስት ዓመት ይጹሙ።

፮. ወእስከዝ ነ ትውልድ ፳ወ፩ ወዘመን ፴፻ወ፫፻ወ፳ ወ፰ቱ። እስከዚህ ድረስ ትውልዱ ሀያ አንድ ነው። ዘመኑም ሦስት ሽህ ሦስት መቶ ሀያ ስምንት ነው።

፯. አብርሃም ወለዶ ለይስሐቅ፤ ወይስሐቅ ወለዶ ለያዕቆብ፤ ወያዕቆብ ወለዶ ለይሁዳ፤ ወይሁዳ ወለዶ ለፋሬስ፤ ወፋሬስ ወለዶ ለኤስሮም፤ ወኤስሮም ወለዶ ለአራም፤ ወአራም ወለዶ ለአሚናዳብ፤ ወአሚናዳብ ወለዶ ለነዓሶን።ማቴ ፩÷፪-፭

አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅ ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብ ይሁዳን ወለደ፤ ይሁዳ ፋሬስን ወለደ፤ ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፤

ኤስሮም አራምን ወለደ፤ አራም አሚናዳብን ወለደ፤ አሚና ዳብ ነአሶንን ወለደ። ማቴ 1÷2-5

፰. ነዋ ተፈጸመ ዘመነ አበው ወእምዝ ተወጥነ ዘመነ መሳፍንት በሙሴ ወእስከዝ ነ ትውልድ ፳ወ፱ ወዘመን ነ ፴፻ወ፯፻ ፶ወ፫ቱ።

እስከዚህ ድረስ ዘመነ አበው ነው። ዘመነ መሳፍንት በሙሴ ተጀመረ። ትውልዱ ሀያ ዘጠኝ ነው፤ ዘመኑ ሦስት ሽህ ሰባት መቶ አምሳ ሦስት ሆነ።

፱. ነዓሶን ወለዶ ለሰልሞን፤ ወሰልሞን ወለዶ ለቡዔዝ፤ ወቡዔዝ ወለዶ ለኢዮቤድ፤ ወኢዮቤድ ወለዶ ለዕሤይ፤ ወዕሤይ ወለዶ ለዳዊት ንጉሥ። ማቴ ፩÷፭-፯

ነዓሶን ሰልሞንን ወለደ፤ ሰልሞን ቡዔዝን ወለደ፤ ቡዔዝ ኢዮቤድን ወለደ፤ ኢዮቤድ ዕሤይን ወለደ፤ ዕሤይ ዳዊትን ወለደ። ማቴ 1÷5-7

፲. ነዋ ተፈጸመ ዘመነ መሳፍንት ወእምዝ ተወጥነ መንግሥት በዳዊት ዘቤተ ይሁዳ ወሊቀ ካህናት በሳሙኤል ወእስከዝ ነ ትውልድ ፴ወ፬ቱ ወዘመን ነ ፵፻ወ፬ቱ፻ት ፶ወ፮ቱ።

እስከዚህ ድረስ ዘመነ መሳፍንት ነው። የቤተ እስራኤል መንግሥት በዳዊት ተጀመረ ሊቀ ካህናትነት በሳሙኤል ተጀመረ ትውልዱ ሠላሳ አራት ዘመኑ አራት ሽህ አራት መቶ አምሳ ስድስት ሆነ።

፪ የ፲ኟ

፲፩.ዳዊት ወለዶ ለሰሎሞን፤ ወሰሎሞን ወለዶ ለሮብዓም፤ ወሮብዓም ወለዶ ለአብያ፤ ወአብያ ወለዶ ለአሣፍ፤ ወአሣፍ ወለዶ ለኢዮሳፍጥ፤ ወኢዮሳፍጥ ወለዶ ለኢዮራም፤ ወኢዮራም ወለዶ ለያዝያን፤ ወያዝያን ወለዶ ለኢዮአታም፤ ወኢዮአታም ወለዶ ለአካዝ፤ ወአካዝ ወለዶ ለሕዝቅያስ፤ ወሕዝቅያስ ወለዶ ለምናሴ፤ ወምናሴ ወለዶ ለአሞፅ፤ ወአሞፅ ወለዶ ለኢዮስያስ፤ ወኢዮስያስ ወለዶ ለኢዮአቄም፤ ወኢዮአቄም ወለዶ ለኢ ንያን። ማቴ ፩÷፮-፲፪

ዳዊት ሰሎሞንን ወለደ፤ ሰሎሞንም ሮብዓምን ወለደ፤ ሮብዓ ምም አብያን ወለደ፤ አብያም አሣፍን ወለደ፤ አሣፍም ኢዮሳፍጥን ወለደ፤ ኢዮሳፍጥም ኢዮራምን ወለደ፤ ኢዮራ ምም ያዝያንን ወለደ፤ ያዝያንም ኢዮአታምን ወለደ፤ ኢዮአታምም አካዝን ወለደ፤ አካዝም ሕዝቅያስን ወለደ፤ ሕዝቅያስም ምናሴን ወለደ፤ ምናሴም አሞፅን ወለደ፤ አሞፅም ኢዮስያስን ወለደ፤ ኢዮስያስም ኢዮአቄምን ወለደ፤ ኢዮአቄምም ኢ ንያንን ወለደ። ማቴ 1÷7-12

፲፪.ነዋ ተፈጸመት መንግሥት በኢ ንያን ወፈለሰት ኢየሩሳሌም ኀበ መንግሥተ ባቢሎን ወእስከዝ ኀ ትውልድ ፱ወ፩ ወዘመንሂ ኀ ፵፱ወ፬፱ ፲ወ፮።

በዚህም በኢ ንያን ዘመን ጴዋዌ/ምር / ሆነ እስራኤል ተማርከው ወደ ባቢሎን ወረዱ የእስራኤል መንግሥት ወደ መንግሥተ ባቢሎን ፈለሰች/ተሰደደች/ እስከዚህ ድረስ

ትወልዱ አምሳ አንድ ዘመኑ አራት ሽህ ዘጠኝ መቶ አሥራ ስድስት ሆነ።

፲፫.ኢ ንያን ወለዶ ለሰላትያል ወሰላትያል ወለዶ ለዘሩባቤል።

ማቴ ፩÷፲፪-፲፫

ኢ ንያን ሰላትያልን ወለደ ሰላትያል ዘሩባቤልን ወለደ።

ማቴ 1÷12-13

፲፬.ወበመንግሥተ ዘሩባቤል ነ ሚጠት ወገብኡ እስራኤል ውስተ ሀገሮሙ በ፷ ዓመት ምስለ ክህነት ወመንግሥት ወእምዝ ተወጥነ ሊቀ ካህናት በሆሴዕ ወመንግሥት በዘሩባቤል ወእስከዝ ነ ትውልድ ፶ወ፬ ወዘመንሂ ፵፻ ወ፱፻ ፹ወ፯ቱ።

በዚህም በዘሩባቤል መንግሥት ጊዜ እስራኤል በተማረኩ በሰባ ዘመናቸው ክህነትን ከመንግሥት ጋር ይዘው ወደ አገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ። እስከዚህ ድረስ ትውልዱ አምሳ አራት ዘመኑ አራት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሰባት ሆነ።

፲፭.ዘሩባቤል ወለዶ ለአብዩድ፤ ወአብዩድ ወለዶ ለአዛር፤ ወአዛር ወለዶ ለኤልያቄም፤ ወኤልያቄም ወለዶ ለሳዶቅ፤ ወሳዶቅ ወለዶ ለአኪም፤ ወአኪም ወለዶ ለኤልዩድ፤ ወኤልዩድ ወለዶ ለአልዓዛር። ማቴ ፩÷፲፪-፲፮

ዘሩባቤል አብዩድን ወለደ፤ አብዩድ አዛርን ወለደ፤ አዛር ኤልያቄምን ወለደ፤ ኤልያቄምም ሳዶቅን ወለደ፤ ሳዶቅም

አኪምን ወለደ፤ አኪምም ኤልዩድን ወለደ፤ ኤልዩድም አልዓዛርን ወለደ። ማቴ 1÷12-16

፲፮.ወአልዓዛር ወለዶ ለቅስራ፤ ወቅስራ ወለዶ ለኢያቄም፤ ወኢያቄም ወለዳ ለእግዚእትነ ማርያም፤ ወእግዝእትነ ማርያም ወለደቶ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘክሮቱ ይደሉ ሰጊድ።

አልዓዛርም ቅስራን ወለደ፤ ቅስራም ኢያቄምን ወለደ፤ ኢያቄምም እግዝእትነ ማርያምን ወለደ፤ እግዝእትነ ማርያምም ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደችው።

፲፯.ወአልዓዛር ወለዶ ለማታን ወማታን ወለዶ ለያዕቆብ፤ ወያዕቆብ ወለዶ ለዮሴፍ ዘውእቱ ፈጻሪሃ ለእግዝእትነ ማርያም፤ ወዮሴፍ ወለዶ ለያዕቆብ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም። ማቴ ፩÷፲፮-፲፯

ዳግመኛም ትውልድ አልዓዛርም ማታንን ወለደ፤ ማታንም ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ዮሴፍን ወለደ ዮሴፍም የእግዝእትነ ማርያም ጠባቂዋ ሞግዚታ ነው።ማቴ 1÷16-17

ይኸውም ዮሴፍ የኢየሩሳሌምን ኤጲስ ቆጶስ ማር ያዕቆብን ወለደ።

፲፰.ወእስከዝ ነ ትውልድ ፷ወ፮ ወዘመን ነ ፶፪ወ፭፪።

እስከዚህ ድረስ ትውልዱ ስድሳ ስድስት ነው። ዘመኑም አምስት ሺህ አምስት መቶ ነው።

እስከዚህ ያለው ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ይባላል።



ሰአሊ ለነ ቅድስት
ቅድስት ሆይ ለምኝልን

አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ግን በገጽ ፪፻፷ ቁጥር ፲፫ ላይ እንደተጠ ቀሰው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳም በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከልጅ ልጅህ ከተባለችው ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስክ ላይ ድሆ በቀራንዮ አደባባይ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ለባሕርይ አባቱ ክሶ ከዲያብሎስ አገዛዝ ነፃ አደረገው፤ ከሲኦል አወጣው ገነትም አስገባው፤ የሰጠውም ተስፋ በዚህ ተፈጸመ። በዚህም ምክንያት ከዚህ በኋላ ያለው ዘመን ዓመተ ሥጋዌ፣ ዓመተ ምሕረት ተባለ።

፲፱.ተፈጸመ ሥነ ፍጥረት መጽሐፈ ቅዱስ ኢጲፋንዮስ ዳግማይ ሙሴ እስመ ፈከረ ዳግማየ ኦሪተ ዘውእቱ አክሲማሮስ።

ሁለተኛ ኦሪትን የተረጐመ ይህውም የሁለተኛው ሙሴ የቅዱስ ኤጲፋንዮስ የሥነ ፍጥረት መጽሐፈ አክሲማሮስ ተፈፀመ።

እስከዚህ ድረስ የዕለተ ዓርብ ሥነ ፍጥረት ነው። ዓርብ ማለት ስድስት ዕለት ማለት ነው። ዓርብ ለፍጥረት ስድስተኛ ለቀመር አራተኛ ለዐሐይ ሦስተኛ ማለት ነው። ስድስት ዕለት ሀያ ሁለት ሥነ ፍጥረት ይህ ነው። ይህስ የተፈጸ መው በምን ቀን ነው ቢባል ሚያዝያ አራት ቀን ነው።

የስድስት ቀን ሥነ ፍጥረት ከብዙ በጥቂቱ ከሙሉ በከፊል ደረሰ ተፈጸመ።

አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን የፍጥረታት ፈጣሪ ክብር ምስጋና ይድረሰው አሜን።

